# ማውጫ


* በረሃ ላይ በተሰራው አስዋን ግድብ ብቻ ከ10 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር በላይ ውሃ ይባክናል
* በሦስቱም የህዳሴ ግድብ ሙሌት ግብጽም ሆነች ሱዳን ተጠቅመውበታል እንጂ አልተጎዱም

3





የቀንዱ **ቀንደኛ** ሀገር ተጋድሎ 12

18 አልገፋ ያለው ዳገት

ቡናችን 19





«ኢትዮጵያ በሯን ከርችማ ብቻዋን መኖር አትችልም»
አቶ ኢየሱስ ወርቅ ዛፉ

8

የኢትዮጵያ ብዝሃ ሕይወት ሀብት እና አጠባበቅ 23





በበጎ ሰው ሽልማት የደመቀው በጎነት 41

የዳሉል ስምጥ ሸለቆ ሳይንሳዊ ይዘት፣ አስደናቂ ውበት እና እምቅ የተፈጥሮ ሃብት

34

አዲስ ሥርዓተ-ትምህርት ለምን ? 29

ዘመን ህዳር 2015

# ርዕሰ አንቀጽ

## ከተጠያቂነት ጎንለጎን ሌብነትን የሚፀየፍ ዜጋ እንፍጠር!

በሀገር ደረጃ ሙስና ወይም ሌብነት ዝርፊያ ያስከተለውን ኪሳራ ከፍ ተደርጎ ሲነገር ችግሩ በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ ያመጣውን ተፅዕኖና ውጤት ቶሎብለን ላናስበው እንችላለን።በተለያየ የሕዝብም ሆነ የግል መገልገያ ሀብትና ንብረት ላይ ሌብነት እያደረሰ ያለው ኪሳራ ከእያንዳንዳችን ኪስ ውስጥ የተዘረፈ ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል።አገልግሎት ለማግኘት በምንሄድባቸው ተቋማት ተገቢው ምላሽ አለማግኘት፣አላግባብ ተጨማሪ ክፍያ እንድንከፍል መገደድ በዚህ መሐል ያጠፋነው ጊዜ፣ ገንዘብና ጉልበት ከኑሯችን ላይ እየቀማ ያለው ብዙ ነገር አለ፡፡

በተለያዩ አካባቢዎች በአገልግሎት አሰጣጥ ከመሬት ጋር የተያያዙ አሠራሮች፣ በፋይናንስ ዘርፍ፣ በሸያጭና ግዥ ዘርፍ፣ በፍትሕ አገልግሎት የተለያዩ የመንግሥት ተቋማት አገልግሎት መስጫውን ሁሉ ሕዝብ እየተንገላታ እየተማረረ እየተመለከትን ነው።ባለጉዳይ የሚያስፈልገውን ሁሉ አሟልቶ ቢቀርብም ጉዳዩን ለመፈፀም ገንዘብ ይጠየቃል።እርግጥ ነው በተለያዩ ጊዜያት ሙስናን ለመከላከል ያስችላሉ የተባሉ እርምጃዎች ተወስደዋል።በሙስና በመሳተፍ የተጠረጠሩትም ተጠያቂ ከማድረግ ጎን ለጎን በአንዳንድ ዘርፎች ላይም አሠራርን በቴክኖሎጂ በመደገፍና ከእጅ ንክኪ ነፃ በማድረግ ሙስናን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት ጥረት ተደርጓል ወይም መልካም ጅምሮች አሉ።ነገር ግን ሙስና አሁንም ስር እየሰደደ ነው የመጣው።

ይህንን በአግባቡ የተረዱት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የፀረ ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ መቋቋሙን ይፋ አድርገዋል።መንግሥት ሙስናን ለመቆጣጠር እና ሙሰኞችን በሕግ ተጠያቂ ለማድረግ በዚህ ደረጃ ቁርጠኝነቱን ማሳየቱ ትልቅ እርምጃ ነው፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባወጡት መግለጫ ሙስና ሀገርን የሚበላ ነቀዝ፣ የሀገርን አንጡራ ሃብት እየቦረቦረ ጥሪቷን ባዶ ለማስቀረት ሌት ተቀን የሚማስን ተባይ ነው በማለት ገልፀውታል።ሙስና የሀገር ደህንነት ስጋት ሆኗልም ሲሉ የችግሩን ስፋት ልክ አስቀምጠዋል።

ከሕግ እና ከአሠራር ማሻሻያዎች በተጨማሪ የሙስና ተዋናዮች ሁሉ ሙስናን እርም እንዲሉ የሚያደርግ እርምጃ ያስፈልጋል።ሙስና ተቀባዩም፣ሙስና ሰጪውም፣ እድል አመቻቹም ያለው ማኅበረሰብ ውስጥ ነው።አሠራሮችን በማወሳሰብ ሰው እንዲማረር በማድረግ ሙስናን አማራጭ እንዲያደርግ የሚገፉ አሠራሮችን፣ አመራሮችንና ግለሰቦችን በመጠቆም ለሕግ አሳልፎ በመስጠት መተባበር ያስፈልጋል።መንግሥት ጥርት ባለ አሠራር ተጠርጣሪዎችን በሕግ ተጠያቂ በማድረግ በየጊዜው የተወሰዱ እርምጃዎችንና የተገኙ ውጤቶችን በመግለፅ፤ ለሙስና ጠቋሚዎች ከለላ በመስጠት ይህ ጅምር እንዲሳካ በትጋት መሥራት አለበት።መገናኛ ብዙኃን ሙስናን በማጋለጥ፣ የሲቪል ማኅበራትና ሌሎች ሕዝቡ ሌብነትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ግንዛቤ እንዲኖረው የማስተማር ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

ከተጠያቂነት ጎንለጎን ሌብነትን የሚፀየፍ ዜጋ ለመፍጠር መጠነ ሰፊ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል።በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤት፣ በየአካባቢያችን ትውልድ የምንቀርፅበትን መንገድ መለስ ብለን ማየትና ማስተካከል፣ ለእውነትና ለሕግ የሚቆም ዜጋ ለማፍራት የሚያስችል ሥራ መሥራት ከሁላችን ይጠበቃል።

# መን እንጠይቅልዎ?

**ንጉሤ ተስፋዬ**

በቦሌ ክፍለ ከተማ፣ የወረዳ 13 እና 14 የገርጂ አካባቢ ነዋሪዎች፣ በመብራት ኃይል አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ቅሬታ አቅርበዋል።ቅሬታ አቅራቢዎቹ “የመብራት ብልሽት ገጥሞን ለማስመዝገብ ስንሄድ መዝጋቢዋ ቀና በሆነ መንገድ አታስተናግደንም፤ ከቢል ንባብ እና ክፍያ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች ሲኖሩንም የሚያዳምጠን የለም፤ በቦታው ላይ የተመደቡ ባለሙያዎችም ኔትወርክ የለም የሚልና ሌሎች ሰበቦችን በመደርደር በሥራ ገበታቸው ላይ አይገኙም፤ አገልግሎት ከሚሰጡባቸው ቀናት ይልቅ አገልግሎት የማይሰጡባቸው ቀናት ይበልጣሉ፡፡” በማለት ቅሬታቸውን በምሬት ይገል ጻሉ።

ከቅሬታ አቅራቢዎቹ የመብራት ኃይል ደንበኞች መካከል አንዱ፣ “ግንቦት ወር 2014ዓ.ም 750ብር፣ በወሩ ሰኔ 2014ዓ.ም 3918.17ብር፣ በሚቀጥለው ሀምሌ ወር 2014 ዓ.ም ቆጣሪ ሳይነበብልኝ ቀርቶ፣ የነሃሴ ወር 2014ዓ.ም ተጨምሮ 2183ብር፣ የመስከረምን ወር ደግሞ ያልተጠቀምኩበትን 281 ኪሎ ዋት ጨምረው 2370 አስከፍለውኛል፡፡” በማለት ከቆጣሪ ንባብ ጋር በተያያዘ የገጠማቸውን ችግር ይገልጻሉ።ይህንኑ ቅሬታቸውን የሚያደምጥ አለመኖሩንና ጉዳዩ የሚመለከተውን ኃላፊ ስልክ ቁጥር ማግኘት አለመቻላቸውንም ጨምረው ነግረውናል።

የዘመን መጽሔት ዝግጅት ክፍልም ለተነሳው የህዝብ ቅሬታ ምላሽ ለማግኘት የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን ሥራ አስኪያጅ ለማግኘት ያደረገው ሙከራ ከብዙ ጥረት በኋላ ቢሳካለትም፣ በአካል ለመገናኘት ባስያዙት የቀጠሮ ቀንና ሰዓት ሊገኙለት ባለመቻላቸው ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በላይ ከፍ በማለት የሚመለከታቸውን የሥራ ኃላፊዎች አነጋግሯል።

በአዲስ አበባ ከተማ፣ የምስራቅ ዲስትሪክት መብራት ኃይል የደንበኞችና የሽያጭ አገልግሎት ስራ አስኪያጅ የቀረበውን የተገልጋይ ቅሬታ ተቀብለው አሰራራቸውን እንደሚፈትሹ ገልጸው ለተጠናከረ ምላሽ ወደ አዲስ አበባ ከተማ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት መርተውታል።

የጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ አቶ በቀለ ክፍሌ የሠራተኞች በሥራ ገበታቸው ላይ አለመገኘትንና፤ የአንባቢ በቸልተኝነትና በተለያዩ ምክንያቶች ቆጣሪ ያለማንበብ ችግሮች መኖራቸውን አምነው፤ ቀደም ሲልም ተቋማቸው ከአገልግሎት አሰጣጥ ችግር ጋር በተያያዘ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ባልተወጡ 121 የተቋሙ ሠራተኞች ላይ የዲሲፒሊን እርምጃ መውሰዱን አስታውሰዋል።ከዚሁ ጋር አያይዘውም ተቋሙ የደንበኛ አያያዝን አስመልክቶ ለሠራተኞቹ ሥልጠናዎችና ምክሮችን እየሰጠ እንደሚገኝም ጠቁመዋል።

ከቆጣሪ ንባብ ጋር ተያይዞ ለተነሳው ቅሬታ ሥራ አስኪያጁ ምላሽ ሲሰጡ፣ የሚፈጠረውን የክፍያ ጫና ለማቃለል የእፎይታ ጊዜ የሚሰጥ መሆኑን ገልጸው፣ በቀጣይ ግን ከአሰራር ጋር የተያያዘውን ችግር ትኩረት ሰጥተው እንደሚያዩትና ተገቢውን አገልግሎት የማይሰጡ ሠራተኞች ሲኖሩና ጥቆማ ሲደርስም እርምጃ እየወሰደ አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ማስተካከያ እንደሚደረግ ተናግረዋል።

በመጨረሻም፣ ከአገልግሎት አሠጣጥ ጋር ተያያዞ ደንበኞች ችግር ሲገጥማቸው ቅሬታቸውን የሚያደምጡ የበላይ ተቋማትና በየተቋማቱ የተቋቋሙ ቅሬታ ሰሚዎች መኖራቸውን በመጠቆም፣ ተገልጋዩ ቅሬታ ሲኖረው በስልክም ሆነ በአካል በመቅረብ ቅሬታውን ማቅረብና ምላሽ ማግኘት ይችላል ብለዋል፡፡


**በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እየታተመ የሚወጣ**

ኢፕድ

**ዋና አዘጋጅ፡-** ሳሙኤል ይትባረክ
**ፖ.ሣ.ቁ፡-** 30145
**ስልክ፡-** 011-1264207
Sammes.zellek@gmail.com
zemenpress@gmail.com
**ከፍተኛ አዘጋጆች፡-** ንጉሴ ተስፋዬ, ስሜነህ ደስታ

**አዘጋጆች፡-** ተስፋ ፈሩ, ዮርዳኖስ ፍቅሩ

**ማስታወቂያና ደንበኞች አገልግሎት**
ስልክ፡- 011 1 56 98 73
ፋክስ፡- 011 1 57 44 40


**ማከፋፈያ፡-**
ስልክ፡- 011 1 57 02 70

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ሰብለ ተስፋዬ

**ፎቶግራፍ፡-**
ፀሐይ ንጉሤ

# ዶክተር ያዕቆብ አርሳኖ ይናገራሉ፡-

- በረሃ ላይ በተሰራው አስዋን ግድብ ብቻ ከ10 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር በላይ ውሃ ይባክናል
- በሦስቱም የህዳሴ ግድብ ሙሌት ግብጽም ሆነች ሱዳን ተጠቅመውበታል እንጂ አልተጎዱም
- ግድቡን ማስተዳደርን በተመለከተም ኃላፊነቱ የግድቡ ባለቤት ሀገር የኢትዮጵያ እንጂ የሱዳንም ሆነ የግብጽ አለመሆኑ ግልጽ ነው.......



ተስፋ ፈሩ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና የዓባይ ውሃ ጉዳይ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ያዕቆብ አርሳኖ የዘመን መጽሔት የህዳር ወር እትም አብይ ርዕስ አምድ እንግዳችን ናቸው። ዘመን ከፕሮፌሰር ያዕቆብ ጋር ባደረገችው ቆይታ ወቅታዊውን የኮፕ 27 የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ፣ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን፣ በፕሪቶሪያ የተደረሰውን የሰላም ስምምነት እና ሌሎች ጉዳያችን የተመለከቱ ጥያቄዎች አቅርባ የተብራሩ ምላሾችን አግኝታለች። መልካም ቆይታ!

**ዘመን፡-** በቅርቡ በአፍሪካ ሀገራት የአየር ንብረት ለውጥ ላይ ትኩረቱን ያደረገው 27ኛው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ በግብፅ ሻርም አል ሼክ ተካሂዷል። መድረኩን እና የኢትዮጵያን ተሳትፎ እንዴት አገኙት?

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** የዚህ ኮፕ 27 የተባለውና በግብጽ የመዝናኛ ከተማ ሻርማ አል ሼክ የተካሄደው ጉባዔ ብዙ ትዝብትን ያዘለና ያሳየ ነው ማለት ይቻላል።ከአሁን በፊት በተደረጉት ጉባኤዎች አውሮፓና አሜሪካ በጠቅላላው ምዕራባውያን ሀብታም ሀገሮች የዓለም አየር ለውጥ ትልቁ ችግር መንስኤው እነሱ መሆናቸውን ሌሎች ሀገራት ነግረዋቸው እነሱም የተቀበሉ መስለው ነበር።ለዚህም ማካካሻ እንዲሆን ተገቢ የሆኑ የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች እጽዋትን ፣ ውሃን ፣ አሰፋፈርን እንደሁም የኢንዱስትሪ ተቋመትን እና የከርሰ ምድር ሀብትን በተሻለ እና በተቆጠበ ሁኔታ በመጠቀም በተለይም ለድርቅ ተጋላጭነት ያለቸው ሀገሮች ጉዳት እንዳይደርስባቸው አስፈላጊ የሆነው ድጋፍ ተሰጥቶ በሀገር ፣ በአህጉርና በዓለም ደረጃ የአየር ንብረት ሁኔታ እንዲስተካከል ስምምነት ላይ ተደርሶ ነበር።

የበለጸጉ ሀገሮች የለሙት የራሳቸውን ጥቅም ብቻ ባስቀደመ እና ሌሎች ሀገራት ላይ ሊደርስ የሚችልን ጉዳት ከግምት ባላስገባ መንገድ በመሆኑ፣ በተለይም ከኢንዱስትሪዎች ኬሚካል አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የሚመነጨው የአየርም ሆነ የሌላ ዝቃጭ የዓለም አየር ንብረትን እንደሚበክል በግድም ቢሆን አምነው የልማት አቅጣጫቸውን በተቻለ መጠን ለአየር ንብረት ተስማሚ በሆነ አካሄድ በመምራት በካይ አካሄዶችን ለመቀነስ ብሎም ለሦስተኛው ዓለም ሀገራት ለደረሰባቸው ጉዳት ማካካሻ እንዲሆን የተሻለ የልማት ድጋፍ ለማድረግ ቃል ገብተው ነበር፤ ይህን ቃላቸውን አልጠበቁም።በዘንድሮ ጉባኤ የተነሳው ዋናው ነገር ሀብታም ሀገሮች ቃላቸውን ባለመጠበቃቸው ጉዳቱ እየቀጠለ መሆኑን የሚገልጽ ነው።

በኢትዮጵያ በኩል የተገለጸው በጣም ጥሩ ነገር ይመስለኛል።ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን በመድረኩ ባደረጉት ንግግር ኢትዮጵያ ባለፉት ቅርብ አመታት በተለይም የአየር ንብረትን በሚያሻሻልና የኢትዮጵያንም ልማት እጅግ በጣም ተስፋ ባለው መሰረት ላይ የሚያኖር ስራ እየተሰራ መሆኑን፤ በመላ ሀገሪቱ ውስጥ ለአየር ንብረቱ ተስማሚ የሆኑ የውሃ ትነትን የሚቀንሱ እና የውሃ ግኝቱን ከፍ የሚያደርጉ ተክሎችን ኢትዮጵያ በሰፊው መትከሏን በዚህም ሂደት 25 ቢሊየን ተክሎች መተከላቸውን ፤ ይሄንኑ አብነትም ለጎረቤት ሀገሮች ኢትዮጵያ በትሩፋትነት እንዳስተላለፈች ገልጸዋል።ይሄም ከአሁን በፊት ሀገራት በየሪፖርቶቻቸውና መገናኛ ብዙሀኖቻቸው ኢትዮጵያን ካመሰገኑትና ካሞካሹት ባሻገር ይህን በመሰለ የዓለም መድረክ በአደባባይ ይሄ ውጤት መተረኩ፣ ለሌሎች አብነት በሚሆን መንገድ ማንሳቱ፣ ሀገሪቱ በዚህ አቅጣጫ እያደረገች ያለችው እንቅስቃሴ ፈርጠም ባለ መንገድ መገለጹ በጣም ጥሩ ነገር ይመስለኛል።

በተጨማሪም ኢትዮጵያ የራሷን የአረንጓዴ አሻራ ንቅናቄ እየቀጠለች እንደምትሄድ ተገልጿል።ከአካባቢ ጋር ተስማሚነት ያላቸውን የታዳሽ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶቿን በሚገባ እንደቀጠለች ይሄም ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአካባቢው አስተዋጽኦ ያለው ትልቅ ስጦታ እንደሚሆን ተነግሯል።ኢትዮጵያ የተያያዘችው ከአየር ንብረት ጋር የተስማማ ትክክለኛ የእድገት አቅጣጫ መሆኑ በሚገባ እንደተገለጸ ነው ያስተዋልኩት።በተለይ በታዳሽ ኃይል በኩል የኢትዮጵያ አስተዋጽኦ ከራሷ አልፎ ጎረቤት ሀገራትን የሚጠቅም መሆኑ በደንብ አጽዕኖት የተሰጠበት ነው።የኢትዮጵያ ጎረቤቶች በህዳሴ ግድብ እና ለወደፊትም በሚሰሩ የታዳሽ ኃይል ፕሮጀክቶች ላይ ትብብር እንዲያደርጉና በቀና መንፈስ እንዲመለከቱ፤ የጋራ ተጠቃሚነትን ከፍ የሚያደርግ መሆኑንን እንዲረዱ፤ ሁልጊዜ የኢትዮጵያን አካሄድ በክፉ እያዩ እንደ ባላንጣ ማየት እንደማይገባቸው መልዕክት የሚያስተላልፍ አይነት ንግግርና መግለጫ ስለሆነ በኢትዮጵያ በኩል የተተላለፈው አወንታዊ ነው ብዬ



አስባለው።

**ዘመን፡-ከአመታት በፊት አንድ የዘርፉ ባለሙያ —እኛ መሬት ሳራሹ ስንል ነው የከረምነው፤ ይህ ደግሞ መሬትን ካራሹ ጋር ማገናኘት ብቻ ሆነ።መሬትን ከውሃ ጋር ማገናኘት ቀዳሚ ቢሆንም በኢትዮጵያ ተረስቷል“ ብለው ነበር።እርስዎም እንደ ዘርፉ ባለሙያነትዎ የኢትዮጵያ የውሃ ፖሊሲ ከመሬት ጋር ያለውን ግንኙነት እንዴት ይገልጹታል?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** መሬት ላራሹ የፖለቲካ መፈክር ነው።መሬት የሚገባው ለሚያርስ ወገን ነው እንጂ ከተማ ላይ ቁጭ ብሎ በጭሰኛ ጉልበት ለሚጠቀም አይገባም የሚል ነበር።ይሄ መፈክር ውሎ አድሮ መሬት የህዝብና የመንግስት እንዲሆን አድርጎታል፤ ይሄ እንግዲህ ከአርባ አመት በላይ ሆኖታል።ውሃና መሬት ቢገናኙ የሚባለው ትክክለኛ ነገር ነው።የአየር ንብረትንም የሚመለከት፣ ሰው ከአካባቢው ጋር ታርቆ አካባቢውን በሚገባ በተገቢው መንገድ መጠቀም እንዲችል ማሰብ ያለበት መንገድ ነው።ውሃ መቼም ለእርሻ፣ ለእጽዋት፣ ለእንስሳት፣ ለሰው ልጅ እና ለአካባቢው አየር ንብረት ሁሉ ጠቃሚ እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለውም፤ ይሄ የተመሰከረለት ነገር ነው።

የውሃ አስተዳደር ፖሊሲ ውሃውን እንዴት አድርገን ነው ጥቅም ላይ የምናውለውን ይመለከታል።ለእርሻ፣ ለእፀዋት፣ ለእንስሳት እንዲሁም ለሰው ልጅ ጤና እና ለተስተካከለ ኑሮ ውሃን እንዴት እንጠቀምበት የሚለው በሚገባ መጤን እና ስራ ላይ መዋል ያለበት ነገር ነው።የኢትዮጵያ መንግስት በየጊዜው የውሃ ፖሊሲ እያወጣ መመሪያዎችንም እያዘጋጀ የውሃ ልማትም እያካሄደ በሚኒስቴር መስሪያቤት ደረጃ የውሃ ጉዳይ ሲሰራበት ቆይቷል።በእኔ አስተሳሰብ የውሃ ልማት ጉዳይ በኢትዮጵያ ውስጥ ገና በቂ የሆነ ትኩረት ያላገኘ መሆኑን አስተውያለሁ።ለምን በበርካታ አካባቢዎች ምንጮች እና ጨፌዎች እየደረቁ እንዲሁም ወንዞች የፍሰት መጠናቸውን እየቀነሱ ናቸው።ይህ የሆነበት ምክንያት የውሃው አጠቃቀምና ውሃን በመሬት ላይ የማስተዳደር ስራው በቂ ትኩረት ባለማግኘቱ ነው ማለት ይቻላል።ጨፌዎች የሚደርቁበት ምክንያት ገበሬዎች መሬት እየጠበባቸው ወይም ደግሞ በኢትዮጵያ በትክክለኛ መንገድ የመሬት አጠባበቅ ፖሊሲ ስላልወጣ፣ የመሬት አስተዳደሩ በትክክለኛ መንገድ ስላልተመራና ስራ ላይ ስላልዋለ እንዲሁም የተፈጥሮ አጠባበቅ ጠበቅ ባለ መንገድ ሳይሰራ ስለቆየ ገበሬውም አልሚውም ሁሉም መሬትን በዘፈቀደ ስለሚጠቀም መሬትና ውሃ ያላቸው ግንኙነት በአግባቡ ስለማይመዘን ነው።በዚህ ምክንያት ውሃ ባነሰባቸው አካባቢዎች ሰፊ የግብርና ስራዎች እየተሰሩ በአንጻሩ ውሃ በሚመነጭበት ማማ ላይ ውሃ መጣጭ ዛፍ እየተተከለ እና ሰፈራ እየተካሄደ ይገኛል።በቂ ውሃ በሌለበት ቦታ ከተሞች እየተቆረቆሩና እየተስፋፉ በሄዱ መጠን ውሀ ላይ ያለው ሸሚያ ያይላል።በመሆኑም ውሃን ለተገቢው ልማት ማዋል መቻል በጣም እየተወዘገበ ከልማቱ ጋር አብሮ ሳይስተጋበር እየቀረ የውሃ እጥረት በየቦታው ሲያጋጥም ይታያል።በአንዳንድ አካባቢዎች የከፋ የውሃ እጥረትም ብክለትም ይስተወዋላል።

የጉድጓድ ውሃም (በባለሙያ ብቻ ሳይሆን በተመልካች አይን ጭምር) ከድሮው ወደታች እየራቀ፤ ከጉድጓድ የሚገኝ ውሃ ከተገኘ በኋላ ቶሎ እያለቀና እየነጠፈ በዚህም የተነሳ የአዳዲስ ጉድጓዶች ቁፋሮ ዋጋ በጣም እየጨመረ ውሃ የማግኛ መንገድ ሁሉ ከበፊቱ እየቀነሰ እንደመጣ የሚያሳይ ነው።ስለዚህ የውሃ አጠቃቀም ከውሃ አስተዳደር ጋር አብሮ ተስተጋብሮ ካልሄደ፤ ያለንን ውሃ በሚገባ ለመጠቀም ካልተቻለና የውሃ አጠቃቀም በዘፈቀደ ሆኖ ከእርሻ ልማት ጋር፤ በገጠርም ሆነ በከተማ ከሰዎች አሰፋፈርና ከከተማ ልማትና ስፋት ጋር  አብሮ በሚገባ ካልተያያዘ የውሃ እጥረት ማጋጠሙ የታወቀ ነው።ይህ ሲባል ደግሞ በየአመቱ ከሰማይ የሚወርድልን ውሃ እያነሰ መጣ ማለት አይደለም።የሜትሮሎጂ ሰዎች እንደሚናገሩት የዝናብ መጠን እየቀነሰ አይደልም።ነገር ግን የወረደው ውሃ በወንዝነት፣ በጨፌነትና በምንጭነት በሚገባ አስተዳደር ውስጥ ካልገባ የውሃ እጥረት ሊያጋጥም እንደሚችልና አሁንም በየቦታው እያጋጠመ መሆኑ በጣም ግልጽ ነው።ውሃ በመኖሩ ብቻ የውሃ ጥቅም ይገኛል ማለት አይደለም።በውሃ ለመጠቀም ከፖሊሲ አንስቶ የአስተዳደር ሁኔታና ዕለት ከዕለት የሚደረገውን የአካባቢ ጥበቃ አስተጋብሮ ማየት ያስፈልጋል።

**ዘመን፡- የግብጹ ፕሬዚደንት በቅርቡ በአረብ ሊግ ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር ኢትዮጵያ አስገዳጅ ስምምነት ለመፈረም ተአማኒነቷን እንድታሳይ ጠይቀዋል።ግብጾች ደጋግመው የሚያነሱት “አስገዳጅ ስምምነት“ ለሁለቱ ሀገራት የሚኖረው ትርጉም ምንድን ነው?**


**ዶክተር ያዕቆብ፡-** የግብጽ ፖለቲከኞች ፕሬዚደንቱንና ሌሎች የፖለቲካ እና የአካዳሚክ ሰዎች ተጠቃለው ኢትዮጵያ ከግብጽ ጋር አንዳንዴም ከግብጽና ሱዳን ጋር አስገዳጅ ስምምነት ትፈርም እያሉ የሚያነሱት ነገር አለ።ይሄም በአረብ ሊግ ጉባዔ ላይ ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል በነበሩት ድርድሮች ላይም ግብጽ ኢትዮጵያ በውሃ አጠቃቀሟ አስገዳጅ ስምምነት ታድርግ ስትል ቆይታለች።በህዳሴ ግድብ ድርድር ጊዜ ትልቁ ማፋረሻ የነበረው ይሄው ግብጽ ይዛው የደረቀችበት አስገዳጅ ስምምነት የሚል ሀሳብ ነው።ግብጾች አስገዳጅ ስምምነት የሚሉትን ጉዳይ በደምብ ብናጤን አንደኛ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የሚሞላው ግብጽ በምትፈልገው የጊዜ ቀመር እንዲሆን የሚጠይቅ ነው።ሁለተኛው የህዳሴ ግድብ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተሰራ ያለ ቢሆንም

ትልቅ ግድብ ስለሆነ የጋራ ጽህፈት ቤታችንን አዲስ አበባ ወይም ግድቡ የሚሰራበት ቦታ ጉባ አድርገን በጋራ እናስተዳደረው የሚል ጥያቄ ነው።ከዚህ ሁሉ ደግሞ የከፋው የኢትዮጵያ መንግስት ከህዳሴ ግድብ ከፍ ብሎ የአባይን ውሃ ማልማት በሚፈልግበት ጊዜ አስቀድሞ ከእኛ ጋር ስምምነት ያድርግ ወይም ደግሞ ያስፈቅድ የሚል ሀሳብ የያዘ ነው።በእነዚህ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ኢትዮጵያ አስገዳጅ የሚሉትን ስምምነት እንድትፈርም ነው ግብፆች የሚፈልጉት።

የግድቡ አሞላል በግብጽ፣ በሱዳን እና በኢትዮጵያ በታወቁ የዘርፉ ሳይንቲስቶች አንደላይ በመሆን ባጠኑት ቀመር መሰረት በሰባት አመታት እንዲሞላ ስምምነት ተደርጓል።ይሄ የህዳሴ ግድብ አሞላል የጊዜ ቀመር ሳይንሳዊ የሆነና የዘርፉ አዋቂዎች መርምረው ተነጋግረው የተስማሙበት ነው።ኢትዮጵያ ግድቡን እየሞላች ያለችው በዚህ መንገድ ነው።ግብጽ በምትፈልገው ረጅም አመታት በሚወስድ አሞላል ላይ ኢትዮጵያ እንደማትስማማ ተነግሯቸዋል።ኢትዮጵያ ጥቅሟ በማይጎድልበትና ሱዳንና ግብጽ በውሃ እጥረት በማይቸገሩበት መንገድ ታስቦ የተነደፈና እየተሰራ ያለ ግድብ ነው።ኢትዮጵያ ግድቡን በተመለከተ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለግብጽና ሱዳን ለመስጠት ፈቃደኛ ነች።ይሄ የመልካም ጉርብትና አንዱ መገለጫ ነው፡፡ ግድቡን ማስተዳደርን በተመለከተም ኃላፊነቱ የግድቡ ባለቤት ሀገር እንጂ የሱዳንም ሆነ የግብጽ አለመሆኑ ግልጽ ነው።ኢትዮጵያ በራሷ መሬት ላይ በአንጡራ ሀብቷ የገነባችውን ግድብ ኢትዮጵያ ውስጥ መጥተው እንዲያስተዳድሩ አልፈቀደችላቸውም።ያንን ያልተፈቀደላቸውን እና ተገቢ ያልሆነ ጥያቄ በአስገዳጅነት ኢትዮጵያ ትፈርምልን ነው የሚሉት፤ ይሄ የማይቻል ነገር ነው።የበለጠ የከፋው ኢትዮጵያ ወደፊት መቶም ሆነ ሺ ግድብ በምትሰራበት ጊዜ አስቀድማ ከግብጽ ፈቃድ ትውሰድ የሚለው ነው።ግብጽ እኔ እስካልተስማማሁ ድረስ ኢትዮጵያ የውሃ ልማት ማካሄድ አትችልም የሚል ሀሳብ አላት።ይሄን ኢትዮጵያ በፊርማ እንድታጸድቅላት ትፈልጋለች።ይህ ማለት ኢትዮጵያ ወንዞቿን ከማልማት ተቆጥባ እጅ እግሯን አጣጥፋ በመቀመጥ የግብጽን ይሁንታ ትጠብቅ ማለት ነው።ግብጽ እነዚህን አስገዳጅ ስምምነት ብላ የምታቀርባቸውን ሀሳቦች በአረብ ሊግ፣ በአፍሪካ ህብረት እና ኢትዮጵያ፣ ግብጽና ሱዳን በሚገናኙበት መድረክ ስትናገር ነው የምትውለው።በኢትዮጵያ በኩል ግን ተቀባይነት እንደሌላቸው ተነግሯታል።

**ዘመን፡- የአባይ ግድብ እየተጠናቀቀ መምጣቱ በአባይ ወንዝ ላይ ለሚነሳው የፍትሃዊ አጠቃቀም ጥያቄ ይበልጥ ጉልበት ይሰጠዋል ወይስ የግብጽን የቅኝ ግዛት ስምምነት መሰረት የሚያደርግ የውሃ ድርሻዬ ይከበርልኝ ጥያቄን ያከረዋል ?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** አሁን ግድቡ



የበለጠ የከፋው ኢትዮጵያ ወደፊት መቶም ሆነ ሺ ግድብ በምትሰራበት ጊዜ አስቀድማ ከግብጽ ፈቃድ ትውሰድ የሚለው ነው

ለሦስት ዙር ተሞልቷል።በሦስቱም ሙሌት ግብጽም ሱዳንም ተጠቅመውበታል እንጂ አልተጎዱበትም።እንዳልተጎዱ ደግሞ በራሳቸውም አንደበት ተገልጿል።ሱዳን ከሞላ ጎደል ከአመታዊ የጎርፍ አደጋ ስጋት ድናለች።የሱዳንን መንደርና ከተማ የሚያጥለቀልቀው ውሃ በሚያመጠው ደለል ከመሞላትም ተርፋለች (ቀንሶላታል)። ውሃም ደግሞ በተመጠነ መንገድ እየሄደላት ስለሆነ የደረሰባት ጉዳት የለም።ግብጾችም ቢሆኑ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሙሌት እኛን አይጎዳንም አስቀድመን ተዘጋጅተንበታል ብለዋል።ግብጽ ተጎዳች ማለት አስዋን ግድብ ላይ ውሃ አነሰ ማለት ነው።አስዋን ግድብ ላይ ውሃ የሚቀንስበት ምንም ምክንያት የለም።ኢትዮጵያ ውሃ የምትሞላው ዝናብ በብዛት በሚዘንብበትና ጎርፍ በብዛት በሚገባበት የክረምት ወቅት እንጂ አመቱን ሙሉ ስላልሆነ ግብጽም ሆነች ሱዳን አይጎዱበትም።ከአሁን በፊት እነሱ ለመጠቀም የሚያስቡበት ኢትዮጵያና ሌሎች ሀገሮች ውሃ እንዳይጠቀሙ የሚያግድና የሚያቅብ መንገድ እንደማይሰራ በተለይም አሁን ኢትዮጵያ በህዳሴ ግድብ አንጻር ያደረገችው ነገር ትምህርት ሰጪ ስለሆነ በአባይ ወንዝ ላይ ለሚነሳው የፍትሃዊ አጠቃቀም ጥያቄ ተግባረዊ ምላሽ የሚሰጥ ነው።ወደፊት በሚሰሩት ግድቦችም ከዚህ የተለየ ነገር አይኖርም።

ዘምን፡-የግብጽ ፖለቲከኞች በሚዲያዎቻቸው የባህር ውሃን ማጣራትን ጨምሮ ለጉድጓድ ቁፋሮ ሰፊ ትኩረት መስጠታቸውን ሲገልጹ እና ዜጎቻቸው ውሃ እንዳያባክኑ ተደጋጋሚ ማሳሰቢያዎችን ሲያወጡ ይታያል።ግብጽ በዚህ ደረጃ የውሃ እጥረት ስጋት የደቀነባት ሀገር ነች ?

ዶክተር ያዕቆብ፡- ውሃ እንቆጥባለን፣ አዳዲስ ውሃ የማጣራትና የማበራከት ዘዴ እንከተላለን ሲሉ እኔ ራሴ ስሰማ ከሰላሳ አመታት በላይ ሆኖኛል።በየጊዜው ነው እንዲህ የሚሉት።ከውሃ አመንጪ ሀገሮች ከሚመጣ ውሃ አጠቃቀም ጋር አያይዘው መልካም አሰራርና መግባባትን ይፈጥራል ብለው የምር ቢያደርጉት ጥሩ ነበር።ግብጾች በዕቅዳቸው፣ በየጉባኤውና በየአደባባዩ የሚገልጹት ነገር ከሚሰሩት ተቃራኒውን ነው።እርግጥ ውሃ ከባህር አጣርተው ከጨው ለይተው መጠቀም የሚችሉበት ቴክኖሎጂ አለ።ይጎድለናል የሚሉትን ውሃ በዚህ ሊያሟሉ ይችሉ ነበር።ነገር ግን እስካሁን በበቂ እንዳላደረጉት የተረጋገጠ ነው።ጉድጓዶችን እንቆፍራለን የሚሉትንም ቢያደርጉት ጥሩ ነው።በመሰረቱ ከጉድጓድ ውሃ የሚገኘው ከኢትዮጵያ እና ከሌሎቹ አመንጪ ሀገሮች የሄደው ውሃ ወደመሬት ሰርጎ ከመሬት የሚያወጡት ውሃ ስለሆነ መልካም ነው።በብዙ ሺ ሜትሪክ ኪብ ውሃ ከግብጽ ከርሰ ምድር ስር እንደሚገኝም ይታወቃል።ይህን ሁሉ በአማራጭ ሊያለሙት ይችላሉ።

ከሁሉም በላይ የውሃ ብክነትን እንቀንሳለን የሚሉት ውሸት ነው።ግብጽ ውስጥ ውሃ ያለቅጥ ይባክናል።በርሃ ላይ በተሰራው አስዋን ግድብ ብቻ ከ10 ቢሊየን ኪዩቢክ ሜትር በላይ ውሃ ይባክናል።ሁለተኛ ግብጽ ውስጥ የሚሰራበት የውሃ አጠቃቀም የጎርፍ መስኖ ጥንታዊ የሆነ የመስኖ አሰራር ነው።ውሃውን በቦይ እየወሰዱ ከትልቁ ቦይ በትንሹ ቦይ እያደረጉ ከዚያ ደግሞ በቀጭኑ ቦይ እያደረጉ እጽዋትና አትክልት ውስጥ ውሃ በጎርፍ ያሰራጫሉ።ይሄ በርሃ ውስጥ የሚሰራውን እርሻ ቢያለማም በእርሻ ቦታ ላይ የሚፈሰውና የሚንጣለለው ውሃ እጅግ በከፋ መንገድ ለትነት የተጋለጠ ነው።እዚያም ላይ ከ10 ቢሊየን ኪዩቢክ ሜትር በላይ ውሃ ይባክናል።ይሄ ብቻ አይደለም አሁን ግብጾች የናይልን ውሃ ከተፈጥሮ ተፋሰሱ ውጭ በብዙ

አቅጣጫ እየወሰዱ እያባከኑት ነው።አንደኛ በርሃ ውስጥ በሰሩት ቶሽካ በሚባለው ትልቅ የእርሻ ልማት ከአምስት ቢሊየን ኪዩቢክ ሜትር በላይ ያለ ውሃ ወስደው ያባክናሉ።ይሄ አንድ ትልቅ የማባከኛ መንገድ ነው።የናይልን ውሃ እንደገና በቀይ ባህር ከታች በመሬት ስር በቱቦ ወስደው በሲናበርሃ ላይ ሻርም አል ሼክ የሚባለውን አሁን የአየር ንብረት ለውጥ ጉባዔው የተካሄደበትን ከተማ አልምተውበታል።በከተማው የሚገኘው የውሃ አገልግሎት የእርሻን ስራና ሌሎች የመንደር ልማቶችን ጨምሮ ሙሉ ለሙሉ ከናይል ወንዝ የሚገኝ ነው።ይሄም ትልቅ ብክነት ነው ማለት ይቻላል።አሁን ፕሬዚደንት አልሲሲ በቀይ ባህር ጫፍ ላይ በስዊዝ ካናል አጠገብ በጣም ትልቅ ዘመናዊ ከተማ እየገነቡ ነው።ይሄ በዓለም ላይ አዲስ ፕሮጀክት ተብሎ በእነሱ በኩል ትልቅ አድናቆት የሚቸሩት ነው።በርሃ ላይ ያንን ህንጻና መንገድ ለመገንባት የናይልን ውሃ ከተፈጥሯዊ ተፋሰሱ ውጪ ቆልምመው ወስደው ነው የሚጠቀሙበት።ስለዚህ ብዙ አይነት የውሃ ማባከን ስራዎች እያካሄዱ ስለሆነ ውሃ እየቀጠብን ነው ወይም ልንቆጥብ ነው የሚሉት ነገር ትክክለኛ አይደለም።ሌሎች ውሃ እየከለከሉን እኛ ግን ውሃ ቆጣቢ ነን ብለው ለዓለም ለማሳየት በአብዛኛው ለፕሮፖጋንዳ እና ሌሎችን ለመወንጀል የሚጠቀሙበት እንጂ ከባህር ውሃ ጨው ለይተው ለመጠቀም ከሚያደርጉት ሙከራ ውጪ የተቀሩት ጉዳዮች ውሃ የማይቋጥሩ ናቸው።

**ዘመን፡- ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ በአባይ ግድብ ድርድር ስታራምደው በነበረው ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ በሚል መርህ ውስጣዊ ችግሯን በአፍሪካ ህብረት ጥላ ስር መፍታት መቻሏ ለተቀሩት የአፍሪካ ሀገራት የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንድን ነው?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** የአፍሪካ ችግር በአፍሪካ ይፈታል የተባለው በኢትዮጵያ በኩል በደምብ በትክክለኛው መንግድ የተቀየሰ ይመስለኛል።የህዳሴ ግድብ ጉዳይ በግብጽ አማካኝነት እንዲሁም ምዕራባዊያን በደገፉት አቅጣጫ ባልተገባ መልኩ ወደ ጸጥታው ምክር ቤት ተወስዶ ሁለት ጊዜ ክርክር ተካሂዶበታል።በሁለቱም ጊዜ የውሃ ጉዳይ የልማት ጉዳይ እንጂ የደህንነት ጉዳይ አይደለም በሚል በኢትዮጵያ በኩል በቀረበው ጠንካራ ክርክር ከዚያ ተመልሷል።ከዚያስ ምን ይደረግ ሲባል እንደችግር ከታየ በአፍሪካ ህብረት በአፍሪካ መድረክ ይታይና መፍትሄ ይፈለግለት ተብሎ በፈረንጆች አቆጣጠር ከ2020 ጀምሮ በአፍሪካ ህብረት እየታየ ነው ያለው።ነገር ግን ግብጽና ሱዳን የያዙት ጉዳይ ውሃ የማይቋጥር ስለሆነና

**በግድቡ ላይ አልፎ አልፎ የተነሱና የተካሄዱ ሳንካዎቹም እየተቀረፉ ግድቡ አሁን በጥሩ መንገድ ላይ ነው ያለው**

የአፍሪካ ህብረት ይህን በደምብ ስለሚረዳ ግብጾች በአፍሪከ ህብረት ጥላ ስር በሚመቻቸው መድረክ ላይ ለቀጠል አፍረው እስካሁን ድረስ እግራቸውን እየጎተቱ ያሉ ይመስለኛል።የአፍሪካ ህብረት ሊቃነ መናብርት ከአንድም ሁለት ሦስቴ ጉዳዩን ተከታትለዋል፣ ግብጾች ግን ወደ ኋላ እየተንሸራተቱ ከመድረኩ እየሸሹ ነው የሚገኙት።የአፍሪካ ጉዳይ በአፍሪካውያን ይፈታ የሚለውን መርህ ኢትዮጵያ በሙሉ ልቦና የተቀበለችውና የህዳሴ ግድብ ጉዳይ ከጸጥታው ምክር ቤት ወደ አፍሪካ ህብረት እንዲመለስ ያደረገችበት መንገድ ነው።

አሁን በሰሜን ኢትዮጵያ ባለው ግጭትም የኢትዮጵያ መንግስትና የህወሃት ጉዳይ ከጦርነት ይልቅ በአፍሪካ ህብረት አመቻችነት እንዲታይ ኢትዮጵያ ፈቃደኛ በመሆኗ ህብረቱ ሁለቱንም ወገኖች ስምምነት ላይ እንዲደርሱ ማድረጉን አስተውለናል።ስለዚህ በኢትዮጵያ በኩል የአፍሪካ ጉዳይ በአፍሪካ መድረክ እንዲቃና የህዳሴ ግድብ ወይም የድንበሮች ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የአንድ ሀገር የውስጥ ግጭት ጉዳይም በህብረቱ ስር ቢታይ ዘላቂ ሰላም ይገኛል የሚል እምነት በሚገባ አጽንታ የያዘች ሀገር መሆኗን ነው የሚያሳየው።ይሄንን ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮችም እንደ አብነት ቢወስዱት አንደኛ አላስፈላጊ ካልሆነ ግጭትና ጉዳት ይተርፋሉ።ሁለተኛ የአፍሪካን ጉዳይ እያባባሱ በሚነሱ ቁስሎች ላይ ዘይት እየጨመሩ ጉዳዮችን በማይገባ ደረጃ እያከረሩ የራሳቸውን ዘላቂ ጥቅም በመፈለግ የሚማስኑትን አውሮፓዊያን እና ሌሎች የውጭ ኃይሎች መከልከያና ማገጃ ለእነሱ አመቺ አለመሆንን የሚያረጋግጥ መንገድ ነው።

ኢትዮጵያ ይሄንን ከአንድም ሁለት ጊዜ አሳይታለች።ከአሁን ቀደምም የአፍሪካን ጉዳይ በሽምግልና እና በማመቻቸት ሰርታ ታውቃለች።በአልጄሪያና በሞሮኮ መካከል የነበረውን ግጭት እንዲሁም በናይጄሪያ ፌዴራል መንግስትና በቢያፍራ አማጽያን መካከል የነበረውን እጅግ የከፋ ግጭት በሽምግልና እንዲያልቅ እንዳመቻቸች ይታወቃል።አሁን ደግሞ በራሷ ጉዳይ ሌሎች የአፍሪካ ሀገራትና የአፍሪካ ህብረት ጭምር ገብተው ሲያስማሙ መድረኩን መጠቀሙ ተገቢ መሆኑን ኢትዮጵያ አሳይታለች፤ በራሷም ሆነ በሌሎች ጉዳይ። ስለዚህ ይሄ በአፍሪካ መለመድ ያለበት ነገር ነው።ሌሎች ሀገሮችም ሁኔታቸውን ለማስተካከልና ለማሻሻል፤ ሰላም ለማስፈን ፤ ልማትን ወደፊት ለማራመድ ፤ ነጻነታቸውና ሉዋላዊነታቸው እንዲጸና እንዲሁም ሀገሮች በመካከላቸው ያለውንም ችግር ከጦርነት ውጭ በአፍሪካ ህብረት መድረክ መፍታት እንደሚችሉ ኢትዮጵያ በሚገባ ያሳየች ሀገር ናት።

**ዘመን፡- ኃያላን ሀገራት እና የአህጉራት ተቋማት በአባይ ግድብ ድርድርም ሆነ በቅርብ በተካሄደው የሰላም ውይይት በታዛቢነት መገኘት የሚፈልጉት ለምንድን ነው ?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** ይሄ ጥሩ ጥያቄ ነው።ይህንን ለመገመት እንደሚቻለው እነሱ በተቻለ መጠን በተለይም በአፍሪካና በሌሎች ባልለሙት ሀገሮች ጥቅማቸው እንዲከበር ግጭት ባለበት ቦታ ሁሉ ከአንዱ ወይም ከሌላው ወገን ጋር የማበር ባህሪ አላቸው። እስካሁን ባለው ልምድ እንደምናስተውለው እነሱ የሚፈልጉት በድርድርም ሆነ በውይይት ሂደት የእነሱ ጥቅም መስመር እንዲይዝላቸው ለማመቻቸት ነው መገኘት የሚፈልጉት።የሚገኙት ፍታዊ በመሆን ነገሮች እንዳይበላሹ ለመከላከልና ሀገሮች ሰላማቸውን መልሰው እንዲያገኙ ለማድረግ ቅን ፍላጎትን ይዘው የሚሰሩ አይመስለኝም።ችግር በሚኖርበት ጊዜ እኛ ምን ትርፍ እናገኛለን፤ እኛን የሚያግዝ ነገርን እንዴት አድርገን እናመቻች ወይም እኛን በሚያግዝ መንገድ የተባለው ግጭት እንዴት መስመር ይያዝ ብለው በስሌት የሚያደርጉት ነገር ነው።ስለዚህ ለፍትህ፣ ለሌሎች ጥቅምና ለዓለም ሰላም በመቆም የሚያደርጉት ነገር እንዳልሆነ እስካሁን ድረስ ባለን ልምድና በተለያየ ሁኔታ በወሰድነው ግምገማ እንረዳለን።

**ዘመን፡- የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች አንድ በር ሲዘጋባቸው ሌላውን ማንኳኳታቸው አይቀሬ ነውና ቀጣይ አጀንዳቸው ሲያደርጉት ከአሁን እንዳንድ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ የጀመሩበት የአባይ ግድብ ጉዳይ ዲፕሎማሲ ከዚህ በኋላ እንዴት ባለ አቅጣጫ መመራት አለበት ይላሉ ?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** ዛሬ ላይ ግድቡ 86 በመቶ ተጠናቋል።ሦስት ሙሌት ተካሂዶ ኤሌክትሪክ

ማመንጨት ጀምሯል።ሌሎች ማመንጫዎችም እየተተከሉ ነው ያሉት።ስለዚህ ግድቡ ወደ መጠናቀቅ እየደረሰ ነው።ይሄን ግድብ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ከሊቅ እስከደቂቅ በመሳተፍ ነው እየገነባ የሚገኘው።ስለሆነም ኢትዮጵያ ግድቡን ለማጠናቀቅ ከፍተኛ ቁርጠኝነት አሳይታለች። በግድቡ ላይ አልፎ አልፎ የተነሱና የተካሄዱ ሳንካዎችም እየተቀረፉ ግድቡ አሁን በጥሩ መንገድ ላይ ነው ያለው። አሰራሩ ለኢትዮጵያ ጠቃሚ ለሌሎች ደግሞ ጎጂ አለመሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ ይሄንኑ በመግለጽ በዛ አቅጣጫ መቀጠል ትልቅ የዲፕሎማሲ መሳሪያ ይመስለኛል።ስለዚህ አዲስ ዲፕሎማሲ፣ አዲስ አይነት መንገድ፣ አዲስ አይነት አገላለጽ እና አዲስ አይነት ብልሃት የሚያስፈልግ አይመስለኝም።ይሄንኑ በሚገባ አጽንቶ በተግባር እያሳዩ መሄድ ያስፈልጋል።

ምናልባት እንደጉድለት ሊነሳ የሚችለውና ኢትዮጵያ ማሻሻል የሚገባት ነገር የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት በማድረግ የምትሰራውን ስራ በሚገባ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሳትታክት መግለጽ አለባት።በዲፕሎማቶቿ ፣ በየጊዜው ወደተለያዩ ሀገራት በሚላኩ ወኪሎቿ፣ በምሁራኖቿ ፣ በጋዜጠኞቿ እንዲሁም ደግሞ በተለያዩ መድረኮች አቋሟን ህዝቧና ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እንዲያውቅላት የማድረግ፣ የማስተዋወቅና የማስረዳት ስራ በሰፊው መስራት ይኖርባታል።

**ዘመን፡- በዓባይ ወንዝ ላይ ግብጾች የሚነዟቸውን የተዛቡ ትርክቶች ለማረም በኢትዮጵያ በኩል ምን መሰራት አለበት ?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** ግብጾች በአባይ ውሃ ላይ ብዙ የተዛቡ ትርክቶችን እንደሚያራምዱ ይታወቃል።አብዛኛው ስራቸው ደግሞ የተዛባና ትክክለኛ ባልሆነ መረጃ ላይ በመመርኮዝ ትክክለኛ ያልሆነ እውቀት ለመፍጠር በማሰብ የሚፈጸም መሆኑ የታወቀ ነው።ኢትዮጵያ ግብጾች የሚሰሩትን መልካም ያልሆነ ነገር ተሻምታ እንደዚሁ ተመሳሳይ ነገር መስራት ያለባት አይመስለኝም።በኢትዮጵያ በኩል እየተሰራ ያለው ግብጽ በሰፊው ከምትሰራው የተሻለ ተቀባይነት ያለው ነገር ነው።ኢትዮጵያ ስለ ድንበር ተሻጋሪ ውሃዎቿ፣ ከግብጽና ከሱዳን ጋር ስላላት ትብብር እና ትብብሩን እንዴት አድርጋ እንደምታኅለብት ለአሁኑም ለሚመጣውም ትውልድ ማሳየትና ማስተማር አለባት፤ ይሄ በጣም ተገቢ ነገር በመሆኑ በዚህ መበርታት በጣም አስፈላጊ ነው።ነገር ግን ግብጽ የሄደችበትን መልካም ያልሆነ እርምጃ ሁሉ ኢትዮጵያ እግር በእግር እየተከተለች በመቃወም ጊዜዋን ማጥፋት ያለባት አይመስለኝም።ኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ የምትሰራው ጥሩ ነገር ይመስለኛል።ይሄ በትምህርት፣ በተግባቦት መረብና እና በሌሎች መንገዶች አንጻር በበቂ ስላልተገለጸ እዛ ላይ ማተኮር አስፈላጊ ነው።ዋናው ጉዳይ በኢትዮጵያ በኩል የውሃ ሀብቱን በተመለከተ በመደበኛ ትምህርት፣ በምርምር፣ በስልጠና እና በቀጥታ ልማት ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል።

**ዘመን፡- ኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት አመታት ጦርነት ውስጥ በመቆየቷ በብዙ ተጎድታለች።አሁን ደግሞ ሰላም ወርዷል።ቀጣዮቹ አመታት ለኢትዮጵያ እንዴት ያሉ ይሆናሉ ብለው ያስባሉ?**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** ኢትዮጵያ በየዘመናቱ ችግር አጋጥሟት ያውቃል።እነዚያን ችግሮች እንደየሁኔታው በስቃይም በመስዋትነትም በብልሃትም ፈትታ አሳይታለች።ከአድዋ ጀምሮ የጣሊያን ፋሺስት ወረራ አምስቱ አመታት ፣ የሶማሌና የባድሜ ጦርነቶችና ሌሎችም በየመሃሉ የተነሱ ግጭቶችና የርስበርስ ጦርነቶች ሁሉ አሉ።ነገር ግን ኢትዮጵያ ከአሁን በፊት በየጊዜው ችግሯን የፈታችው በአንድነቷ ላይ ተመስርታ ነው።ለወደፊትም ችግሯን ልትፈታ የምትችለው በአንድነቷ ላይ ቆማ ነው።ምክንያቱም ኢትዮጵያ መንግስትነቷ የቆየ ነው። የኢትዮጵያ መንግስትነት የኢትዮጵያን ህብረተሰብ በአንድ መቆምን፤ በአንድ ተስፋ መንቀሳቀስን እና ጠላት በመጣ ቁጥር በአንድ ልቦና ቆሞ በአርበኝነት መመከትን እንዲሁም የውስጥ ችግሮችን በህዝቧ አንድነትና ትብብር መፍታትን ነው ያሳየው።

**እስካሁን የኢትዮጵያ ህልውና ተጠብቆ የቆየው በአንድነቷ ነው። አንድነቷ ካለ ሰላም ይሰፍናል፤ ከፍ ያለ የወደፊት ብልጽግና ይገኛል፤ ጠላቶቿንም ማሸነፍ ትችላለች**

አሁንም ቢሆን ችግሮቿ የሚፈቱት የኢትዮጵያን አንድነት በጠበቀ መንገድ መሆን አለበት።ወደፊትም ቢሆን በአንድነትና በአንድ መንፈስ፤ በአንድ መድረክና በአንድ ሀገራዊነት እንዲሁም በእኩል የዜግነት መብት ላይ ቆማ ማናቸውንም ችግሮቿን ልትፈታ ትችላለች።ኢትዮጵያውያን የሀገራቸውን አንድነት በጠበቀ መልኩ ሲንቀሳቀሱ ነው የኢትዮጵያ ልዕልና፣ ነጻነት፣ አንድነትና ሰላም የሚገኘው፤ ይሄ በጥቅሉ ነው።ኢትዮጵያን በተሸረፈ መንገድ ከተመለከትናት ፤ በመንደር ከመዘንናት፤ ኢትዮጵያን በሃይማኖት ብቻ ከመዘንናት፤ ኢትዮጵያን በቋንቋ ብቻ ከመዘንናት፤ ኢትዮጵያን በደጋ ወይም በቆላ ብቻ ከመዘንናት፤ ኢትዮጵያን በዚህ ባህል ወይም በዛ ባህል አንጻር ብቻ ከመዘንካት በተሸራረፈ መንገድ ችግሯ ሊፈታ አይችልም።

የኢትዮጵያአንድነትማለትየኢትዮጵያውያንን መብት የሚያጎድል ሳይሆን የሚያሟላ ነው መሆን ያለበት። እስካሁን የኢትዮጵያ ህልውና ተጠብቆ የቆየው በአንድነቷ ነው።አንድነቷ ካለ ሰላም ይሰፍናል፤ ከፍ ያለ የወደፊት ብልጽግና ይገኛል፤ ጠላቶቿንም ማሸነፍ ትችላለች። አንድነቱ ከሌለ ግን እዚህም እዚያም ጦርነት፣ መጨፋጨፍ፣ መናናቅ፤ መነነታተልና በሆነ ባልሆነ ግጭት ወስጥ መግባት ይከተላል።ስለዚህ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ እና ከታሪክ አንጻር ስለወደፊቱ በእኔ በኩል የሚታየኝ የህብረተሰቡ ዕኩልነት፤ በፍትህ መተዳደር፤ በልማት ጎዳና መጓዝ፤ የሚሰራ የሚተጋ መንግስት ማበጀት እና የዜጎች ክብር መረጋገጥን ጨምሮ ነባራዊ ልዩነቶችን በሚገባ ያጤነ ለሁሉም የሚሆን የአንድነት ንጣፍ ካለ ለሁሉም ነገር መፍትሄ የሚገኝ ይመስለኛል።

ለአንዳንድ ሰው አንድነት ጨቋኝነትና ጨፍላቂነት ሊመስለው ይችላል።አንድነት ጨፍላቂና ጨቋኝ መሆን የለበትም።አንድነት የሚያስተሳስር፤ የሚያስተባብርና በተቻለ መጠን የሚያስተጋግዝ ሆኖ ማህበረሰቡ በፍትህ አንገቱን ቀና አድርጎ ደረቱን ገልብጦ በየቦታው በዜግነቱ ተከብሮ ንብረቱን፣ ነጻነቱን እና ክብሩን ጠብቆ ያልተጨፈለቀ መብት ኖሮት ሲኖር ነው ኢትዮጵያ የምትጸናውና የምትለማው።ነገር ግን አንድነት በሌለበት መድረክ፣ አንድነት ባልሰፈነበት መንፈስ፣ አንድነት ዋና የሀገር መቆሚያ ባልሆነበት ሁኔታ እንዲሁም አንድነት የኢትዮጵያን መንግስትነት በማያጸናበት ሁኔታ የኢትዮጵያን የወደፊት ተስፋን ማየት በጣም አዳጋች ይመስለኛል።

**ዘመን፡- ዶክተር ያዕቆብ ለጥያቄዎቻችን የተብራራ ምላሽ ስለሰጡን እናመሰግናለን፡፡**

**ዶክተር ያዕቆብ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# «ኢትዮጵያ በራን ከርቸማ ብቻዋን መኖር አትችልም»

## አቶ ዛፉ ኢየሱስ ወርቅ ዛፉ



ተስፋ ፈሩ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የካቲት 15 ቀን 2014 ዓ.ም. በፓርላማ ተገኝተው በሰጡት ማብራሪያ፣ የውጭ አገር ባንኮችን ወደ ኢትዮጵያ ስማስገባት የፖሊሲ ማሻሻያ ስማድረግ ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ተናግረው ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዕለቱ ማብራሪያቸው «ተጨማሪ ሀብት፣ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ስሳስብን የውጭ ባንኮች እናመጣስን። የአገር ውስጥ ባንኮች ዝግጅት ማድረግ ይኖርባቸዋል» ሲሉ አሳስበው ነበር።

ከስድስት ወራት ቆይታ በኋላ የሚኒስትሮች ምክር ነሐሴ 28 ቀን 2014 ዓ.ም. ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ የኢትዮጵያን የባንክ አገልግሎት ዘርፍ ስውጭ ባስሀብቶችና ተቋማት ክፍት የሚያደርገው ፖሊሲ በሥራ ሳይ እንዲውል ውሳኔ አሳልፏል። የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ውሳኔውን ተከትሎ ባወጣው መግስጫ መንግሥት ፖሊሲው ተግባራዊ እንዲሆን የወሰነው የፋይናንስ ዘርፉን ተወዳዳሪነት፣ ውጤታማነትና ቀልጣፋነት በመጨመር፤ በቂ የፋይናንስ አቅርቦት እንዲኖር እና የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት እንዲሳስጥ ስማድረግ መሆኑን ጠቁሞ፤ አዲሱ ፖሊሲ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከዓለም አቀፍ ገበያ ጋር ያለውን ትስስር ወደ ሳቀ ደረጃ ስማሸጋገር ያስችሳል ተብሎ ታምኖበታል። ፖሊሲው ከዚህ በተጨማሪ የሥራ ዕድል ፈጠራ እንዲጎለብት እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ውጤታማነትን እና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ስማረጋገጥ ያስችሳል። የዘርፉን አገልግሎቶች በእውቀት እና በቴክኖሎጂ ስመደገፍ ያግዛል ሲል ጉልህ ጠቀሜታ ይኖረዋል ብሎ ነበር።

ዘመን መፅሔት መንግሥት የፋይናንስ ዘርፉን ስውጭ ባንኮችና ኢንሹራንሶች ክፍት ማድረጉ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እና በባንክ አገልግሎት ዘርፉ ሳይ የሚኖረውን አጠቃሳይ አንድምታ አስመልክታ በኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፍ ውስጥ ቀደምት ተዋናይ ከሆኑት የህብረት ባንክ የቦርድ ሰብሳቢ አቶ ዛፉ ጋር ቆይታ አድርጋስች፤ እንደሚከተስው ቀርቧል።

**ዘመን፡- የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ ዘርፍን ስውጭ ባንኮች ክፍት ስማድረግ ያሳስፈውን ውሳኔ እንዴት አገኙት ?**

**አቶ ዛፉ፡-** ዘገየ እንጂ አዲስ ነገር ሆኖ አይደለም ያገኘሁት። እኔ ወደአገር ቤት ከመመለሴ በፊት ለ 18 አመታት ያህል ከአገር ውጪ ነበርኩ። የመጨረሻዎቹን ዘጠኝ አመታት የመላው አፍሪካ ጠለፋ ዋስትና ድርጅት (African reinshurans corporation) ዋና ሥራ አስፈጻሚ ነበርኩ። ኢትዮጵያም ከዚህ ድርጅት መሥራች አገሮች አንዷ ናት። ዋና መስሪያቤቱ ናይጄሪያ ሌጎስ ሆኖ አፍሪካ ውስጥ ብዙ ቅርንጫፎች አሉት። የዛሬ 30 አመት እዚያ እየሠራሁ እያለ የአፍሪካ የፋይናንስ ገበያዎች ለውጭ ተወዳዳሪዎች ክፍት መሆናቸው አይቀርም ጥያቄው መቼ እና እንዴት ይከፈቱ የሚለው ነው ብዬ ተናግሬ ነበር። እኔ ይህን ስናገር አገራችን ውስጥ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ፣ የኢትዮጵያ መድህን ድርጅት እና አንድ የቁጠባና ቤቶች ባንክ ብቻ ነበር የነበሩት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በበኩሌ የኢትዮጵያ ገበያ ለውጭ ተወዳዳሪዎች ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ዝግ ሆኖ ይቆያል እንጂ ለዘለቄታው ዝግ እንደማይሆን እናገር ነበረ።

መከፈቱ የማይቀር መሆኑን የሚያመላክቱ ነገሮች ነበሩ። አንደኛ ከ18 አመታት በፊት ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ለመሆን አመልክታ ነበር፤ እስካሁን ድረስ ድርድር እየተደረገ ነው የሚገኘው። የአገር ውስጥ ገበያውን ለውጭ ባንኮች ክፍት ማድረግ ድርጅቱን ለመቀላቀል እንደ አንድ መስፈርት የሚወሰድ ነገር ነው። ይሄ ባልተቋጨበት ሁኔታ የኢትዮጵያ ተወካዮች በተገኙበት መድረክ ኪጋሊ ላይ የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣናን እውን ለማድረግ ስምምነት ላይ ተደርሶ ወደ እንቅስቃሴ ተገብቷል። እነዚህ ሁለት ጉዳዮች የፋይናንስ ዘርፉ ለውጭ ተወዳዳሪዎች ክፍት የሚሆንበት ጊዜ በቶሎ እንዲሆን ተጽዕኖ አሳዳሪ ናቸው። ገበያውን ለውጭ ባንኮች ክፍት ማድረጋችን ጥሩ ነገር ነው።

እኛ ችግራችን ገና የግል ባንኮችና ኢንሹራንሶች እንዲመሠረቱ ሲፈቀድ ጀምሮ ሌላ ተወዳዳሪ እንደማይገባበት አድርገን ማስብ ጀመርን። አንዱ በሃይማኖት ሌላው በብሔር እየሔደ በጎጥ ነው ገበያ የፈለግነው፤ በመሠረቱ ይሄ ጥፋት ነው። አስቀድመን ገበያው ለውጭ ባንኮች ክፍት መሆኑ አይቀሬ እንደሆነ መገንዘብ ነበረብን።

**ዘመን፡- ዘርፉ ስውጭ ባንኮች ክፍት የተደረገበት ጊዜ ሳይ የሚስተጋቡ ሀሳቦች አሉ። በአንድ በኩል የኢትዮጵያ ባንኮች ራሳቸውን ከዓለም አቀፍ ባንኮች ጋር ስሚኖር ውድድር ዝግጁ ባሳደረጉበት ሁኔታ ገበያው ክፍት መደረጉ ባልተረጋጋው**

**የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ተጨማሪ ፈተና ይዞ መምጣቱ አይቀሬ ነው የሚሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ባንኮች አቅም እንዲያዳብሩ መንግሥት የተከተለው አካሔድ ከ20 አመታት በላይ እንዳስቆጠረ በመጥቀስ ውሳኔው ተገቢ ነው የሚሉ የዘርፉ ባለሙያዎች አሉ። እነዚህን ሁለት አቋሞች እንዴት ይመለከቷቸዋል?**

**አቶ ዛፉ፡-** እዚህ አገር የተቋቋምን ኩባንያዎች ስለውድድር ብዙ ልምድ የለንም። ልክ እንደ ፖለቲካችን ማሸነፍ ወይም መሸነፍ ነው የምናውቀው። በአንድ ወቅት አቶ ሌንጮ ለታ ይመስሉኛል ስለፖለቲካው ሲያወሩ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ፖለቲካ ፓርቲዎች ድርድር አድርገው ሁለቱም ወገን አሸናፊ ሆኖ የሚወጣበት ነገር ላይ መድረስ በጣም አስቸጋሪ የሚሆንብንና የማናውቀው ነገር ነው፤ ልምድ የለንም። ማሸነፍ ወይም መሸነፍ ነው የምናውቀው ይሄ ልምድ መለወጥ አለበት ብለው ነበር።

ባንክና ኢንሹራንስ ማቋቋም ከጀመርን ወደ 30 አመታት ግድም ሆነን። አሁን ጊዜው እየተለወጠ መጥቷል። ኢትዮጵያ ብቻዋን ጥርቅም አድርጋ በሯን ዘግታ መኖር አትችልም። ከሌሎች አገሮች ጋራ መራመድ ይኖርባታል። ከሌሎች አገሮች ጋር መገበያየት ይኖርባታል። የኢትዮጵያ ድርጅቶችና ኩባንያዎች ከጎረቤት አገራት አቻዎቻቸው ጋር መወዳደር፤ አንዳንድ ጊዜም መዋሃድና አብረው መሥራትም ይኖርባቸዋል። ስለዚህ ጊዜው ላይ እኔ እንዲያውም ዘግይተናል ነው የምለው።

**ዘመን፡- ባለፈው አመት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስብሰባ ላይ የፋይናንስ ዘርፉ ለውጭ ባንኮች ክፍት የሚሆነው ቅድመ ሁኔታዎች ሲጠናቀቁ እና ባንኮች ሲዘጋጁ እንደሆነ ገልጸው ነበር። አሁን በመንግሥት በኩል ቅድመ ሁኔታዎች ተጠናቀዋል፤ የኢትዮጵያ ባንኮች ተዘጋጅተዋል ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ዛፉ፡-** እስኪዘጋጁ እንጠብቅ ከተባለ ምንጊዜም አንዘጋጅም። ምክንያቱም 30 አመታት ተሰጡን፣ ምንም ያህል ወደፊት አልተንቀሳቀስንም። እሺ ስንት አመት ነው የሚበቃን 50 ወይስ 60 አመታት? በመሠረቱ 30 አመታት ብዙ ነበሩ ነገር ግን አልሠራንባቸውም።

**ዘመን፡- የውጭ ባንኮች ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ ሊያበረክቱ የሚችሉት አወንታዊ አስተዋጽኦ ምንድን ነው ?**

**አቶ ዛፉ፡-** በአሁኑ ሰዓት አገራችን ችግር አለብን። አገራችን በጣም ብዙ የውጭ እና የውስጥ እዳ አለባት። የውጭ ምንዛሬ እጥረት እጅግ አድርጎ ጠርንፎ ይዟታል። የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በሚመጣበት ጊዜ የውጭ ምንዛሬ ኢንቨስትመንት ይመጣል። ይሄ ብቻ አይደለም የውጭ ባንኮች በአንድ ወይም በሌላ መልክ እኛ ገበያ ውስጥ ሲገቡ፤ ለምሳሌ የኬንያና ናይጄሪያ ባንኮች ቢመጡ እዚያ አገር ያሉ ወደ



**“የባንክ ዘርፉን ለውጭ ባንኮች ክፍት ለማድረግ ባንኮቻችን ይዘጋጁ ከተባለ ምንጊዜም አንዘጋጅም**

አገራችን መጥተው ኢንቨስት ለማድረግ ፈራ ተባ ሲሉ የነበሩ ተቋሞች ባንካቸው እዚህ ሲገባላቸው ይበረታታሉ። ነገር ግን የውጭ ባንኮች ወደ አገራችን እንዲገቡ መፍቀድ ብቻውን የውጭ ምንዛሬ ማግኛ ዘላቂ መፍትሄ መሆን አይችልም። ዘላቂ መፍትሄ የወጪ ንግዳችንን በማሳደግ የውጭ ምንዛሬ ገቢያችንን ከፍ ማድረግ ነው።

**ዘመን፡- ዓለም አቀፍ ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ ገበያ ሲገቡ በአገር በቀል ባንኮች፣ በማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት፣ በኢንሹራንሶችና በአጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደርና አለማሳደራቸው መንግሥት በሚፈቅዳቸው የአገልግሎት ዓይነቶች እንደሚወሰን የፋይናንስ ዘርፍ ሰዎች ይናገራሉ። መንግሥት ምን ዓይነት ማዕቀፎችን በአማራጭነት ማቅረብ አለበት ይላሉ?**

**አቶ ዛፉ፡-** የውጭ ባንኮች ወደ አገር ውስጥ ይገቡበታል ተብሎ በፖሊሲ ደረጃ የቀረበው አራት መንገድ ነው። አንዱ መንገድ ቀድሞም የነበረ ገበያውን ለመከታተል እንዲችሉ ቢሮ እንዲከፍቱ መፍቀድ ነው። ሌላኛው መንገድ እንደ ውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ተቆጥረው

የራሳቸውን ባንክ አቋቁመው ወደ ሥራ መግባት ነው። በዚህ መንገድ ገብተው ተቀማጭ ገንዘብ ይቀበላሉ ሁሉንም ነገር እንደሌሎች ባንኮች ይሠራሉ ማለት ነው። ይህ ማለት የውጪ ባንክ ከኢትዮጵያውያን አክሲዮን መግዛት ሳያስፈልገው ራሱን እዚህ አገር እንዲፈጥር መፍቀድ ነው። ተጨማሪ አማራጭ ሆኖ የቀረበው ሌላ መንገድ ቅርንጫፍ እንዲከፍቱ ዕድል የሚሰጥ ነው። ኬንያ፣ ናይጄሪያ ወይም ሎንደን ያለ ባንክ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ብሎ ኢትዮጵያ ውስጥ ተደራሽ የሚሆንበት ነው። ሦስተኛው መንገድ የውጭ ባንኮች ከዚህ አገር ባንኮች ጋር ተቀናጅተው አዲስ ኩባንያ ማቋቋም ወይም ካሉት ባንኮች ውስጥ የባለቤትነት ድርሻን መግዛት ነው። ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ በበኩሌ የተሻለ ነው የምለው ይሄኛውን ነው።

የውጭ ባንኮች ወደአገራችን መግባታቸው በአንዳንድ ሁኔታዎች ችግር እንዳይፈጥር ጥንቃቄ ይደረጋል። እንዲሁ ዝም ብሎ ፈረንጆች "fly by night" እንደሚሉት አንድ ጊዜ ቦጭቀው የሚሄዱ ኢንቨስተሮች አይደለም የምንፈልገውና የምንጠብቀው። አገራችን ውስጥ ገብተው ተቀናጅተው ጥሩ ሥራ ሠርተው ውጤት አምጥተው እነርሱም ተጠቃሚ እንዲሆኑ እኛም እንድንጠቀም ነው የምንፈልገው። በተለይ ደግሞ ከላይ እንደጠቀስኩት የውጭ ባንኮች እዚህ መጥተው ራሳቸውን ችለው ቢሯቸውን ከፍተው የሚቋቋሙ ከሆነ አንዳንድ ዋስትናዎች ያስፈልጉናል። እዚህ መጥተው የሚቋቋሙት ባንኮች በአገራቸው በምን ዓይነት ቁጥጥር ስር እንዳሉ መታወቅ አለበት። ምክንያቱም እዚያ ያለ ኪሳራ እዚህ ሊመጣ ይችላል። በእርግጥ እዚህ አገር መጥተው ሲቋቋሙ በአገራቸው ሕግ ሳይሆን በአገራችን ሕግ ነው የሚተዳደሩት። ብሔራዊ ባንክ ነው የሚቆጣጠራቸው፤ ስለዚህ የሚቀመጡ መስፈርቶች ይኖራሉ እነሱን ማሟላት አለባቸው። በአጭሩ ጥንቃቄ የሚወሰድባቸው ነገሮች አሉ ማለት ነው።

ባንኮቹ አገር ውስጥ ካሉ ባንኮች የባለቤትነት ድርሻ ሲገዙ እስከ ምንያህል በመቶ ነው የሚወስዱት የሚለው በእጅጉ ወሳኝ ነገር ነው። ለምሳሌ በአንድ ጊዜ ከፍተኛ ድርሻ እንዲወስዱ ማድረግ ይጎዳናል። አሁን በብሔራዊ ባንክ የቀረበው ሀሳብ 30 በመቶ የውጭ ባንክ፣ አምስት በመቶ የውጭ ድርጅት ወይም ዜጋ እንዲሁም አምስት በመቶ ትውልደ ኢትዮጵያውያን በአጠቃላይ በውጭ ሰዎች እና ድርጅቶች እስከ 40 በመቶ የባለቤትነት ድርሻ መያዝ ይችላል የሚል ነው። ይሄ ብዙ ጥናት ተደርጎበት የቀረበ ነው። ለምን ያህል ጊዜ በዚህ ደረጃ እንደሚቆይ ገና አልተወሰነም። እኔ በበኩሌ ቀደም ሲል ጀምሮ ከ15 እስከ 30 በመቶ፣ ቢበዛ እስከ 35 በመቶ የሚል ሀሳብ ነበረኝ አሁን በብሔራዊ ባንክ የቀረበው ሀሳብ ከዚህ ብዙም የራቀ አይደለም።

በዚህ የባለቤትነት ድርሻ ይዞታቸው እስከ ምን ያህል ጊዜ ይቆያሉ የሚለው መወሰን



አለበት። ምናልባት ሦስት አመት ሊሆን ይችላል፣ ከዚያ በኋላ ግን እንደሚታወቀው አሁን የሼር ገበያ ከአመትና ሁለት አመት በኋላ ስለሚከፈት ሼሮች እዚያ ላይ ሲሸጡ እነዚህ 30 በመቶ ድርሻ የነበራቸው የውጭ ባንኮች 70 እና 80 በመቶ አልፈውም መቶ በመቶ የባለቤትነት ድርሻዎችን ሊይዙ ይችላሉ። ቀደም አድርገን ብንጀምረው ኖሮ ለመጀመሪያ ሦስት አመት ይህን ያህል፣ ለተከታዮቹ አምስት አመታት ደግሞ የዚህን ያህል እያልን ረዘም ያሉ አመታት ልንወስድ እንችል ነበር። አሁን እየተጣደፍን ነው የምናደርገው፣ ምክንያቱም ከሚያስፈልገው በላይ ዳተኞች ሆነን ብዙ ቆየን። ነገር ግን ትክክለኛ ነገር እስከሆነ ድረስ ዘግይተናል በማለት ነገሩን ልናኮስሰው ስለማይገባ በአሁኑ ሰዓት ውሳኔ ላይ መደረሱ ጥሩ ነው ብዬ ነው የማስበው።

**ዘመን፡- ዘርፉን የሚመራው ብሔራዊ ባንክ የተሻለ ቴክኖሎጂና የሰለጠነ የሰው ኃይል ይዘው የሚመጡትን የውጭ ባንኮች ለመምራትና መቆጣጠር አቅም ገንብቷል ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ዛፉ፡-** ብሔራዊ ባንክ ራሱ ባወጣው አንድ ሰነድ ላይ ራሱን እንደገና ማደራጀትና ማጠናከር እንዳለበት ይገልጻል። ቢያንስ ብሔራዊ ባንክ አሁን ባለበት ሁኔታ መቶ በመቶ ዝግጁ አለመሆኑን ማወቁና መገንዘቡ መልካም ነገር ነው። ይሄ ማለት አስፈላጊውን ዝግጅት ያደርጋል ማለት ነው። ገበያው ለውጭ ባንኮች ይከፈታል ሲባል አሁንም ቢሆን የአመታት ዕድሜ ባይሆንም የወራት የዝግጅት ጊዜያት አሉ። ምክንያቱም ባንኮችም ራሳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው፣ ብሔራዊ ባንክም ራሱን ማዘጋጀት አለበት። እንጂ እንዲሁ ዝም ብሎ ዛሬ ተወስኖ ከነገ ጀምሮ ባንኮች መግባት ትችላላችሁ የሚባልበት ሁኔታ አይደለም።

**ዘመን፡- የፋይናንሱ ዘርፍ ለውጭ ባንኮችና ኢንሹራንሶች ክፍት ሲደረግ የኢትዮጵያ ባንኮችና ኢንሹራንሶች ተወዳዳሪ ስመሆን የሚቸገሩበት አንዱ ጉዳይ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማግኘት ነው። ይህን ነባር ችግር ለመቅረፍ የፋይናንስ የስልጠና ተቋም ለማቋቋም ረዘም ላለ ጊዜ ሲደረግ የነበረው እንቅስቃሴ አሁን ምን ደረጃ ላይ ደገኛል?**

**አቶ ዛፉ፡-** በአገር ደረጃ ከ25 አመታት በፊት ለፋይናንስ ተቋማት የሰው ኃይል ለማፍራት በደምብ ታስቦበት አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጎ ነበር። በደብረዘይት መንገድ ከአቃቂ ከተማ መውጫ ላይ በስተግራ በኩል የሚገኝ አንድ ትልቅ ግቢ በኮንትራክተር ተሠርቶ እዚህ የኢትዮጵያ የባንክና ኢንሹራንስ ስልጠና ኢንስቲቲዩት ይቋቋማል ተብሎ ነበር። በኋላ ባልታወቀ ምክንያት ለአዲስ አበባ ለዩኒቨርሲቲ ተሰጠ። ከጊዜ በኋላ በምዕጻረ ቃል ዩኒሳ ተብሎ ለሚጠራው የደቡብ አፍሪካ ዩኒቨርሲቲ ተሰጠ። እባካችሁ የፋይናንስ ኢንዱስትሪው የሰለጠነ የሰው ኃይልን ከየት ያግኝ? እያልን ስንወተውት ቆይተናል። አሁን እንደማውቀው ለብሔራዊ ባንክ ተመልሷል። ብሔራዊ ባንክ ይሄን ተቋም ሥራ ለማስጀመር ጥናት እያደረገ እና አንዳንድ ሥራዎችን እየሠራ ያለ ይመስለኛል ነው።

አንዳንዶቻችን ይህንን ተቋም ሥራ ለማስጀመር የሚደረገውን እንቅስቃሴ በበላይነት መምራት ያለባቸው የብሔራዊ ባንክ ገዢ ናቸው ብለን እናምናለን። ብሔራዊ ባንክ ከ10 አመታት በፊት የውጭ ባንኮች ሲገቡ እነርሱን በደንብ ለመቆጣጠር የሚያስችል አቅም እንድንፈጥር በሚል ከዓለም ባንክ ከ13 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ብድር ወስዷል። አቅም ገንብተውበታል አልገነቡበትም የሚለውን እኔ አላውቀም። ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት ተቋሙ ለብሔራዊ ባንክ ስለተመለሰ ቢቋቋም ጥሩ ነው። እንዲያውም ኢንስቲቲዩቱ የምሥራቅ አፍሪካ የልዕቀት ማዕከል ሆኖ ቢቋቋም ጥሩ ነው። ኢትዮጵያ በዲፕሎማቶች መናኸሪያነት ከዓለም ሦስተኛዋ አገር ስለሆነች ለእንዲህ ዓይነት የልዕቀት ማዕከል አመቺ ቦታ ናት። በአገር ውስጥ ዘርፉ የሚፈልገውን የሰው ኃይል ከማሟላት አልፈን ከሌሎች አገራት ሰልጣኞች እየመጡ የሚሰለጥኑበት ተቋም እንዲሆን ማድረግ እንችላለን።

ባንኮችና የፋይናንስ ተቋማት በሙሉ ይህንን ተቋም ለመፍጠር የሚያስፈልገውን መዋዕለንዋይ ለማፍሰስ ዝግጁ ስለሆኑ የገንዘብ ችግር የለብንም። እኔ እንግዲህ ምን ችግር እንደያዘን አሁን ለጊዜው አልገባኝም። ከሁለት አመት በፊት የብሔራዊ ባንክ ገዢው ክቡር ዶክተር ይናገር ደሴ ኢንስቲቲዩቱ

ስለሚቋቋምበት ሁኔታ ሀሳብ አምጡ ብለውን አንድ ስድስት ሆነን ጥናት አድርገን ኢንስቱቲዩቱ ባንኮችን፣ ኢንሹራንሶችን፣ ማይክሮ ፋይናንስን፣ ሊዝ ፋይናንስን እና ዩኒቨርሲቲን ያሳተፈ ሆኖ እንዲቋቋም ሀሳብ አቅርበን ነበር። ዩኒቨርሲቲዎች ያስፈለጉት ስልጠና ስለሆነና ወደፊት ሙያዊ የሆነ ዕውቅና ሊሰጥበት ስለሚችል ነው። ምክንያቱም ይሄ ተቋም ቢፈጠር መጀመሪያ ማድረግ ያለበት መካከለኛ አመራር ለሚባሉት በሥራ ላይ ላሉት በፋይናንሱ ዘርፍ ላሉት ሠራተኞች አሁኑኑ ውጤታማ መሆን እንዲችሉ አጫጭር የሥራ ላይ ስልጠናዎች መስጠት ነው። ወደፊት ግን ጥናትና ምርምሮች ይደረጉበታል፤ ከዩኒቨርሲቲ ጋር ተቀናጅቶም ለድህረ ምረቃና ከዚያም በላይ ትምህርት ሊሰጠበት ይችላል። ይህን ጥናት አቅርበን የብሔራዊ ባንክ ገዢውን አነጋግረናል። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንቱን ፕሮፌሰር ጣሰውን ቀጥሮ ተቀብዬ አነጋግሬያለሁ፤ ለመሳተፍ ዝግጁ እንደሆኑ ነግረውኛል። ይሄ ነገ ዛሬ ሳይባል አሁኑኑ መደረግ ያለበት ነገር ነው። አሁን እንደምሰማው ደግሞ ይህንኑ ሥራ ለመሥራት በንግድ መልክ ተቋም ለማቋቋም የሚንቀሳቀሱ ሰዎች አሉ። በእኔ እይታ በአሁኑ ጊዜ አቅማችንን በያለበት ከመበታተን አንድ ላይ ሆነን ሙያተኞችና ተቋማት ተሳትፈውበት ሕዝብና መንግሥት በጋራ አንድ ተቋም በቶሎ ብናቋቁም በጣም ይጠቅማል።

**ዘመን፡- በመንግሥት በኩል የባንክ ዘርፉን ለውጭ ባንኮች ክፍት ማድረግ ያስፈለገው «ተጨማሪ ሐብት፤ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ» ማግኘት መሆኑን ጠቅሰው ነበር። በአንጻሩ በጥቁር ገበያ አንድ ዶላር ከመቶ ብር በላይ እየተመነዘረ ይገኛል። ይህ በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ ምን ዓይነት ጫና ይፈጥራል ? መንግሥት ሁኔታውን ለዘለቄታው ለመቆጣጠር ምን ዓይነት እርምጃዎችን መውሰድ አለበት?**

**አቶ ዛፉ፡-** *መንግሥት ጥቁር ገበያውን በተመለከተ በቅርቡ እርምጃዎችን ወስዷል። እንዲህ ያለ ተጨማሪ እርምጃ ይውሰድ ለማለት እቸገራለሁ። ነገር ግን ምንድን ነው አስቀድሞ ማሰብና ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን በተወሰነ ደረጃ ተንብዮ እንዳይሆኑ ዝግጅት ማድረግ ላይ አገራችን ውስጥ ችግር አለብን። የፋይናንስ ዘርፉ አንዱ የዚህ ችግር ሰለባ ነው። የተናጠል እርምጃዎች ይወሰዳሉ። እኔ እንደሚገባኝ ይህ ከግንዛቤ ማጠር እንጂ ሆነኝ ተብሎ ለተንኮል የሚደረግ አይመስለኝም። ምክንያቱም በሙያው ውስጥ ብዙ ያልቆዩ ሰዎች የሥራው ጫና ተጣደባቸው፤ ምን ያድርጉ? የሚችሉትን ያህል ይሞክራሉ።*

አንዳንድ የተወሰዱ እርምጃዎች ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው አመዝኗል። ለምሳሌ ፍራንኮ ቫሎታ ሲፈቀድ ሌሎች ብዙ ቀዳዳዎች ይከፈቱ ነበር። ይህንን ለማወቅ ኒውክሌል ሳይንስ መማር አያስፈልግም ነበር። ፍራንኮ ቫሎታ ሲፈቀድ ምንድን ነው የሆነው? በቀጥታ ላኪዎች አስመጪ



ነው የሆኑት። ቡና ወደ ውጭ ይልኩና የውጭ ምንዛሬውን ወደ አገራችን በማምጣት ፈንታ ሌላ ዕቃ ማስገባት ጀመሩ። እንዲያውም ከጊዜ በኋላ የውጭ ምንዛሬው ላይ የሚያገኙት ትርፍ ያንን ኪሳራ ሸፍኖ ሌላ ገቢ ስለሚያስገኝላቸው ቡናውን ከተገዛበት ባነሰ ዋጋ በኪሳራ ለውጭ አገራት መሸጥ ጀመሩ። ቆይቶ ብሔራዊ ባንክ ሲነቃ ዋጋ ቆርጦ ወደ ውጭ አገር የሚላክ ቡና ከዚህ ዋጋ በታች መሸጥ አይቻልም የሚል ሕግ አወጣ።

**ዘመን፡- ገንዘብ ሚኒስቴር የውጭ ምንዛሬን የቅድሚያ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው የምግብ ሸቀጦች፣ መድኃኒቶችና የሕክምና ቁሳቁሶች ለማዋል በሚል ከውጭ የሚገቡ 38 ዓይነት ምርቶች ላልተወሰነ ጊዜ የውጭ ምንዛሬ ከማግኘት ታግደዋል። ክልከላውን እንዴት ይመለከቱታል?**

**አቶ ዛፉ፡-** ይሄ ብዙ ጊዜ የምንጠይቀው ነገር ነበረ። ሰው በልቶ ማደር እያቃተው ግብስብስ ነገር በውጭ ምንዛሬ ወደ አገር ውስጥ መግባት የለበትም። ያለችንን የውጭ ምንዛሬ በትክክለኛ ቦታ ላይ ማዋል እንዲሁም ሊያጋጥሙ የሚችሉ ነገሮችን አስቀድሞ በመተንበይ የጥንቃቄ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። ተቸግረን ነው ምን እናድርግ? አገር የውጭ ምንዛሬ ገንዘብ የላትም። ዕዳ መክፈልም አለባት። ተጽዕኖ የሚያደርጉብን አገራት ስላሉ ብድር ደግሞ እንደ ድሮ አይደለም። የተበደርነውን እንኳን ክፍያ ለማራዘም በዓለም ባንክ በኩል ጥያቄ አቅርበን እስካሁን ድረስ አበዳሪዎቻችን አንድ ላይ ቁጭ ብለው ተነጋግረው እንዲህ ያለ አስተያየት እናድርግላቸው አላሉም። አገራችን ጦርነት ውስጥ በመክረሟ በተለያየ መልኩ ጫናዎች እየመጡብን ነው። ሁሉነገር የተሳሰረ ነው። እኔ እንዲያውም አገራችን ካለችበት ሁኔታ አንጻር ከዚህ የባሰ ነገር ውስጥም ልንገባ እንችል ስለነበር ተመስገን ነው የምለው። ችግር አለ ነገር ግን ጠንክረን መታገልና ማለፍ አለብን፤ እኔ እናልፋለን ብዬ ነው የማምነው።

**ዘመን፡-** ለነበረን ቆይታ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

**አቶ ዛፉ፡-** እሺ እኔም አመሰግናለሁ።

# የቀንዱ ቀኝጸኛ ሀገር ተጋድሎ

ተስፋ ፈሩ

ኢትዮጵያ፣ ኤርትራ፣ ኬንያ፣ ሶማሊያ፣ ሱዳን፣ ኡጋንዳ፣ ደቡብ ሱዳን እና ጂቡቲን የያዘው የአፍሪካ አህጉር ምሥራቃዊ ጫፍ (በቅርጻዊ አጠራሩ የአፍሪካ ቀንድ) በምስራቅ በህንድ ውቅያኖስ እና በሰሜን በኤደን ባህረ ሰላጤ መካከል ይገኛል። የአፍሪካ ቀንድ በመቶዎች በሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮች ወደ አረብ ባህር ይዘልቃል። ከ 772,200 ስኩዌር ማይል በላይ የሚሸፍን ሲሆን አብዛኛው ከፊል ደረቃማ እና ደረቃማ የአየር ጠባይ ያለው ነው። አካባቢው ለባህር ንግድ፣ ለነዳጅ ታንከሮች እና ለጭነት አገልግሎት ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ የዓለም ኃያላን ሀገራት አይን ማረፊያ ነው።

ኢትዮጵያ በቀጠናው በሚገኙ ሀገሮች ሰላም፣ ፀጥታና መረጋጋት ላይ ቁልፍ ሚና የምትጫወት ሀገር ነች። ከሦስት አስርት አመታት በፊት በሩዋንዳ የተፈጸመውን የዘር ፍጅት ተከትሎ ሀገሪቱን ለማረጋጋት ሰላም አስከባሪ ወታደሮችን ከላኩ ሀገራት መካከል ግንባር ቀደም ናት። አሜሪካኖች ተዋርደው ወደ ወጡባት ሶማሊያ ወታደሮቿን በመላክ መንግሥት አልባነትንና አክራሪነትን ታግላ መንግስት እንዲመሰረት ጉልህ ሚና ተጫውታለች። በሱዳን-ዳርፉር ግዛት የእርስ በርስ ግጭት እንዳይስፋፋ የበኩሏን አስተዋጽኦ አበርክታለች። ሱዳንና ደቡብ ሱዳን በይገባኛል በሚወዛገቡበት የአብዬ ግዛት ከሁለቱም ወገን እምነት የተጣለባት ብቸኛ ሀገር ሆና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጥላ ስር ሰላም አስከባሪ ኃይል በማሰማራት በጎ ሚናዋን አጠናክራ ቀጥላለች።

ይህ ኢትዮጵያ በቀጣናው ሰላምና መረጋጋት ላይ የምትጫወተው ቁልፍ ሚና በታሪካዊ ጠላቶቿ እና በአካባቢው ጥቅማቸውን ለማስከበር በሚንቀሳቀሱ አንዳንድ ምዕራባውያን ሀገራት ዘንድ በበጎ አይታይም። ስለዚህም ምቹ ጊዜ አገኘን ብለው ባመኑ ቁጥር ይህችን ታላቅ ሀገር ወደ ደርዘን ትናንሽ ሀገርነት ለመቀየርና ህዝቦቿን ለመበተን የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። ይህን ማድረግ የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ደግሞ የተረጋጋችና ሰላማዊ ሀገር እንዳትሆን የጦርነት አውድማ ሊያደርጓት ላይ ታች ይላሉ። ኢትዮጵያ በቀጣናው ካሉ ሀገራት ጋር ያላትን የመሰረተ ልማት ትስስር በአይነትና በመጠን እያሰፋች መምጣቷ እንቅልፍ ነስቷቸዋል።

ፀሐይ በምስራቅ እንደምትወጣ የአፍሪካ የነጻነት ፀሐይ ኢትዮጵያም በምስራቁ የአህጉሪቱ ክፍል መገኘቷ ግጥምጥሞሽ ብቻ አይመስልም። እንደ ትናንቱ አድዋ ሁሉ ለወቅታዊው የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ እምቢኝ አሻፈረኝ በማለት የሞት ሽረት ተጋድሎ አድርጋ ዛሬም ለአፍሪካውያን የነጻነት አርማ ሆና መቀጠሏን በተግባር አስመስክራለች። በዚህ ጽሑፍ ኢትዮጵያ የገጠማትን ውስጣዊ ችግር ለመሻገር ባደረገችው ተጋድሎ የተቀናጀችውን ድል እና አጋጣሚውን ተጠቅመው ከካርታ ላይ ሊፍቋት የተነሱ ጠላቶቿን ርብርብ ከምስራቅ አፍሪካ ቀጣና ጋር አያይዘን እንመለከታለን፤ መልካም ቆይታ።

**አሞራ በሰማይ ...**

"አሞራ በሰማይ ሲያይሽ ዋለ" ተብሎ የተዘፈነው ለአፍሪካ ቀንድ ሳይሆን አይቀርም። ምድሯ ላይ ላለው ስጋ የሚፋለሙት የሰማይ አሞራዎች ቁጥር የትየለሌ ነው። መሬት ላይ ያለው ሀቅ እና ቀጠናውን ለመቀራመት የሚቋምጡ ሀገራት የሚያስተጋቡት ትርክት የማይገናኝ ነው። "ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ ግጅራ ነሽ ይሏታል" ነው ነገሩ። አፍሪካን አይዞሽ ባዮቹ አመዛኝ "ወዳጆቿ" ማጽናኛቸው "No matter how bad you are, you're not useless. You can still be used as a bad example." የሚል ነው። አጃኢብ! እውነታው ግን ሌላ ነው። የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ህዝቦች በባህል፣ በታሪክ፣ በቋንቋ ፣ በአብሮ መኖር፣ በጋብቻ በመተሳሰር እና አንዱ የሌላኛውን ሀገር እንደ ሁለተኛ መኖሪያው በመቁጠር ጥብቅ ግንኙነት የመሰረቱ እና ዘመናትን በዘለቀ ትስስር የተጋመዱ ናቸው።

አንዳንድ ኃያላን ሀገራት እንዲሁም አህጉር እና ዓለም አቀፍ ተቋማት በሌሎች መሰል ቀጣናዎች ባልተለመደ ሁኔታ ለአፍሪካ ቀንድ ብቻ ልዩ መልዕክተኛ መሾማቸው ለብዙዎች እንግዳ ነገር ነው። አሜሪካ፣ ቻይና፣ ብሪታንያ፣ የአውሮፓ ህብረት ተመድ እና የአፍሪካ ህብረት በአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ (ልኡክ) ሾመዋል። እነዚህ ሀገራት እና ተቋማት በአፍሪካ አህጉር ካሉ ክፍሎች ውስጥ ልዩ አምባሳደር የሾሙት ለአፍሪካ ቀንድ ብቻ ነው።

አሜሪካ በውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቷ ቀድሞ ያልነበረ አዲስ መዋቅር በመፍጠር የአፍሪካ ቀንድን ሁኔታ "ለመከታተል" በሚል ልዩ መልዕክተኛ ከመደበች ገና ሁለተኛ አመቷን መያዟ ነው። መጀመሪያ ጄፍሪ ፌልትማንን የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ አድርጋ ሾማ የነበረ ሲሆን

**ኢትዮጵያ በቀጣናው ካሉ ሀገራት ጋር ያላትን የመሰረተ ልማት ትስስር በአይነትና በመጠን እያሰፋች መምጣቷ እንቅልፍ ነስቷቸዋል**

ውጤት እንዳጣ የእግር ኳስ ቡድን አንዱን አባራ ሌላኛውን እየተካች በሁለት አመት ውስጥ አራት ልዩ መልዕክተኞችን አፈራርቃለች። ሴናተር ክሪስ ኩንስ፣ አምባሳደር ጄፍሪ ፌልትማን ፣ አምባሳደር ዴቪድ ሳተርፊልድ እና አሁን በኃላፊነት ላይ ያሉት አምባሳደር ማይክ ሐመር ለዲፕሎማቲኩ መንደር እንግዳ በሆነ መንገድ ተፈራርቀው የአፍሪካን ቀንድ "ሾፍረዋል"

ፎሬይን ፖሊሲ የተባለው መጽሔት አምባሳደር ዴቪድ ሳተርፊልድ ከኃላፊነት መነሳታቸውን ሲሰማ እርምጃውን "ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የጅምላ ግድያና የረሃብ ስጋት ባለበት ቀጣና ትልቅ የሆነ የዲፕሎማሲ ክፍተት የሚፈጥር" ሲል ዘግቦት ነበር። መሰል ዓለም አቀፍ የዜና ተቋማት የአፍሪካን ቀንድ ሲኦል አድርገው በማቅረብ ራሳቸውን የቀጣናውን ህዝብ ለመታደግ እሳት ውስጥ የተገኘ "መልአክ" አድርገው ማቅረብ መደበኛ ስራቸው ነው። በጎ ነገርን ላለማየት ሆነ ብሎ አይንን የጨፈነን ሰው እውነታውን እንዲመለከት መለማመጥ ጉንጭ ማልፋት ቢሆንም በቀጣናው ያሉ ኢትዮጵያን የመሰሉ ሀገራት ግን ሳይታክቱ እውነታውን ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለማስረዳት ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ ከማድረግ አልተቆጠቡም። ጽናት!

አሜሪካ ልዩ መልዕክተኛ ከሾመች ከ 270 ቀናት በኋላ ቻይናም በአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛዬን እወቁልኝ ብላለች። ቻይና አምባሳደር ሹ ቢንግን በአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ አድርጋ መሾሟን ይፋ ስታደርግ በውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቷ በኩል በሰጠችው መግለጫ በአፍሪካ ቀንድ ሰላምና ልማት እንዲጎለብት ለማበረታታት እንደምትሰራ ገልጻለች። በቀጣናው ያሉ ሀገራት የሚያጋጥሟቸውን የፀጥታ እና ደህንነት ስጋቶችን ለመቀልበስ የሚያደርጉትን ጥረት እደግፋለሁ ስትልም በአካባቢው የሚገኙ ሀገራትን አለውላችሁ ብላለች። በዚህ እርምጃዋ ያልረካቸው የቻይና ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዋንግ ዪ በምስራቅ አፍሪካ የሚገኙ ሁሉም ሀገራት በአፍሪካ ቀንድ ሰላም ላይ ያተኮረ ጉባዔ እንዲያደርጉ ሃሳብ እስከመገፋፋት ደርሰዋል።

የብሪታኒያ መንግስት ለአፍሪካ ቀንድ እና ለቀይ ባሕር አካባቢ አዲስ ልዩ መልዕክተኛ መሾሙን ያሳወቀው ከአምስት ወራ በፊት ነበር። በወቅቱ በብሪታኒያ ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የአፍሪካ ሚኒስትር ቪኪ ፎርድ በአፍሪካ ቀንድ ካለው የሰብዓዊ ቀውስ እስከ ገልፍ ባለው ቀጣና ብሪታኒያ ከቀይ ባህር ጋር ያላት ግንኙነት ጠንካራ ሰው እንደሚፈልግ ገልጸው ነበር። ከሹመት ዜናው ጋር በቀይ ባህር እና በአፍሪካ ቀንድ ባሉ ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ የብሪታኒያን ምላሽ የልዩ መልዕክተኛዋ ስራ መሆኑ ተገልጿል። ለአፍሪካ ቀንድ እና ለቀይ ባሕር አካባቢ የተሾሙት ልዩ መልዕክተኛ ሳራህ ሞንትጎሜሪ ናቸው። አዲሷ ልዩ መልዕተኛ የአፍሪካ ቀንድ በግጭት፣ባለመረጋጋትና በአየር ጸባይ ለውጥ ምክንያት የሰብዓዊ መቅሰፍት ላይ እንደሆነ በመግለጽ ስለቀጣናው ያላቸውን የተንሸዋረረ ግንዛቤ ተንፍሰው ትልቅ ስራ ይጠብቀኛል ሲሉ ለመኩራት ዳድቷቸው ነበር።

**አንዳንድ ምዕራባውያን ሀገራት እና ድርጅቶቱ በተቀናጀ መንገድ ተጸፖፖሚ ጫናዎቱ ሲያደርሱባት ቆይተዋል**

ልዩ መልዕክተኛ ከመሾም በበለጠ በአፍሪካ ቀንድ የጦር ሰፈር ለመገንባት የሚደረገው እሽቅድምድም ሀገራትን ፍጥጫ ውስጥ እየከተተ ይገኛል። ፈረንሳይ፣ ቱርክ ፣አሜሪካ፣ ቻይና እና ጃፓን በቀጠናው የጦር ሰፈር ገንብተዋል። ጂቡቲ የስምንት ሀገራትን የጦር ሰፈሮች በመያዝ በቀዳሚነት ተቀምጣለች። ሀገራቱ አሜሪካ፣ ጃፓን ፣ ጣሊያን፣ ቻይና፣ ሳዑዲ አረቢያ፣ ፈረንሳይ ፣ ጀርመን እና ስፔን ናቸው። በኤርትራ ደግሞ የሩሲያ እና የተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች የጦር ሰፈራቸውን ገንብተዋል። በሶማሊያ የቱርክ የጦር ሰፈር የተገነባ ሲሆን በሶማሊላንድ የተባባሩት አረብ ኤምሬትስ የቀጣናው ሁለተኛ ሰፈር ይገኛል። ሩሲያ ሁለተኛ የጦር ሰፈሯን በሱዳን ለመገንባት የአሜሪካ ተጽዕኖ ያረፈበት እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ናት። ሌሎች ሀገራትም በአካባቢ ባሉ ሀገራት ውስጥ የጦር ሰፈር ለመገንባት መንገድ ላይ ናቸው።

ሎግማን አስማን በተመድ የአፍሪካ ቢሮ የደህንነት አማካሪ ሲሆኑ የአፍሪካ ቀንድ የጸጥታ እና ደህንነት ጉዳዮችን በመተንተን ይታወቃሉ። ሎግማን አስማን ለአንላይን የዜና ድረ ገጽ እንደተናገሩት፤ ባለጸጋ ሀገራትን ጨምሮ መላው የዓለማችን ሀገራት ሁሉ የተፈጥሮ ሀብት፣ ሰፊ የገበያ አቅም ያለው ህዝብ ብዛት መኖር እና አካባቢው ከሌሎች አህጉራት ጋር ያለው ቅርበት ሀገራቱን ለአፍሪካ ትኩረት እንዲያደርጉ አድርጓል ብለዋል። እነዚህ ሀያላን ሀገራት ወደ አፍሪካ ቀንድ መምጣታቸው በራሱ ችግር ባይኖረውም የፍላጎት መወሳሰብ እና በሉዓላዊ ሀገራት የውስጥ ጉዳዮች ላይ ጣልቃ መግባትን ሊያስከትል እንደሚችል ስጋታቸውን አክለዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማህበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ የአፍሪካ እና ኢስያ ጉዳዮች መምህር ዶክተር ሳሙኤል ተፈራ በበኩላቸው አፍሪካ ቀንድ በዓለም ላይ ካሉ ተፈላጊ ቦታዎች መካከል አንዱ መሆኑን ይጠቅሳሉ። ሽብርተኝነት፣ የባህር ላይ ዝርፊያ እና ሌሎች ጉዳዮች በአካባቢው ያሏቸውን ጥቅሞቻቸውን እንዳያሳጧቸው በመስጋት የአፍሪካ ቀንድ በኃያላኑ ሀገራት ትኩረት የሚደረግበት ቦታ በመሆኑ፣ ወታደራዊ የጦር ሰፈርን ከመገንባት ጀምሮ ልዩ ልዑክ እስከመሾም የደረሰ እንቅስቃሴዎች እንደሚደረጉበት ይናገራሉ። እነዚህ የዓለማችን ሀገራት ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ የአጋር ሀገራት መሪዎች በስልጣን ላይ እንዲቆዩ ድጋፍ ማድረግን ጨምሮ ለጥቅማቸው ስጋት የሆነ ሀገር ስርዓትን እንዳይረጋጋ በሚል ቡድኖችን እና አማጺዎችን እስከመርዳት ሊደርሱ እንደሚችሉም ዶክተር ሳሙኤል ይገልጻሉ። ከዚህ በፊት አፍሪካ ቀንድ ላይ ትኩረት የሚያደርጉት ዋና ዋና የዓለማችን ሀያላን ሀገራት እንደነበሩ በማውሳት ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ግን ቱርክ፣ ኢራን ፣ግብጽ እና መሰል ሀገራትም ለቀንዱ ልዩ ትኩረት በመስጠት ላይ ናቸው። እነዚህ ኃያላን ሀገራት ጥቅማቸውን ሊያስጠብቁላቸው የሚችሉ ታዛዥ ሀገራትን መያዝ ዋነኛ ትኩረታቸው በመሆኑ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት

ከጥገኝነት ሊያወጧቸው የሚችሉ ስራዎችን ከወዲሁ ሊሰሩ ይገባል ሲሉ ያሳስባሉ።

በቀጣናው ተስፋን የሚሰጡ መልካም ዜናዎችም እየተሰሙ ነው። የሩሲያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጌይ ላቭሮቭ የሀገራቸውን ቀጣይ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲና ስትራቴጂ በተመለከተ በቅርቡ በሰጡት መግለጫ "ቅድሚያ ሰጥተን ከምንሰራባቸው የውጭ ጉዳይ ቁልፍ ስራዎች መካከል ከአፍሪካ ሀገራት ጋር ያለንን ሁሉን አቀፍ አጋርነት ማጠናከር አንዱ ነው" ማለታቸው ቻይና ለቀጠናው ከሰጠችው ትኩረት ጋር ተደምሮ አንዳንድ ምዕራባውያን ሀገራት በአፍሪካ አህጉር ብሎም በአፍሪካ ቀንድ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ልጓም ሊበጅለት ጊዜው መቃረቡን አመላካች ተደርጎ እየተወሰደ ነው። እ.አ.አ በ2019 ስትራቴጂካዊ በሆነ ውሳኔ በሶቺ የተጀመረው የሩስያ አፍሪካ ጉባኤ የሁለትዮሽ ግንኙነቱን የበለጠ ለማጠናከር የሚያስችል ሁነኛ ሀዲድ በመሆን እያገለገለ ነው። ቻይና እና ሩሲያ ከአፍሪካ ጋር ያላቸው ግንኙት የሚመራበት መርህ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥን እና ወንድማማችነትን በማጠናከርና ሉዓላዊነትን ማክበር ላይ ያተኮረ በመሆኑ የእጅ ጠምዛዥ እና አዛዥ ናዛዦቹ ጀንበር መጥለቅ አይቀሬ መሆኑን ነጋሪ ሆኗል። የቀጣናው ትልቅ ሀገር ኢትዮጵያ የዚህ ስበት ማዕከል መሆኗ ሳይታለም የተፈታ ነውና አሁናዊ ተጋድሎዋ ከቀንዱ አውድ ተለይቶ ሊታሰብ አይችልም።

## ምኞት አይከለከልም

ኢትዮጵያ ያላት የመልማት እምቅ አቅም እንዲሁም እየጨመረ የመጣው በምስራቅ አፍሪካ ያላት ተሰሚነት ስጋት ውስጥ እየከተታቸው፤ በሌሎች ሀገራት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ባለመግባት በምታራምደው የገለልተኝነት አቋም እና በዓለም አቀፍ ሰላምና ጸጥታ ጉዳዮች ላይ አውንታዊ ሚና በመጫወት የምታበረክተውን አስተዋጽኦ ተመልክተው "ይህች ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም" በሚል ጥርሳቸውን የነከሱባት አንዳንድ ኃያላን ሀገራት አሉ። የዛሬ አያያዟን አይተው የነገ ተስፋዋ እያስፈራቸው፤ እንደ እምቢኝ አልገዛም ባይነቷ ሁሉ በራስ እግር መቆምንም በተግባር ለቀረው አፍሪካ አሳይታ ታላቢ ላሞቻችንን ከጉያችን ትነጥቅብናለች የሚል ስጋት ገብቷቸው ከጉዞዋ ሊያሰናክሏት ጠዋት ማታ የሚዶሉቱባትና በተደራጀ መንገድ ባለ በሌለ ኃይላቸው የሚዘምቱባት በዝተዋል። እነዚህ አካላት በብዙዎች ዘንድ የአፍሪካ የነጻነት ጸሐይ የወጣባት ምድር ተደርጋ የምትቆጠረው ይህች የአፍሪካ ቀንድ ቀንደኛ ታላቅ ሀገር ችግር ውስጥ ገብታለች ብለው ባሰቡ ቁጥር ከታሪካዊ ጠላቶቿ ጋር በማበር ሊበታትኗት ይመኛሉ፤ ምኞት አይከለከልም።

አንዳንድ ምዕራባውያን ሀገራት እና ድርጅቶች በተቀናጀ መንገድ ተደጋጋሚ ጫናዎች ሲያደርሱባት ቆይተዋል። አሜሪካዊው የፖለቲካና ኢኮኖሚ ተንታኝ ላውረንስ ፍሪማን ከኢዜአ ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት የተወሰኑ ምዕራባውያን አፍሪካን በቁጥጥራቸው ስር አድርገው እንደፈለጉ የማዘዝ ፍላጎታቸው ከፍተኛ ነው። በአህጉሪቱ ጠንካራ መንግስትና ሀገር እንዳይኖር እየሰሩ ስለመሆኑ ጠቁመው በሰሜን ኢትዮጵያ ያለውን ግጭት በማባባስ ደካማ ሀገር የመፍጠር እቅድ ይዘው እየሰሩ መሆኑን ተናግረው ነበር።

መንግስት የሀገር ሉዓላዊነትን ለማጽናት በትግራይ ክልል ቁልፍ ከተሞችን እየተቆጣጠረ በመጣ ወቅትም አንዳንድ ምዕራባውያን በመንግስት ኃላፊዎቻቸው፣ በተቋማትና በሚዲያዎቻቸው የተናበበ ጫና ሲፈጥሩ ቆይተዋል። በእነዚሁ አካላት በኢትዮጵያ ላይ እየተደረገ ያለው ጫና ለእነሱ የሚላላክ መንግስት ለመፍጠር ካላቸው የረጅም ጊዜ እቅድ የሚቀዳ ስለመሆኑም ተንታኙ ይገልጻሉ፤ ምኞት አይከለከልም።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን የኤክስፐርቶች ቡድን ከሁለት ዓመታት በፊት በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የተቀሰቀሰውን ጦርነት ተከትሎ በሁሉም ወገኖች የተፈጸሙ የመብት ጥሰቶችን የሚያሳይ ማስረጃ ማግኘቱን ጠቅሶ ሪፖርቱ በማውጣት ኢትዮጵያ ላይ ፖለቲካዊ ተልዕኮ ያነገበ ጫና ለመፍጠር ተንቀሳቅሷል። በሪፖርቱ "የኢትዮጵያ ሰራዊት በትግራይ ክልል በነበረባቸው ጊዜያቶች ሰላማዊ ዜጎች ላይ ግድያዎች መፈጸሙን መረጃ አግኝቻለው" ያለው ተቋሙ፤ በተጨማሪም "ረሃብን እና መድሃኒቶችን መከልከል እንደ ጦር መሳሪያነት ጥቅም ላይ እየዋለ ስለመሆኑ የሚያሳዩ መረጃዎችም አሉ" በማለት የጸጥታው ምክር ቤት ኢትዮጵያ ላይ ጠንካራ እርምጃ እንዲወስድ በመፈለግ ግፊት አድርጎ ነበር። መቼስ ምኞት አይከለከል። ነገር ግን ዕድሜ ለእንቁ ዲፕሎማቶቿ እና ወዳጅ ሀገራት የጸጥታው ምክር ቤት በጉዳዩ ላይ አንዳች አቋም ለመያዝ ተቸግሮ ያለስምምነት ተበትኗል።

እጇን ጠምዝዘን ለፍላጎታችን እናንበረክካታለን በሚል ከማዕቀብ መጣል እስከ ብድር ክልከላ እና የእዳ መክፈያ ጊዜን ላለማራዘም ዳተኛ እስከመሆን የደረሱ ደባዎች ኢትዮጵያ ላይ ተፈጽመዋል። የጸጥታው ምክር ቤት የኢትዮጵያን ሁኔታ አጀንዳ አድርጎ እንዲነጋገርበት ተደጋጋሚ ጥረቶች ተደርገዋል። ማስፈራሪያና ዛቻዎች ሲዥጎደጎዱ ቆይተዋል። ከፍተኛ በጀት ተመድቦ ትልቅ ስም ባላቸው ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች የኢትዮጵያን ስም የሚያጠለሹ ዘገባዎች በዘመቻ መልክ እንዲስተጋቡ ተደርጓል። የአውሮፓ ህብረት የአንድን ሀገር ሉዋላዊነት የሚጋፉ አቋሞችን አራምዷል፤ ተራ ስም የማጥፋት ተግባር እንኳን አልቀረም። በኢትዮጵያ የአውሮፓ ኅብረት ጽሕፈት ቤት ከሳምንታት በፊት በፌስቡክ ገጹ ላይ የኢትዮጵያና ኤርትራ መንግሥታት በትግራይ የዘር ማጥፋት ጦርነት እያፋፋሙ ቀጥለዋል የሚል ይዘት ያለውን የአንድ ግለሰብ የፌስቡክ መልዕክት አጋርቶ ምኞቱን ተንፍሷል። በኋላም ከአንድ አህጉር አቀፍ ድርጅት ንዑስ ጽህፈት ቤት የማይጠበቅ ተራ ፕሮፖጋንዳ መስተጋባቱን ተከትሎ በተነሳ የተቃውሞ ማእበል ከግማሽ ሰዓት ላነሰ ጊዜ የቆየውን ልጥፍ በማንሳት ይቅርታ ለመጠየቅ ተገዷል። በፌስቡክ ገጹ የተጋራው የአንድ ግለሰብ የፌስቡክ መልዕክት የኅብረቱ እውቅና የሌለው መሆኑን ገልጦ አስተባብሏል። አይኑን በጨው

አጥቦም "የግለሰቡ መልዕክት የተጋራው የፌስቡክ ገጼ ተጠልፎ ስለነበር ነው"ብሏል።

ይህ ሁሉ ጉራማይሌ ማዋከብ ኢትዮጵያን ከተያያዘችው የብልጽግና ጉዞ ጠልፎ ለማስቀረት ካለ ፍላጎት የሚቀዳ ምኞት የወለደው መተራመስ ነው። ኢትዮጵያ ግን ወጀቡን እየቀዘፈች ጉዞዋን ቀጥላለች። ምድሯ ላይ ላለው ስጋ የሚፋለሙት የሰማይ አሞራዎችና ታሪካዊ ጠላቶቿ ደግሞ የማይነጋ ህልም ማለማቸውን ቀጥለዋል።

## አንገት ከሚሰበር ...

ድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) በአንድ ሙዚቃው ሆድ ከክብር እና ነጻነት በላይ አለመሆኑን ሲገልጽ "አንገት ከሚሰበር ባይበላስ ቢቀር" ሲል ተቀኝቷል። ኢትዮጵያም ፍርፋሪ ለማግኘት ስትል ክብሯን እንደማትጥልና በነጻነቷ እንደማትደራደር ኢትዮጵያዊ ወኔን በተሞሉ ቃላት በመግለጽ "ባይበላስ ቢቀር" ያለችባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት አጣሪ ኮሚሽን የሰሜን ኢትዮጵያን ጦርነት በማስመልከት ያወጣውን ሪፖርት ቆፍጠን ያለ አቋም በመያዝ ውድቅ አድርጋዋለች። መጀመሪያም ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የሰብአዊ መብት ኮሚሽን እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብዓዊ መብት ቢሮ ምርመራ ግኝት እያለ ሌላ አጣሪ ኮሚሽን መቋቋሙ ፖለቲካዊ ዓላማ ያነገበ ነው ስትል ተቃውሟ ነበር። በጄኔቭ የተባበሩት መንግስታት የኢትዮጵያ ቋሚ መልእክተኛ አምባሳደር ዘንበ ከበደ፤ የተመድ የሰብአዊ መብት አጣሪ ኮሚሽን ያወጣውን ሪፖርት ፖለቲካዊ አላማን የያዘ ነው ሲሉ አጣጥለውታል። የሰብአዊ መብት አጣሪ ኮሚሽኑ ያወጣው ሪፖርት ድምዳሜዎች እርስ በእርሳቸው የሚጣረሱ እና ወገንተኛነት ያለበት መሆኑን ለኤ.ኤፍ.ፒ ተናግረዋል። የኢትዮጵያ መንግስት ሰብአዊ እርዳታን እንደ ጦር መሳሪያ መጠቀሙን የሚያሳይ አንድም ማስረጃ በሪፖርቱ አልቀረበም። ሪፖርቱ ፌዝ እና የማይረባ ስለሆነ ውድቅ ከማድረግ ውጭ ሌላ አማራጭ እንደሌለን እወቁት ብለዋል። የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሄራዊ ደህንነት አማካሪ አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን በበኩላቸው በትዊተር ገጻቸው ባጋሩት ጽሁፍ ኢትዮጵያን ዝቅ የማድረግ ፖለቲካዊ ስራ ውጤት ነው ሲሉ የነቀፉትን ሪፖርት የመወንጀል አላማ ያለው፤ እርስ በእርሱ የሚጣረስ እና ተዓማኒነት የሌለው ነው ሲሉ ገልጸውታል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጥቅምት 18 ቀን 2015 ዓ.ም "ኃላፊነት የጎደላቸው አካላት ለአደገኛ የፖለቲካ አጀንዳ ሲባል እየፈጠሯቸው የሚገኙ መሠረተ ቢስ ውንጀላዎችን ኢትዮጵያ ታወግዛለች" በማለት ባወጣው መግለጫ እጃችሁን ከኢትዮጵያ ላይ አንሱ ሲል ጠንካራ መልዕክት አስተላልፏል። መግለጫው በምዕራባውያንና የተለያዩ አካላት አማካኝነት በኢትዮጵያ ላይ የሚነዙ የሐሰት ስም ማጥፋቶችን የኢትዮጵያ መንግሥት ፈጽሞ አይታገሥም። እነዚህ አካላት ኢትዮጵያ ውስጥ የከፉ ወንጀሎች ሊፈጸሙ ይችላሉ በሚል የታሪካዊ ጠላቶቻችን ጊዜ ያለፈበት ፕሮፓጋንዳ እንደ በቀቀን መድገማቸው አሳፋሪ ነው። እነዚህ አካላት የሚከሱት ፍንጮችን ወይም ተጨባጭ ክስተቶችን መሠረት አድርገው አይደለም፤ የመፈጸም ዕድል አለ በሚል ያልተጨበጠ ግምት እንጂ። እጅግ የሚያሳዝነው ደግሞ የተሻለ ስም ያላቸው ተቋማት ሳይቀሩ ይሄንን በኢትዮጵያ ላይ ተቀነባብሮ የሚለቀቅ ፕሮፓጋንዳ ለመቃወም አለመቻላቸው ነው። ጥቂቶቹም ስለ ኢትዮጵያ የተነገረውን ስም ማጥፋት በማመን ሳይሞኙ እንዳልቀሩ ይገመታል። አንዳንዶችም እነዚህን የሐሰት ክሶች ኢትዮጵያን ለማንበርከክ ሊጠቀሙባቸው ይፈልጋሉ ሲል ወቅሷል።

አንዳንድ ምዕራባውያን ባለሥልጣናት ጭምር ይሄንን የሐሰት ክስ የሚነዙት ኢትዮጵያ ትእዛዛቸውን አልቀበል ስላለቻቸው መሆኑን በይፋ መናገር ጀምረው ነበር። ይህ ጊዜ አመጣሽ የሐሰት ክስ መሬት ላይ ያለውን እውነታ ጨርሶ አይቀይረውም። እነዚህ ጉምቱ ተቋማትና ወሳኝ ተዋንያን፣ በቂ ግንዛቤ ሳይኖራቸው በዚህ የሃሰት ዘመቻ ተሳትፈዋል። ይሄን የመሰሉ የከፉና ሊወገዙ የሚገባቸው ውንጀላዎች ለፖለቲካ ዓላማ መዋላቸው ኃላፊነት የጎደለውና አሳፋሪ ነው በማለትም ኢትዮጵያ ለምንም አይነት ጫና እንደማትንበረከክ መንግስት ግልፅ አድርጓል።

ብዙዎችን ያስገረመውና የኢትዮጵያን አትንኩኝ ባይነት እና ለነጻነቷ ምንም አይነት ዋጋ ለመክፈል ያላትን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው የተባለለት ሌባ ጣትን በማወዛወዝ የተነገረ ያህል በኃይለቃል የተመላው ደግሞ የመግለጫው መቋጫ ክፍል ነው። እንዲህ ይነበባል "ይሄንን ለመሰለው አደገኛ ስም ማጥፋት ምላሽ ሳይሰጡ ታግሦ ማለፍ የሚቻል ባለመሆኑ በከፋ መልኩ በኢትዮጵያ ላይ ያልተረጋገጡና ፖለቲካዊ ዓላማ ያላቸውን ውንጀላዎች ከሚያቀርቡ ከአንዳንድ ሀገሮችና ተቋማት ጋር ያለውን ግንኙነት የኢትዮጵያ መንግሥት መልሶ እንዲያጤን ተገድዷል። የኢትዮጵያ መንግሥት ከመነሻውም በግልፅ እንዳሳወቀው በአፍሪካ ኅብረት በኩል እየተደረገ ላለው የሰላም ንግግር ቁርጠኛ ነው። ምክንያቱም ግጭቱን በሰላማዊና ቋሚ በሆነ መንገድ ለመፍታት የጸና አቋም አለውና። በሌላም በኩል በግጭቱ ምክንያት የተከሡቱ የሰብአዊ መብትና የሰብአዊነት ጥሰቶችን ተጠያቂ ለማድረግ ቁርጠኛ መሆኑን ለመግለጥ ይወዳል።"

እንዲህ ያለ የምዕራባውያኑን ደም የሚያንተከትክ ቆምጨጭ ያለ መግለጫ በአፍሪካ ምድር ሊደመጥ የሚችለው ከአፍሪካ ቀንዷ ቀንደኛ ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ ነው። ጉልበተኞቹን እንደ ቻይና እና ሩሲያ አሊያም እንደ ኢራን እና ሰሜን ኮሪያ ለመቋቋም የምትደፍር አንድ ለእናቷ አፍሪካዊት ሀገር የአድዋ ድል ወላጅ እናት ብቻ ናት።

ኢትዮጵያዊነት መልኩ ብዙ፣ ሰይፉ ህልቆ መሳፍርት ነው። በመላው ዓለም የሚገኙ 17 የዳያስፖራ አደረጃጀቶች ጥምረት አባላት በውይይቱ ውጤት ላይ ያልተገባ ጫና ለመፍጠር የሚሞክሩ

አካላትን ተግባር በገዛ ምድራቸው ላይ ቆመው በመቃወም የሀገራቸውን ድፍረት ደግመውታል። የጥምረቱ አባላት ባወጡት መግለጫ ህጋዊ የሆነው የኢትዮጵያ መንግስት በደቡብ አፍሪካ የተካሄደውን ውይይት ጨምሮ እያከናወናቸው ባሉ ተግባራት ላይ አንዳንድ ሀገራት የሚፈጥሩትን ያልተገባ ጫና እንቃወማለን። በኢትዮጵያም ሆነ በቀጣናው ሰላም እንዲሰፍን የውይይት ፋይዳ ከፍተኛ ስለሆነ ጸብአጫሪ እጃችሁን ሰብስቡልን ሲሉ ጠይቀዋል። የውይይቱን ውጤት ለመቀየር የሚደረጉ ማናቸውንም አይነት ጫናዎች እንደሚቃወሙ ገልጸው፣ የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ከግጭት ለመውጣት የሚያደርጉትን ጥረት በምንችለው ሁሉ ለመደገፍ ሁልጊዜም ዝግጁ ነን ብለዋል።

ኢትዮጵያ “ባይበላስ ቢቀር” ብላ ጦም ማደርን ብቻ አልመረጠችም። ኢትዮጵያ እስከዛሬ ከውጪ የስንዴ ምርትን ለማስገባት እስከ 1 ቢሊዮን ዶላር ድረስ ስታወጣ የቆየች ሲሆን በዚህ ዓመት ግን በቂ ምርት በማምረትዋ የውጭ ምንዛሬውን ሙሉ በሙሉ ማስቀረት ችላለች። የስንዴ ፍላጎቷን በአገር ውስጥ ምርት ከመሸፈን አልፋ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ሰፊ የመኸር እና የመስኖ ልማት እያካሄደች ትገኛለች። በመኸር እርሻው 13 ነጥብ 37 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር የተሸፈነ ሲሆን ከዚህም 400 ሚሊዮን ኩንታል የተለያዩ ዝርያ ያላቸውን ምርጥ ዘሮች ለማግኘት እየተሰራ ነው። በአሁኑ ጊዜ የምርት ስብሰባ ሂደቱ በተለያዩ አካባቢዎች ተጀምሯል። 1ሺህ 500 ኮምባይነሮች ምርት ለመሰብሰብ ተሰማርተዋል። በመኸር እርሻ ወቅት በዘር ከተሸፈነው 13 ነጥብ 37 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ 2 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሄክታሩ የስንዴ ምርት ነው። ከዚህም 108 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይገኛል።

በበጋ የመስኖ ልማት ስራ 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በስንዴ እንደሚለማ የግብርና ሚኒስቴር ገልጿል። በበጋው ወራት በዘር ከሚሸፈነው 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት 52 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዷል። ይህ የበጋ የስንዴ ልማት ስራም በዘጠኝ ክልሎች የሚከናወን ነው። መንግስት ከውጭ የሚገባውን ስንዴ በማስቀረትና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ትኩረት ሰጥቶ መስራቱ ለውጤቱ መገኘት ጉልህ ድርሻ አበርክቷል። ኢትዮጵያ በስንዴ ምርት እያስመዘገበች ያለችው ውጤት አፍሪካ በምግብ እህል እራሷን ከመቻል አልፋ ለሌሎች መትረፍ እንደምትችል የሚያሳይ ነው። ኢትዮጵያ በስንዴ ላይ ያገኘችውን ውጤት በሌሎች የምግብ ሰብሎች፣ ፍራፍሬዎች እና የእንስሳት ተዋጽኦዎች ላይም መድገም ከቻለች አንገት ሳይሰበር ሆድም ጦም ሳያድር ወደ ነበረችበት ማማ ለመመለስ የጀመረችው ጉዞ ይበልጥ ይፋጠናል።

## ጣታ ነው ጸሌ

አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ ጥቅምት 17 ቀን 2015 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር በተጠራው 77ኛው የተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ ኢትዮጵያ ላይ ለቀረበው የሀሰት ውንጀላ በሰጡት ግሩም መልስ የሀገራቸውን ፈርጣማ

> **በርካታ ችግሮቻችንን ተጋፍጠን እንዳለፍናቸው ሁሉ፣ ዛሬም የገጠሙንን ችግሮች በእርግጠኝነት እንሻገራቸዋለን**

አቋም በተዋቡ ቃላት ገልጸዋል። አምባሳደሩ ሴረኞችን ገስጸው ወዳጅ ሀገራትን ባመሰገኑበት ንግግራቸው ኢትዮጵያ እንደትናንቱ ሁሉ ዛሬም ከገጠሟት ችግሮች በላይ እንደምትሆን በማስረገጥ የድሉን ችቦ ቀድመው ለኩሰዋል። አምባሳደር ታዬ በዕለቱ ያደረጉት አጭር ንግግር ተከታዩ ነው።

“እየሰማን ያለነው የሰላም መልእክት ሳይሆን ተከታታይ ማስጠንቀቂያዎችን ነው። ነገር ግን በርካታ የፖለቲካ ምስቅልቅሎችን ማለፍ እንደቻለች ኩሩ አፍሪካዊት ሀገር አባል ሀገራትን አንድ ነገር ማስታወስ እፈልጋለሁ። በርካታ ችግሮቻችንን ተጋፍጠን እንዳለፍናቸው ሁሉ፣ ዛሬም የገጠሙንን ችግሮች በእርግጠኝነት እንሻገራቸዋለን። በአንዳንድ ኃያላን ሀገሮች ዐይን ፊት ልክ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት እንደሆነው ዐቅመ ቢስ መስለን እንታይ ይሆናል። ክቡር ሊቀመንበር፤ አንድ ነገር ግን ላረጋግጥልዎት እወዳለሁ። የውስጣችን መንፈስ ጽኑ ነው። የውስጣዊ መንፈሳችን ጥንካሬ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ለመቆም ብቻ ሳይሆን ሰላማዊ ለመሆን እና ተግዳሮቶቻችንን ለመፍታትም ጭምር ነው። የ120 ሚሊዮን ሕዝባችንን ዕድል ለ200 ኤክስፐርቶች ልንተወው አንችልም። ይህንን ብዬ፤ ሁልጊዜም ቢሆን በጎ ሀሳብ ያላቸውን ተሳታፊዎች በደስታ የምንቀበል ሲሆን ሊያወግዙን እና ለሞት አሳልፈው ሊሰጡን ቀድመው የወሰኑትን ግን “የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር ይበላቸው” እላለሁ። ስለዚህ እንደ መንግሥት ላረጋግጥላችሁ የምፈልገው ሁሉም የሰብአዊ መብት ጥሰት ላይ የተሳተፉትን ተጠያቂ እናደርጋቸዋለን። ይህንንም የምናደርገው የተወሰኑ ድርጅቶችን ወይም ኤክስፐርቶችን ለማስደሰት ሳይሆን ለራሳችን መርህ ስንል ነው። ዘላቂ ሰላም መስፈን የሚችለው በሁሉም አካባቢዎች ለተሠሩ ወንጀሎች ተጠያቂነት እና ፍትህ ሲሰፍን ብቻ መሆኑን እንረዳለን። ነገር ግን ይህ በሀገሪቱ ባለቤትነት መመራት አለበት።”

የማታ ማታ አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ አስረግጠው የተናገሩት ነገር እውን ሆነ። የአድዋዋ ንግስት ተጋድሎዋን በለመደችው ድል ደምድማ የተጋዳሊዎቿን ቅስም ሰባብራ እብሪታቸውን ቀብራለች። ረቡዕ ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም. በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ፣ በኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት እና በሕወሓት መሪዎች መካከል ሲካሄድ የነበረው ድርድር ተጠናቅቆ ከስምምነት ላይ መድረሳቸው ተበሰረ። ለአስር ቀናት ያህል ሲካሄድ በቆየው ድርድር ማብቂያ ላይ የተፈረመው ባለ 12 ነጥብ ስምምነት በዘላቂነት ግጭት ማቆም፣ የሕወሓት ታጣቂዎችን ትጥቅ ማስፈታት እና የሰብዓዊ እርዳታ ማድረስ የሚሉ ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮች ተካተዋል። ሕወሓት እና መንግሥት ስምምነቱን ለማብሰር በተሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ በጋራ ሆነው “ግጭቱ ከፍተኛ ሰብዓዊ እና ቁሳዊ ኪሳራዎችን አስከትሏል። በዘላቂነት ግጭት ለማቆም መስማማታችንን የኢትዮጵያ ሕዝብ እና ዓለም ይወቅልን። የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም ከግምት በማስገባት ግጭቱን ምዕራፍ ከኋላችን ትተን በሰላም እና በመቻቻል ለመኖር ተስማምተናል” ሲሉ ተደምጠዋል። ኢትዮጵያ

ያሸነፈችባትና ታሪካዊ ጠላቶቿ አንገታቸውን የደፉበት ይህ የሰላም ስምምነት አፍሪካውያን ችግሮቻቸውን በራሳቸው መፍታት እንደሚችሉ አሳይቷል። ስምምነቱ የኢትዮጵያን ሰላም የማይሹ ቡድኖችን ሴራ አክሽፎ ለዘላቂ ሰላም ዕድል ሰጥቷል።

ኢትዮጵያን በመወከል በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የተሰየመው ልዑክ አባል የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሄራዊ ደህንነት አማካሪ ሚኒስትር አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ስምምነቱን ከፈረሙ ከሰዓታት በኋላ  በትዊተር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት ዕለቱን የገለጹት "የዛሬው ቀን ኢትዮጵያና ሰላም ድል ያደረጉበት ነው" በማለት ነበር። "ለሁሉም ኢትዮጵያውያንና ወዳጆች እንኳን ደስ አላችሁ፤ እኔ ልገልጸው የማልችለው ደስታ ተሰምቶኛል" ሲሉም የሰላም ስምምነቱ በመፈረሙ የተሰማቸውን ልባዊ ደስታ ብዙዎች ላይ አጋብተዋል። አምባሳደሩ እንኳን ደስ አላችሁ ያሉት ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ወዳጆን ጭምር ነውና ለቃሉ የሚመጥኑት የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ወዳጅ ሀገራትና ተቋማት አጸፋውን ለመመለስ ጊዜ አልወሰደባቸውም።

የአፍሪካ ሕብረት ኮሚሽነር ሙሳ ፋቂ ማህማት በአፍሪካ ሕብረት አማካኝነት ሲካሄድ በነበረው የሰላም ውይይት የግጭት ማቆም ስምምነት ለተፈራረሙት ወገኖች አድናቆታቸውን ገልጸው፣ የአፍሪካ ህብረት ለኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም መረጋገጥ የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል። በአዲስ አበባ የሩሲያ ኤምባሲ ባወጣው መግለጫ በፌደራል መንግስትና ሕወሓት መካከል የተፈረመው ስምምነት መላው ኢትዮጵያውያን ሰላምን አረጋጥጠው ብልጽግናን እንዲያገኙና የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለማቋቋም ጠንካራ መሰረት የሚጥል እንደሆነ አመልክቷል። በኢትዮጵያ የቻይና አምባሳደር ዣኦ ዠዩዋን በትዊተር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት ቻይና በፌደራል መንግስትና ሕወሓት መካከል ለተፈረመው የሰላም ስምምነት ያላትን አድናቆት ገልጸው፣ ሀገራቸው በአፍሪካ ሕብረት ጥላ ስር የተደረሰውን ስምምነት በበጎ እንደምትቀበለው ጽፈዋል። ሌሎች ወዳጅ ሀገራትና ተቋማትም ደስታቸውን ገልጸዋል። ኢትዮጵያ ዛሬም እንደ ቀድሞ ሁሉ የገጠማትን ችግር ትሻገራለች በማለት የማታ ማታ ኢትዮጵያ አሸናፊ መሆኗ እንደማይቀር ቀድመው የተናገሩት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴም "ሰላም የኢትዮጵውያን የአይበገሬነት ውጤት መሆኑ በድጋሚ ታይቷል" በማለት በኩራት ተናግረዋል።

## ፍቅር እንደገና

የሰላም ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላ ትናንት ኢትዮጵያን ከግራ ከቀኝ ወጥረው ይዘዋት ከፍተኛ ጫና በማድረግ ሲያስጨንቋት የነበሩ አካላት በሚያስገርም ፍጥነት 360 ዲግሪ ተከርብተው ቀና አሳቢና ተቆርቋሪ ሆነው ተከስተዋል። "አጥበቀን ስንሻው የነበረው" የኢትዮጵያ ሰላምና የግዛት አንድነት በመረጋገጡ ደስ ብሎናል እንኳን ደስ አላችሁ፤ ከጎናችሁ ነን የሚሉ የደስታ መግለጫዎችን አዥጎድጉደዋል።

የአውሮፓ ሕብረት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ቻርለስ ሚሸል ቻርለስ ሚሸል በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት ጽሑፍ የኢፌዲሪ መንግሥት እና ሕወሓት በአፍሪካ ህብረት አማካኝነት ባካሄዱት የሰላም ንግግር ስምምነት ላይ በመድረሳቸው መደሰታቸውን ገልጸው፤ የአውሮፓ ሕብረት በቀጣይ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ጠቁመዋል። የአውሮፓ ሕብረት የአፍሪካ ቀንድ ልዩ ተወካይ አኔት ዌበር በበኩላቸው በተደረሰው ስምምነት የተሰማቸውን ደስታ ገልጸው፣ ስምምነቱ አበረታች እርምጃ ነው ብለዋል።

የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከንም ዘግየት ብለው በሰጡት ምላሽ በአፍሪካ ህብረት አማካኝነት በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ሲካሔድ የቆየው የኢፌዴሪ መንግስትና ሕወሓት የሰላም ውይይት በስኬት በመጠናቀቁ አድናቆታቸውን ገልጸዋል። የጦር መሳሪያ ድምፆችን በማስቆም የሰብዓዊ እርዳታና መልሶ መቋቋም ስራውን ለማከናወን በሚደረገው ቀጣይ ስራም ከአፍሪካ ህብረት ጎን በመሆን አሜሪካ ድጋፏን እንደምታጠናክር አረጋግጠዋል።

አይኤምኤፍ (IMF) በኢትዮጵያ የሰላም ስምምነት መደረጉን ተከትሎ ቀጣይ ፈንድ ለመልቀቅ እያሰበ መሆኑን አስታውቋል። ብሉምበርግ እንደዘገበው የድርጅቱ የፈንድ ጉዳይን የሚከታተሉ ባለሙያዎች ከኢትዮጵያ ባለስልጣናት ጋር ውይይት እያደረጉ መቆየታቸውን አስታውሷል። ተቋሙ "ቀጣይ እርምጃዎችን እያሰብን ሲሆን ከኢትዮጵያ ባለስልጣናት ጋር እንወያያለን" ብሏል።

## መውጫ

ኢትዮጵያ የተፈተነችባቸውና ውስጡም ውጪውም እሳት ያደራባቸው ያለፉት ሁለት አመታት መንግስቷ፣ ዜጎቿ እና በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያያን ባደረጉት ተጋድሎ ላይ የወዳጅ ሀገራት አስተጽኦ ታክሎበት በድል ተደምድሟል። ድሉ ኢትዮጵያ በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ላይ የተቀዳጅውና ለአፍሪካውያን ዳግም ምሳሌ የሆነችበት ታሪካዊ ድል በመሆኑ የዘመናችን አድዋ ነው። ኢትዮጵያውያን በጋራ ከቆምን የትኛውንም አይነት ተግዳሮት መግዳደር የሚያስችል አቅም እንዳለን የታየበት ነው። ልዩነቶቻችንን በንግግር እየፈታን አንድነታችንን ካፀናን ታሪካዊ ጠላቶቻችን እንኳን ወዳጅ ከመሆን ውጪ ምርጫ አይኖራቸውም። ይህንን አንድነታችንን ሰላምን ለዘለቄታው በማስፈን የጀመርነውን የብልጽግና መንገድ አጠናክረን

**በበጋው ወራት በዘር ከሚሸፈነው 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት 52 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዷል**

በመቀጠል ወደነበርንበት የከፍታ ማማ ለመመለስ ልንጠቀምበት ይገባል። ጽሑፌን በአፍሪካ ሕብረት የአፍሪካ ቀንድ ልዩ ልዑክ ኦሊሴጉን ኦባሳንጆ የሰላም ስምምነቱ በተበሰረበት ቀን ካደረጉት ንግግር በተወሰደ ዓረፍተ ነገር ልቋጭ፤ "ኢትዮጵያ ትልቅ አገር ናት፣ ትልቅ እንደሆነች መቀጠል ይኖርባታል"።

በዚህ ዓምድ ስር የሚስተናገዱ ጽሁፎች የፀሀፊውን አመለካከት እንጂ የዝግጅት ክፍሉን አቋም አይወክሉም

# አልገፋ ያለው ዳገት

**ስሜነህ ደስታ**

አብሮ አደግ ወዳጄ ተክዞ አገኘሁትና ‹‹ምን ሆነህ ነው? ›› ብዬ ጠየኩት። ‹‹ሁለት ወይም ሶስት ሆነው ባሉበት የኑሮ ውድነት ወሬ በሰፊው ይነሳል ሲባል ሰምተህ ታውቃለህ ወይ? ›› በማለት ጥያቄውን በጥያቄ መለሰልኝ። ‹‹ሰምቼ አላውቅም›› አልኩት። ‹‹አንተ እሱን ሳትሰማ፣ የኑሮ ውድነቱ አንድን ሰው ብቻውን እንዲናገር ማድረግ ደረጃ ደርሷል! ›› አለኝ።

ወዳጄ እውነት አለው። የኑሮ ውድነቱ ያልነካው የህብረተሰብ ክፍል የለም ማለት ይቻላል። በተለይ ዕለት በዕለት በምንጠቀምባቸው ሸቀጦች ላይ የሚታየው የዋጋ ንረት የትየለሌ ነው። ለምሳሌ የሾላ ወተትን እንመልከት ግማሽ ሊትሩ አስር ብር ሲሸጥ ቆይቶ አስራ ሁለት ብር ገባ። ከዚያ 15፣ 18፣ 20 እያለ አሁን 25 እና ከዚያ በላይ እየተሸጠ ይገኛል (ይሄ ጽሑፍ ታትሞ እስኪወጣ ድረስ ዋጋው ከ40 በላይ እንዳይሆን ምን የሚያግደው ነገር ይኖራል?)። ሌሎቹማ ወተቶች ዋጋቸው የሚደመጥ እንጂ የሚሸመት አልሆነም። ድፍን ምስር አንድ ኪሎ 120 ብር ሲሸጥ ቆይቶ 130፣140፣150፣160 እያለ አሁን ዋጋው ነጋዴው በወሰነው ሆኗል። ጠዋት 160 ተገዝቶ ማታ እዚያው ቦታ ለመግዛት ሲኬድ 170 ይባላል። አቅሙ ካለ መግዛት፤ ከሌለ ትቶ መሄድ እንጂ አቤት ቢባል ጉዳዩን በጥልቀት አይቶ መፍትሔ የሚሰጥ አካል የለም።

ይሄም ስለሆነ ነጋዴው በዋጋው ላይ እንደፈለገው ያዛል። እንዲሁም የሚሸጠውን ሸቀጥ በማከማቸት ዋጋው በከፍተኛ ሁኔታ እንዲንር ያደርጋል። ከዚህ አንጻር ዘይት ላይ የተሠራውን ስንመለከት አምስት ሊትር ፈሳሽ ዘይት ሶስት መቶ ብር ይሸጥ ነበር። ነጋዴዎች ከገበያ ለዐይን እንኳን እንዲጠፋ አድርገው በኋላ ላይ አንድ ሺህ ብር እና ከዚያም በላይ በሆነ ዋጋ ሸጠዋል።

ዘይት ላይ የተደረገውን ብቻ ሳይሆን በሌሎች ምርቶች ላይ ያለውንም መጥቀስ ይቻላል። የሲሚንቶ ዋጋ መሸጥ ከሚገባው ከሶስት እጥፍ በላይ መሸጡ የአደባባይ ምስጢር ነው። አንድ ቤት የሚሠራ ሰው መደበኛውን ሂደት በመከተል ሲሚንቶ ማግኘት ፈተና ቢሆንበት አማራጭ ባገኝ ብሎ ደላላ ጋር ሲደውል “አሁን መግዛት ትችላለህ መኪና ላይ ሲሚንቶው ተጭኖ ገዢ እየጠበቀ ነው” ብሎ ቀለል አድርጎ በነገረው መሰረት ተደራድሮ የሚችለውን ያህል መጠን በመውሰድ ችግሩን አቃሏል። በመደበኛ አካሄድ ማግኘት እንዳይቻል ችግር የሚፈጥረው ማን ነው? ችግሩስ እንዴት ይፈታል? በሚል ትኩረት ሰጥቶ ከልብ የሚሠራ አካል ባለመኖሩ ችግሩን የሚፈጥሩት አካላት በድርጊታቸው ገፍተውበታል።

አንዳንድ ጊዜ “ችግሩን ለማቅለል ይሄን የመሰለ የመፍትሔ አካሄድ ተከትለናል” ተብሎ በተነገረ በጥቂት ቀናት ውስጥ ያው ችግር መልኩን ቀይሮ በሌላ መንገድ ይገለጻል። ይሄን በሲሚንቶ ንግድ ላይ በስፋት ለማስተዋል ተችሏል። ስለኑሮ ውድነቱ አስከፊነት ማሳያ ለማቅረብ የቱ ተነስቶ፣ የትኛው ይቀራል በሚል ለመምረጥ ይቸግራል። በዚህ የኑሮ ውድነት የተነሳ ከአምስት ዓመት በፊት ትዳር ይዘው ከቤተሰባቸው የወጡ ወጣቶች ትዳሩን ማስቀጠል ስላቃታቸው አሁን ሁለት ልጆቻቸውን እንደ ዕቃ ተካፍለው ወደ ቤተሰቦቻቸው ቤት መመለሳቸውን አውቃለሁ። መጀመሪያ ተፋተው መስሎኝ ነበር፤ በኋላ ባልየው ሲያስረዳኝ ተፋተው ሳይሆን ቢያንስ የቤት ኪራይ ወጪ ለማዳን ያደረጉት ዘዴ እንደሆነ ነገረኝ።

የዋጋ ግሽበትና የማኅበረሰቡ የመግዛት አቅም ማነስ የፈጠረው የኑሮ ውድነት ባለፉት ሦስትና አራት ዓመታት ዕድገቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መጥቶ አሁን እንደሚታየው ለመቆጣጠር በሚያስቸግር ደረጃ ደርሷል። ስለሆነም አፋጣኝ መፍትሔ ያስፈልገዋል። የኑሮ ውድነቱን የሚመጥን መፍትሔ ለመስጠት በዋናነት መንግሥት የአንበሳውን ድርሻ መውሰድ አለበት። መንግሥት ኃላፊነቱን በመወጣት መቅደም አለበት እንጂ ሌሎችም የኅብረተሰብ ክፍሎች እንደድርሻቸው ኃላፊነት ወስደው መሥራት ይገባቸዋል።

መንግስት የኑሮ ውድነቱን ለመቀነስ የተለያዩ ጥረቶች አድርጓል። ነገር ግን የውስጥ እና የውጭ ተጽዕኖዎች በፈጠሩት ጫና ዘላቂ መፍትሔ ባለማምጣቱ ሕዝቡ ሊቋቋመው ከሚችለው በላይ ሆኖበታል። በተለይ መንግሥት የነዳጅ ድጎማውን ማንሳት ከጀመረ በኋላ ያለው ደግሞ የተለየ ነው። ወደፊት ያለው ከዚህ የባሰ እንዳይሆን ምን ቢደረግ ይሻል ይሆን? ለዚህ ብቁ የሆነ ምላሽ መስጠትና መፍትሔ የሚሆን የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ የሚችሉት ለመንግሥት ቅርብ የሆኑ ባለሙያዎች ናቸው። ነገር ግን አንድ ወዳጄ እንደሚለው እነሱ የኑሮ ጫናው እንደሕዝቡ አይሰማቸውም። ይህ ወዳጄ ስለእነዚህ ሰዎች ሲያስረዳ ‹‹እነሱ የነዳጅ ተብሎ የሚሰጣቸው ብር በሊትር ተተምኖ ነው የሚያገኙት፤ የአርባ ሊትር ነዳጅ በብር ተሰልቶ የሚሰጣቸው ከሆነ ዋጋ ጨመረ፣ ቀነሰ ለእነሱ ምንድን ነው? ዋጋ ሲጨምር ገንዘቡ ተጨምሮ ይሰጣቸዋል፤ እንዴት ተብሎ መፍትሔ ይምጣ! ›› በማለት በምሬት ይናገራል።

መቼም የኑሮ ውድነቱ ሁሉም እኩል እንዲሰማው ባይጠበቅም፣ አብዛኛውን ሕዝብ ዕለት በዕለት እያመሰው ይገኛልና ተመጣጣኝ መፍትሔ መስጠቱ ግድ ይላል። አስከፊ የኑሮ ውድነቱን ለመቀነስና መረጋጋት ለመፍጠር መፍትሔ ይሆናል ብዬ ከምለው ነገር አንዱ የሥራ ግብርን ምጣኔን ማሻሻል ነው። በፌዴራል ገቢ ግብር አዋጅ 983/2008 እንደተደነገገው፣ ማንኛውም ተቀጣሪ የሚያገኘው ጠቅላላ የወር ገቢ ከ601 ብር በላይ ሲሆን፣ ከአሥር በመቶ አንስቶ፣ እስከ 35 በመቶ የሚደርስ የግብር ምጣኔ ይጣልበታል። ይህን የሥራ ግብር ምጣኔን ማሻሻል መንግሥት ሊያገኝ የነበረውን ገንዘብ ሊያሳጣው እንደሚችል ይታወቃል። ነገር ግን የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት ሌሎች ሀገሮችም የሚጠቀሙበት ስልት ስለሆነ መንግሥት እየመረረውም ቢሆን ለዜጎቹ ሲል ሊጠቀምበት ይገባል። ይህን ስልት በመጠቀሙ የሚያጣውን ገንዘብ ጥናት ተደርጎ ወደ ተግባር ያልገባውን የንብረት ታክስን ወደ ተግባር በማስገባት ሊያካክሰው ይችላል።

የሥራ ግብር ምጣኔ ሲሻሻል የኑሮ ውድነቱ በከፍተኛ ሁኔታ ያጠቃቸውን ዝቅተኛ የደመወዝ ክፍያ የሚያገኙትን የሚያግዝ ሊሆን ይገባዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚገባው ሌላ ጉዳይ ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል ነው። የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሠማኮ) የሠራተኛውን የኑሮ ጫና ታሳቢ በማድረግ ዝቅተኛ የደመወዝ ወለልን በሚመለከት ለመንግሥት ጥያቄ አቅርቦ በረቂቅ ደንቡ ላይ ውይይት ተደርጓል። ረቂቁም በቀድሞው የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት መቅረቡ የሚታወቅ ነው። እስካሁን ግን ረቂቁ ታይቶ ወደ ተግባር አልተገባም። በሚኒስትሮች ምክር ቤት አማካይነት ደንቡ እንዲወጣ ቢደረግ ከድህነት ወለል በታች ለሚኖሩ ዜጎች መፍትሔ ይሆናል። በተለይ በዚህ ወቅት ያልወጣ ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል ክፍያ መቼ ሊወጣ ነው? ለአብነት ኬንያ  የዓለም አቀፍ የላብ አደሮች ቀን ሲከበር ከዚህ ቀደም በሥራ ላይ የነበረውን ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል የኑሮ ውድነትን ከግምት ውስጥ በመክተት፣ የቀድሞው ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ አደባባይ ተገኝተው ዝቅተኛ የደመወዝ ወለሉን በአዋጅ በስድስት በመቶ እንዲጨምር አስደርገዋል። ኢትዮጵያ ከመነሻውም ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል የሌላት ሀገር በመሆኗ መንግሥት በጉዳዩ ላይ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል።

አሁን እየተደረገ ያለው የሸማቾች ማኅበራት ከተለያዩ የጅምላ አከፋፋዮች ጋር ትስስር በመፍጠር በመረከብ ኅብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ ለሽያጭ ማቅረባቸው የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ተጠቃሽ የሚሆን ነው። በተለይ የእሁድ ገበያ ተብሎ በተለያዩ ቦታዎች በማኅበራቱ የሚሸጡ መሰረታዊ የሆኑ ምርቶች በብልጣብልጥ ነጋዴዎች ከደረጃ በታች የሆኑ ምርቶች በውድ ዋጋ ለሚገዛ ሰው መፍትሔ ሆነዋል። የዋጋ ውጣ ውረድ ስለሌለው በትክክለኛው ወቅታዊ ዋጋ ለመግዛትም አስችለዋል። ይህ ተግባር ያለበትን ውስንነት በማሻሻል ባልተቆራረጠና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ቢፈጸም ለኑሮ ውድነቱ መረጋጋት ያለው ድርሻ ከፍተኛ እንደሚሆን እስካሁን ካሳየው ስኬት መመልከት ይቻላል።

ጽሑፌን የማጠቃልለው ማሳሰቢያ በመስጠት ነው። ‹‹የኑሮ ውድነቱ መናር ያለበትን ያህል ንሯል፤ ከዚህ በኋላ መፍትሔው ጫንቃዬን አደንድኜ የሚመጣውን ችግር መጠበቅ ነው›› የሚለው የኅብረተሰብ ክፍል ቁጥሩ አይሎ፣ ነገን በፍርሃትና በሰቀቀን የሚጠብቅ ከሆነ አደጋው ለሀገር ይተርፋል። ስለሆነም ለመፍትሔው የአንበሳውን ድርሻ የሚውሰደው መንግሥት፣ ማኅበራዊ ቀውስ ከመምጣቱ በፊት የኑሮ ውድነቱን የሚመጥን መፍትሔ ይስጥ።





# ቡናችን

ስሜነህ ደስታ

**የኢኮኖሚ ዋልታ ቡና ቡና፣**
**የገቢ ምንጫችን ቡና ቡና፣**
**የእድገታችን ገንቢ ቡና ቡና፣**
**ዋልታ ነው ቡናችን ቡና ቡና፣. . .**
**“ጅማ ከተማ፣ ቦሳ ቀበሌ 04 ኪነት ቡድን“**

በኢትዮጵያ አብዛኛውን አካባቢ አንድ ጊዜ የተወቀጠ ቡና ተመጥኖ ጀበና ውስጥ ከገባ በኋላ ከአቦል እስከ በረካ ይጠጣል። ጀበናው በተጣደ ቁጥር አተላው ተደፍቶ የተወቀጠ ቡና እንደአዲስ እየተጨመረ የሚጠጣ ቢሆን ኖሮ፣ አሁን በሚላከው መጠን ወደ ውጭ ገበያ አይላክም ነበር። ስለሆነም የቡና አፈላል ስርዓታችንን ጠብቀን ማቆየታችን ለቱሪዝም ከሚያበረክተው አስተዋጽዖ በተጨማሪ የውጭ ንግድ አቅርቦት መጠንን ከፍ ለማድረግ የተጫወተው ሚና ቀላል የሚባል አይደለም። ለማሳያነት በ1994 ዓ.ም. 126,188 ቶን የቡና ምርት ሲመረት፣ ለውጭ ገበያ የቀረበው 110,347 ቶን ነበር፤ ከ10 ዓመታት በኋላ በ2014 ዓ.ም. ደግሞ 652,208 ቶን ቡና የተመረተ ሲሆን፣ ለውጭ ገበያ የቀረበው ደግሞ 300,000 ቶን ነበር። ይህም፣ ከተመረተው ከግማሽ በላይ የሆነው ምርት ለውጭ ገበያ አለመቅረቡን ያሳያል። ለውጭ ገበያ ያልቀረበው ቡና በሙሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ተጠጥቷል ባይባልም፣ በከፍተኛ ሁኔታ እንደተጠጣ ግን መገመት ይቻላል (በኮንትሮባንድ ከሀገር የሚወጣውን ታሳቢ በማድረግ)።

ኢትዮጵያ የቡና መገኛ ሀገር ነች። የቡና መገኛ ሀገር እንደመሆኗ ቡናን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ሲገባት በዛ ልክ ተጠቃሚ አልሆነችም። ቡና ከነዳጅ ቀጥሎ በከፍተኛ ደረጃ ኢኮኖሚውን የሚዘውር እና የሚያነቃቃ ሰብል እንደሆነ በስፋት ይነገርለታል።

“የኢኮኖሚ ዋልታ ቡና ቡና . . .” እንደምንለው ያህል ከማሳው ጀምሮ እስከ ውጭ ገበያው ባለመሥራታችን ብራዚል፣ ቬትናም፣ ኮሎምቢያ እና ኢንዶኔዥያ ሀገሮች ቡናን በብዛትም በጥራትም በማምረት የዓለም ገበያን በስፋት ተቆጣጥረውት ይገኛሉ። እነዚህ ሀገራት ለዚህ የበቁት የአሰራር ሥርዓታቸውን ትኩረት ከገበሬው ጀምሮ እስከ ውጭ ገበያው ድረስ በማድረጋቸው ነው።

ኢትዮጵያ ቡና ወደ ውጭ መላክ ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ በ2014 ዓ.ም የላከችውን ያህል ከፍተኛ መጠን ያለው ቡና ልካና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ አግኝታ አታውቅም፤ በ300 ሺህ ቶን ቡና አንድ ነጥብ አራት ቢሊየን ዶላር አግኝታለች። በዚሁ ዓመት ለሶስተኛ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ በተደረገ የባለልዩ ጣዕም ቡና ቅምሻ ውድድር (ካፍ አፍ ኤክሰለንስ) ላይ 480 ኪሎ ግራም ቡና ለፍጻሜ ውድድር ያቀረበው ከሲዳሞ ክልል፣ አርቤጎና ወረዳ፣ ቡርሳ ቀበሌ የመጣው አቶ ለገሠ በጦሳ በውድድሩ አንደኛ በመውጣት አንድ ኪሎ ቡና በ884 ነጥብ 10 ዶላር (ከ47 ሺህ ብር በላይ) ሸጧል። ይህ ገቢ በኢትዮጵያ የቡና ሽያጭ ታሪክ በከፍተኛ ዋጋ ሆኖ ተመዝግቧል።

በ2014 ዓ.ም. ለተገኘው ውጤት በአንድ በኩል በቡና ምርት ላይ የተለያዩ ጉልህ ሥራዎች መሠራታቸው በምክንያትነት ሲጠቀስ በሌላ መልኩ ደግሞ የብራዚል ቡና ምርት በድርቅና በውርጭ በመመታቱ የተገኘ ልዩ አጋጣሚ ያመጣው ዕድል ነው በሚል ሲገለጽም ይሰማል። ይህንና ሌሎች ቡናን የተመለከቱ ጉዳዮች በማንሳት ከቡናና ሻይ ባለስልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሻፊ ዑመር፣ ከኢትዮጵያ ቡና ላኪዎች ማህበር (በአዲሱ ስያሜ “የኢትዮጵያ ቡና ማህበር”) ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ግዛት ወርቁ እና ከኢኮኖሚ ባለሙያው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸ ተስፋ ጋር ቆይታ በማድረግ የሚከተለውን አቅርበናል።

በዓለም ውስጥ የተለያዩ ሀገራት፣ የተለያየ ጣዕምና መጠን ያላቸውን የቡና ምርቶችን ያቀርባሉ። በተለይ “አረቢካ” የሚባለው ቡና በአሜሪካ በጣም ተወዳጅና ሰባ አምስት ከመቶ ያህሉን የቡና ገበያ የሚሸፍን ነው የሚሉት የኢኮኖሚ ባለሙያው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፣ ኢትዮጵያ አረቢካ ቡናን ለዓለም ገበያ የምታቀርብ ቢሆንም፣ ብራዚል ግን ከፍተኛውን ድርሻ እንደምትይዝ ይጠቅሳሉ። በ2014 ዓ.ም. የብራዚል ቡና በውርጭ በመመታቱ፣ ቡና አቅራቢ የሆኑ ሀገራት በዚህ አጋጣሚ ተጠቃሚ እንደሆኑና ኢትዮጵያም የዚህ ዕድል ተቋዳሽ እንደሆነች ይገልጻሉ። ከዚህ በፊትም የብራዚል ቡና ውርጭ ሲመታው የኢትዮጵያ ቡና በከፍተኛ ሁኔታ የውጭ ገበያ አግኝቶ ገቢ ማስገኘቱን ያስታውሳሉ።

ከአሜሪካ ሀገር ገበያ በተጨማሪ ቻይናን ጨምሮ ሌሎችም ሀገራት በሰፊው ገበያ ውስጥ መግባታቸውን የጠቆሙት ዶ/ር ቆስጠንጢኖስ፣ በውርጭና በኮቪድ ምክንያት አንዳንድ ሀገራት የቡና ምርታቸው ሲቀንስ፣ በሀገራችን ያለው የቡና ግብይት ሥርዓት ግን የተወሰነ መሻሻል ማሳየቱን ይገልፃሉ፡፡ በሀገራችን የተመዘገበው የቡና ምርት ውጤት እንዴት እንደመጣ ከአጠቃላይ እይታ አንጻር መልስ ለመስጠት ያህል ነው እንጂ፣ ሀገር ውስጥ ባደረግነው ጥረት ነው? ወይስ ዓለም ውስጥ ባለው የአቅርቦት ሰንሰለት መበላሸት ነው? የሚለውን ለመለየት ሰፋ ያለ ምርምር ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ቡና ማህበር ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ግዛት ወርቁ ደግሞ፣ ከፍተኛ ገቢ የተገኘበትን

ሁኔታ ሲያስረዱ፣ በኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን በኩል ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ቡናን በተመለከተ እየተደረገ ያለውን እንቅስቃሴ በምክንያትነት ያነሳሉ። ግብይቱ ላይ ያለው ችግር ሙሉ ለሙሉ የተፈታ ባይሆንም ለማስተካከል የሚደረገውን ጥረት በበጎ ጎኑ የሚታይ መሆኑን ገልጸው፣ የብራዚል ቡና በድርቅና በውርጭ በመመታቱ በዓለም የቡና ገበያ አቅርቦት ላይ ክፍተት መምጣቱንና በዚህ ሳቢያም የዓለም ቡና ገበያ ዋጋ ቀደም ሲል ከነበረው ጭማሪ በማሳየቱ፣ በ2014 ዓ.ም. ከተላከው ቡና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ሊገኝ ችሏል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሻፊ ዑመር፣ በ2014 ዓ.ም የብራዚል ቡና በድርቅ በመመታቱ ምክንያት ገበያ ላይ የተወሰነ ክፍተት መፈጠሩን ቢያምኑበትም ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ለመገኘቱ ይሔ ምክንያት ነው የሚለውን እይታ ግን አይቀበሉም፤ ለዚህ ደግሞ ብራዚል ዓመቱን በሙሉ ገበያ ውስጥ መቆየቷን ለማሳያነት ያነሳሉ። ብራዚል እና ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም ቡና አቅራቢ ሀገራት በመኖራቸው ተወዳዳሪ መሆንን እንደሚጠይቅ ጠቅሰው ለከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ መገኘት ከፍተኛውን ደረጃ የሚይዘው ባለፉት አራት ዓመታት ቡናን በተመለከተ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ችግሮችን በመለየት የቡና መጠን አቅርቦትና ጥራት ላይ የተሠራ ሥራ መሆኑን አጽንዖት ሰጥተው ይናገራሉ።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፣ ኢትዮጵያ በ2014 ዓ.ም. ብቻ ሳይሆን ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ከሁለት መቶ ሺህ ቶን በላይ ቡና ለውጭ ገበያ ማቅረቧን በማስታወስ፣ ለተከታታይ አምስት ዓመታት በመጠን ብቻ ሳይሆን በጥራትም ማምረት መቻሏንም ይገልጻሉ። በእነዚህ ዓመታት ውስጥም ብራዚል በሙሉ አቅሟ ገበያ ውስጥ እንደነበረችም በመጥቀስ ሀሳባቸውን ያጠናክራሉ። እርሳቸው እንዳሉት፣ ለዚህ ውጤት መገኘት አስተዋጽኦ ካደረጉ ጉዳዮች መካከል ዋነኛው፣ ቡና ላይ ያሉ ችግሮችን በመለየት በሪፎርም ለመፍታት ጥረት መደረጉ ሲሆን፣ ሪፎርሙን ሊያግዙ የሚችሉ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ወደ ሥራ መገባቱ፣ በተለይ "Vertical Integration" በሚል የተደረገው ለውጥ በላኪና ተቀባይ መካከል ያለው ግንኙነት በአግባቡ እንዲፈፀም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። በዚህም የግብይት ሰንሰለቱ አጥሮ እንዲሳለጥ ሆኗል፤ የቡና መጠንና ጥራት በመጨመሩም የውጭ ምንዛሬ መጠንን ከፍ ማድረግ ችሏል።

ባለፉት ዓመታት ቡና ላይ የተሰሩ ውጤታማ ሥራዎችን መሰረት በማድረግ በ2015 ዓ.ም. 360 ሺ ቶን ቡና በመላክ አንድ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት ዕቅድ መያዙን ያነሱት ዳይሬክተሩ፣ ያለፉት ሶስት ወራት 430 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 426 ሚሊዮን ዶላር በማግኘት የዕቅዱን 98 በመቶ መፈጸም እንደተቻለ ገልጸዋል።



አቶ ሻፊ ዑመር

የቡና የውጭ ንግድ ሰንሰለቱ የተሳለጠ መሆን ለከፍተኛ ገቢ መገኘት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ይኖራል። የግዥ ሰንሰለቱ ከገበሬ ጀምሮ እስከ ውጭ ንግዱ የተራዘመ ከመሆኑ በተጨማሪ በመሃል ደላሎችም አሉበት። አቶ ግዛት ምርቱ የት የት አካባቢ እንዳለ፣ከገበሬ የሚገዛበትን ዋጋ፣ በሳምንት ውስጥ ምን ያህል ቡና እንደተሸጠ፣ ያልተሸጠበት አካባቢ የት እንደሆነ፣ ወዘተ. መረጃ የሚሰጥ የተደራጀ ማዕከላዊ አካል የግልም ሆነ የመንግሥት ቢኖር ደላላ የሚመራበትንና የሚያዝበትን ሁኔታ ማስቀረት እንደሚቻል በአጽንኦት ይናገራሉ።

በዚህ ረገድ ያለውን ሁኔታ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ሲናገሩ፣ የቡና የውጭ ንግድ ሰንሰለቱ ብዙ ፈተና ነው ያለው። ደላላ በዚህ ዋጋ ነው የሚጠው በሚለው እንዲሸጥ ያደርጋል። ላኪዎች መረጃ እንዲያገኙ በሚል የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት ቢቋቋምም መሥራት የሚገባውን ያህል አልሠራም ይላሉ። ብዙ ጊዜ ደላላ የበላይነት የሚያገኘው መንግሥት ሊሠራ የሚገባውን ሥራ በአግባቡ ሳይሠራ ሲቀር እና የቁጥጥር ኃላፊነቱን ሲያስተጓጉል ነው። ስለሆነም ደላላን ማውገዝ ብቻ ሳይሆን ቡና የሚያመርተውንም ሆነ ቡና የሚያቀርበውን ገበሬ ምን ማድረግ እንደሚገባው ተገቢ የሆኑ መረጃዎችን እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይገባል በማለት ይመክራሉ።

አቶ ሻፊ ዑመር፣ በቡና የውጭ ገበያ ላይ ከሚስተዋሉ ችግሮች መካከል አንዱ ደላሎች በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ እየገቡ ማወካቸው መሆኑን በጥናት ከተገኙ ውጤቶች ውስጥ እንደሚጠቀስ ያስቀምጣሉ። እንደእርሳቸው ገለጻ፣ ደላላ በሚበዛበት ጊዜ አርሶ አደሩ ተጠቃሚነቱ ይቀንሳል። የደላላን ሚና ለመቀነስና መፍትሄ ለማበጀት ደግሞ ሪፎርም ተሠርቷል። በሪፎርሙም ለአርሶ አደሩ የተለያዩ አማራጮች ቀርበውለታል። አርሶ አደሩ ራሱ ወደ ውጭ መላክ አይችልም ነበር፣ አሁን ግን ተፈቅዶለታል፤ በሀገር ውስጥም ለህብረት ሥራ ማህበራት መሸጥ ይችላል። አማራጩ ሰፊ ስለሆነለት አርሶ አደሩ ከደላላ ጋር የሚያገናኘው መስመር ተቋርጦ ጥራት ያለው ቡና በማቅረብ በተሻለ ዋጋ መሸጥ ችሏል። በገበያ ሂደቱ ቀደም ሲል አቅራቢ ራሱ ሰብስቦ ወደ ውጭ መላክ አይችልም ነበር። አሁን አቅራቢ ከፈለገ ፈቃድ አውጥቶ ወደ ውጭ መላክ እንዲችል ስለተፈቀደ ሌላው አማራጭ ሆኖ ቀርቧል። በእነዚህ አሠራሮች ደላላ ሙሉ ለሙሉ ተወግዷል ባይባልም ሚናውና ጫናው እንዲቀንስ ተደርጓል። አሠራሩን በማዘመንና በማጠናከር ከዚህ በበለጠ ሲሠራ ደግሞ የደላላን ሚና የበለጠ ማሳነስ ይቻላል።

በቡናና ሻይ ባለስልጣን በኩል የገበያ ሂደቱ እንዲያጥርና እንዲሳለጥ የተለያዩ አዋጆችና እነሱን ለማስፈጸም የሚረዱ መመሪያዎችና አሠራሮች እየወጡ ይገኛሉ። አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ካደረጉ አሠራሮች መካከል የቀጥታ የገበያ ትስስር አንዱ ነው። በተለይ በቀጥታ የገበያ ትስስር አሠራር ላይ መጀመሪያ እንዳሳዩት አይነት ጥራት ያለው ቡና አለማቅረብ እንዲሁም በተዋዋሉበት ዋጋ



አቶ ግዛት ወርቁ

ለመገበያየት የቁጥጥር ዘዴ አለመኖር በባለድርሻ አካላት የሚነሱ ችግሮች ናቸው። የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን በሚሠራቸው ሥራዎች ላይ የተለያዩ ደረጃዎች ይኖራቸው ይሆናል እንጂ ችግሮች ይኖራሉ በማለት የሚጀምሩት የባለስልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሻፊ፣ የቀጥታ ገበያ ትስስር አሰራር ብዙ አርሶ አደሮችን እንደጠቀመ ይገልጻሉ። አሠራሩ ያልገባቸው አንዳንድ ተጠቃሚዎች አሠራሩን በትክክል ካለመተግበራቸው የተነሳ አዲሱ አሰራር ችግር እንዳመጣ ሊያነሱ ይችላሉ ያሉት ዳይሬክተሩ ይህ እንዳይፈጠር፣ በባለስልጣኑ በኩል ተገቢ የሆነ ስልጠና መስጠቱን ጠቁመዋል፡፡ በተለይም ቀደም ሲል አላግባብ ተጠቃሚ የነበሩ ደላሎች የገበያ ሰንሰለቱ ስላጠረ ብዙ ሊሉ እንደሚችሉ ያነሱት አቶ ሻፊ አሰራሩ በአቅራቢና በላኪ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በተገቢ ሁኔታ መፍታት የሚያስችልና ቅሬታ ያለው አካል ቅሬታውን አቅርቦ ማስፈታት የሚችልበት አሰራር ነው ብለዋል።

ለከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ መገኘት አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ ሁኔታዎች አንዱ የባለልዩ ጣዕም ቡና ቅምሻ ውድድር (ካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ) በሀገራችን ውስጥ መከናወኑ እንደሆነ ይጠቀሳል። ቀደም ሲል ይካሄድ የነበረው አሜሪካ ነበር። አሁን ግን እንደ ኬኒያ፣ ኡጋንዳ፣ ሩዋንዳ እና ኢትዮጵያ የመሳሰሉ በሀገራቸው ውስጥ የጥራት ውድድሩን ያካሄዳሉ። የቡና ጥራቱ ከ85 በመቶ በላይ ሲሆን፣ ከፍተኛ ጣዕም አለው ይባላል፤ ዋጋውም በከፍተኛ መጠን ይጨምራል፤ ከዚህ አኳያ ውድድሩ በኢትዮጵያ ውስጥ መደረጉ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከማስገኘቱ በተጨማሪ አምራች ገበሬዎች የሌሎቹን ውጤት በማየት በቀጣይ ጥራት ላይ ተበረታተው እንዲሠሩ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል። ቀደም ሲል አንድ ኪሎ ኮሜርሻል ቡና በአለም ገበያ ከሁለት ዶላር በታች የነበረ ሲሆን አሁን ከሁለት ዶላር በላይ ሆኗል። የቡናን ጥራት በማሻሻል ወደ ስፔሻሊቲ ቡና ግብይት ቢገባ እንዲሁም ቆልቶና ፈጭቶ መሸጥ ቢቻል በከፍተኛ ዋጋ መሸጥ ይቻላል በሚለው ዶክተር ቆስጠንጢኖስና አቶ ግዛት ይስማማሉ።

ቡና ቆልቶና ፈጭቶ መላክ በዕውቀት ስለሚሠራ ከደላላ ተጽዕኖ ያላቅቃል የሚሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፣ አሜሪካ በሥራ በነበሩበት ወቅት ስታርባክስ የተባለ ድርጅት ከኢትዮጵያ ግማሽ ኪሎ ጥሬ ቡና አንድ ዶላር ባልሞላ ዋጋ ገዝቶ፣ ቆልቶና ፈጭቶ 24 ዶላር ይሸጥ እንደነበረ ያስታውሳሉ። በተለይ ስፔሻሊቲ ቡና በጥሬው ከመላክ ቆልቶና ፈጭቶ ገዥዎች በሚፈልጉት ልክ በአንድም ሆነ በሁለት ኪሎ በማሸግ መላክ ለላኪውም ሆነ ለሀገር ከፍተኛ ገቢ እንደሚያስገኝ ያስገነዝባሉ።

አቶ ግዛት የባለልዩ ጣዕም ቡና ጥራት ውድድር ለከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ዕድገት አስተዋፆ እንዳለው አንስተው በሀገራችን በተለይ ገበሬው ጥራትን የማሻሻል ጥቅምን እንዲረዳ በማድረግ በኩል አስተዋጽዖ እንዳደገ ተናግረዋል። አክለውም፣ ውድድሩ ተጠናክሮ ከቀጠለ ከፍተኛ የምርት ጥራት ብሎም የውጭ ምንዛሪ እንደሚያመጣ ያላቸውን ተስፋም ገልጸዋል።

ዋና ሥራ አስኪያጁ ግብይቱን ከኮሜርሻል ወደ ስፔሻሊቲ ቡና ማስገባት በዓብይ ጉዳይ ሊታይ እንምሚገባውና ከማሳው ጀምሮ እስከ ግብይቱ ጥራት ማሻሻል ድረስ ጠንካራ ሥራ መሥራት እንደሚገባ ይመክራሉ። ከጥራት ጎን ለጎን በሔክታር ከ7 እስከ 8 ኩንታል የሚገኝበትንና በመጠንም ለማሳደግ የሚያስችል አሰራርን ማጠናከር ያስፈልጋልም ብለዋል።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ እንደሚሉት ደግሞ፣ ስፔሻሊቲ ቡና ማለት የተለየ ትኩረት ሰጥቶ በዕውቀት ላይ በመመስረት መልቀም፣ ማድረቅ እና ማከማቸት እና ማሸግን የሚያካትት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ቡና ስፔሻሊቲ በማድረግ ለውጭ ገበያ በማቅረብ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት መንግሥት አበባን ለሚልኩ አምራቾች የሚያደርገውን ማበረታቻና ድጋፍ ለቡና አምራቾች እና ላኪዎችም ቢያደርግ ሰፊ ለውጥ ማምጣት ይቻላል። አንዳንድ ሙከራዎች ቢኖሩም በስፋት ሥራዬ ብሎ ምን መሥራት እንደሚገባ፣ መንግሥት ከአምራቹና ከላኪው ጋር በመወያየት ወደ ስፔሻሊቲ ቡና ሽያጭ መግባት እንደሚያስፈግ አጽንኦት ሰጥተው ያስገነዝባሉ።

ከኮሜርሻል ወደ ስፔሻሊቲ ለመግባት ስልጠና እየተሰጠ እንደሚገኝ የገለጹት አቶ ሻፊ ዑመር፣ በቡናና ሻይ ባለስልጣን በኩል ከዚህ በፊት ከተሰጠው በተጨማሪ በቅርቡ ጅማ፣ ሚዛን እና ሀዋሳ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል። በዚህም ቡናን በጥራት በማምረት ወደስፔሻሊቲ ለማስገባት እስከታች ወረዳ ድረስ ስልጠናው ዘልቋል ይላሉ። እርሳቸው እንዳሉት፣ ስልጠናውን ተግባራዊ በማድረግ በርካታ አርሶ አደሮች ተጠቃሚ ሆነዋል፤ በዚያው ልክ ሀገሪቷም የውጭ ምንዛሪ አግኝታለች። ጥራት ያለው ቡና ከተለያዩ አካባቢዎች ስለሚመጡ ከዚህ በፊት ያልታዩ የቡና ዝርያዎችን ለማወቅም ዕድሉ ተገኝቷል። በዚህም ባለፉት ሶስት ዓመታት ስፔሻሊቲ ቡና ለመላክ በተሠራው ሥራ የሚላከውን ቡና መጠን ከ36 በመቶ ወደ 40 በመቶ ከፍ ማድረግ ተችሏል። ይህ ተግባር ወደፊት በተጠናከረ መልኩ ይቀጥላል።

ስለኢትዮጵያ ቡና ሲነሳ መነሳት የሚገባው አንዱ የጫካ ቡና ነው ያሉት አቶ ግዛት፣ የጫካ ቡና ማንም ሰው ሳይንከባከበው አድጎ ይመለከተኛል የሚል አካል ለመልቀም ብቻ በመሄድ የሚሰበስበው እንደሆነ ያስረዳሉ። እርሳቸው እንዳሉት፣ የጫካ ቡና እንክብካቤ ስለማይደረግለት ጥራቱ እንክብካቤ እንደሚደረግለት ባይሆንም፣ ለማስታወቂያ አገልግሎት የሚሰጠው ጥቅም ግን ከፍተኛ ነው። “የኢትዮጵያ ጫካ ቡና በተፈጥሮ የበቀለና ከንክኪ በፀዳ ሁኔታ የሚያድግ ነው” በሚል መሸጡ ከሚያስገኘው የውጭ ምንዛሪ በበለጠ የኢትዮጵያ ቡናን ያሻሽጣል። ስለሆነም ማስተዋወቁ ላይ ተግቶ መሥራት ይገባል።

የጫካ ቡና ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ እንደማይገኝና ኢንዶኔዥያ እያቀረበች በከፍተኛ ዋጋ እንደምትሸጥ የሚገልጹት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፣ አሁን ገበሬዎችና ባለሀብቶች ሰፋ አድርገው ማምረት በመጀመራቸው መሻሻል አምጥቷል እንጂ፣ ቀደም ሲል በነበረ

መረጃ 98 በመቶ የኢትዮጵያ ቡና ወፍ ዘራሽ (የጫካ ቡና) እንደነበረ ያስታውሳሉ። አያይዘውም፣ የኢትዮጵያ ጫካ ቡና፣ የቡና መነሻ ተብሎ ዩኔስኮ መመዝገቡን ጠቅሰው፣ ይህን በማስተዋወቅ ገበያውን ማሳደግና ማስፋፋት እንደሚገባ ይናገራሉ። "በመረጃና በማስረጃ ራሳቸውን መግለጽ የሚችሉ የቡና ነጋዴዎችና አስተዋዋቂዎች መኖር አለባቸው። ቬትናሞች የቡና ገበያው ላይ ራሳቸውን ማስተዋወቅ ስለቻሉ ከዓለም ሁለተኛ ቡና ላኪ ሀገር ሆነዋል። ኮሎምቢያም ቡናን በማስተዋወቅ በኩል ከፍተኛ ሥራ በመሥራቷ ሶስተኛ ላኪ ሀገር ሆናለች። የማስተዋወቅ ሥራ ካልተሠራ በስተቀር በየጊዜው ተከታታይነት ያለው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት አይቻልም። ጎረቤታችን ኤርትራ እንኳን የቡና አፈላል ባህልን በተለያዩ መንገዶች በከፍተኛ ሁኔታ ታስተዋውቃለች፤ ለቱሪዝም መስህብነትም ትጠቀምበታለች" በማለት የማስተዋወቅን ጥቅም ይገልጻሉ።

የኢትዮጵያ ጫካ ቡና ተፈጥሯዊና በጣም ጣፋጭ ቡና ስለሆነ በተለይ አውሮፓዎች የሚፈልጉት እንደሆነ የሚጠቅሱት አቶ ሻፊ ናቸው። በተለይ በኤግዚቢሽኖች ላይ በከፍተኛ ሁኔታ የማስተዋወቅ ሥራ እንደሚሠራ እንዲሁም የጫካ ቡና ተብሎ ብራንድ እንደተለየላቸው ይናገራሉ። በተሠራው ሥራ ገበያ ከመገኘቱ በተጨማሪ ጎብኝዎችም መጥተው እየተመለከቱት ስለሆነ ለቱሪዝም የሚሰጠው አገልግሎት ከፍተኛ ነው ይላሉ።

አቶ ግዛት፣ ለቡና ምርት መጠንና ጥራት መሻሻል በፌዴራል ደረጃ የሚወጡ መመሪያዎች እስከታችኛው እርከን ድረስ ግንዛቤ አግኝተው የተናበበ ሥራ መሥራትን እንደሚጠይቅ ያነሳሉ። አፈጻጸሙ ሲታይ ግን ቡና ላይ እንዲተገበሩ የሚወጡ መመሪያዎች በክልሎችና በወረዳ ደረጃ ሲታይ ዝቅተኛ መሆኑንም ይጠቅሳሉ፤ አቶ ግዛት እንደሚሉት ፌዴራሉ ያወጣውን ቡናን በሚመለከቱ የሚሰራጩትን መረጃዎ በክልሎች በኩል ተቀባይነት አግኝተው እስከታችኛው እርከን ድረስ በመውረድ ተግባር ላይ እንዲውል ማህበራቸው ከሁሉም አካላት ጋር ተቀራርቦ ለመሥራት የበኩሉን ጥረት እያደረገ ይገኛል። ኢትዮጵያ ለዓለም ገበያ ቡና የምታቀርበው ኮሎምቢያ እና ብራዚልን ከመሳሰሉ ቡናን በብዛትና በጥራት ከሚያቀርቡ ሀገራት ጋር ተወዳድራ ነው። በመሆኑም፣ ሀገር ውስጥ ያለውን የቡና ማምረትና መላክ ሰንሰለት የተሳለጠና ውጤታማ ማድረግ ላይ ተነጋግሮ መግባባት እንደሚያስፈልግ ይጠቅሳሉ። ይሄ በጊዜ ሂደት ይሻሻላል የሚል ተስፋ አላቸው። አያይዘውም አሁን የሚታዩት በክልሎችና በወረዳ ደረጃ መመሪያዎች ተግባር ላይ ያለመዋል ችግር ሀገሪቱ ውስጥ የሚታየው ያለመረጋጋት ሁኔታ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ያነሳሉ።

ቡናና ሻይ ባለስልጣን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ትስስር በመፍጠር በቅንጅት



ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸ

እንደሚሠራ የገልጹት ደግሞ አቶ ሻፊ ናቸው። አቶ ሻፊ እንደሚሉት የባለስልጣኑ ትልቁ የሥራ ድርሻ የክልሎችን አቅም መገንባት፣ መመሪያዎችንና አሠራሮችን ማውጣት ነው። ከዚህ አልፎ ግን አምራቹን፣ አቅራቢውን፣ ላኪውን እና ማህበራትን እየደገፈና እያበረታታ ይገኛል። አዋጅ፣ደንብና መመሪያ ሲያዘጋጅ ደግሞ ባለድርሻ አካላትን ያወያያል። ከክልሎችና ከሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት ጋርም የቡናን ግብይት በተመለከተ በጋራ የሚወያይበት፣ የሚያቅድበት እና ሥራዎቹን የሚገመግምበት በሳምንት አንድ ጊዜ የግንኙነት ጊዜ አለው።

ቡና ወደ ውጭ ተልኮ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እንዳያስገኝ ማነቆ ከሚሆኑበት ነገሮች አንዱ የኮንትሮባንድ ንግድ ነው። ቡና ከፍተኛ ቁጥጥር እየተደረገለት የሚንቀሳቀስ አረንጓዴ ወርቅ ነው። ቁጥጥሩ ቢኖርም በኮንትሮባንድ የሚንቀሳቀስ ቡና መኖሩ በየጊዜው ይነገራል። እንደ አቶ ግዛት ገለጻ፣ ኮንትሮባንድን ለመቀነስ ቁጥጥሩ ላይ ያለውን አሠራር ፈትሾ ከማስተካከልና ከማጠናከር በተጨማሪ አሁን አምራች በሆኑ አካባቢዎች ያለውን የምርት መጠን መጨመር እንዲሁም፣ ለቡና ተስማሚ የሆኑ አዳዲስ መሬቶችን በቡና መሸፈን ያስፈልጋል።

ቡና ብቻ ሳይሆን ብዙ ነገሮች በህገ ወጥ መንገድ እንደሚዘዋወሩ ያነሱት የኢኮኖሚ ባለሙያው ዶ/ር ቆስጠንጢኖስ ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት፣ ኢትዮጵያ በዓመት ከ1.5 እስከ 3.5 ቢሊዮን ዶላር በህገወጥ ንግድ ታጣለች የሚል ሪፖርት መኖሩን ይጠቅሳሉ። በቅርቡ ህንድ ውስጥ የተያዘ 16 ኪሎ ወርቅ መነሻው ኢትዮጵያ እንደሆነ የተሰማውን ዜና በማሳያነት ያነሳሉ። አያይዘውም፣ ህገወጥ ንግዶች የራሳቸው የሆነ የአቅርቦት ሰንሰለት እንዳላቸው በመግለጽ፣ ህገወጥ ነጋዴዎቹ ከባለስልጣናትና በየድንበሩ ካሉ ተቆጣጣሪዎች ጋር የጥቅም ተካፋዮች ከሆኑ ኮንትሮባንድን መከላከል ከባድ ስለሚሆን ጥብቅ ክትትል ማድረግን እንደሚጠይቅ ያሳስባሉ። ወርቅ፣ ቡና፣ የቁም ከብት፣ እጣንና ሌሎችም በህገወጥ መንገድ ከወጡ በኋላ በዚህ የተገኘው ዶላር ደግሞ ኢኮኖሚውን እንዳሻው ያተራምሳል ያሉት የኢኮኖሚ ባለሙያው መንግሥት ስለጉዳዩ አያውቅም ማለት አስቸጋሪ ስለሚሆን መፍትሔ ሊሰጠው ይገባል በማለት ያሳስባሉ። በመጨረሻም አፍሪካ በየዓመቱ በህገወጥ መንገድ ወደ 156 ቢሊዮን ዶላር ታጣለች፤ ይሄ ጉዳይ አፍሪካን በከፍተኛ ሁኔታ ስላደማ በኢትዮጵያም አፈጻጸሙ ላይ የሚመለከታቸው አካላት ትኩረት ሰጥተው ማሻሻያ እንዲያደርጉበት ይመክራሉ።

የባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እንዳሉት፣ በቡናና ሻይ ባለስልጣን በኩል ኮንትሮባንድን ለማስቀረት ሁለት ተግባራት ተከናውነዋል። አንደኛው ቡናን በተመለከተ ብቻ ሀገራዊ የኮንትሮባንድ ኮሚቴን ማቋቋም ሲሆን፤ ኮሚቴው ፌዴራል ፖሊስ፣ ጉምሩክ ኮሚሽን እና ክልሎችን አካቷል። ሁለተኛው ደግሞ፣ በባለስልጣኑ በኩል የቡና ግብይት ሂደትን በተመለከተ ሶፍትዌር በማበልጸግ የቡና ባላንስ እየተሠራ ችግር የሚፈጥሩትን ሰዎች በመለየት እርምጃ እንዲወሰድባቸው የማድረግ ተግባር ነው። እንደሳቸው ገለጻ ቁጥጥሩን በግልጽ ከማድረግ በተጨማሪ በስውርም የማጠናከር ሥራ ተሠርቷል። በዚህም ቡና የሰወሩ አካላት እና ተባባሪዎቻቸው ለሕግ ቀርበው ተጠያቂ እንዲሆኑ ለፌዴራል ፖሊስ መረጃዎች ቀርበዋል። የቡና ኮንትሮባንድ ንግድ ላይ ሰፊ ተግባራዊ ሥራ በመሠራቱ በጉልህ በሚታይ ደረጃ ህገወጥነቱ ቀንሷል። በ2015 ዓ.ም. ደግሞ ቅንጅታዊ አሠራሩን በማጠናከር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ዕቅድ በማውጣት ተፈጻሚ እንዲሆን እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል።

ኢትዮጵያ ቡናን ለዓለም ገበያ በማቅረብ ተከታታይነት ያለው የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ከሌሎች ቡና አቅራቢ ሀገሮች ጋር በመወዳደር ጥራት ያለው ቡና በከፍተኛ መጠን ማቅረብ ይጠበቅባታል። ይህን ተግባር ለመፈጸም ደግሞ በቡና ማምረት፣ ማቅረብ እና መላክ ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላትን መንግሥት በክህሎትና በፖሊሲ ሊያግዛቸው ይገባል። በተጨማሪም፣ መንግሥት የቡና የውጭ ንግድ ግብይት ሰንሰለቱ እንዲያጥር አሁን እያደረገ ያለውን ጥረት በማጠናከር መተግበር ይኖርበታል። በዚህም በቡና የውጭ ንግድ ሂደቱ ላይ ሁከት የሚፈጥሩትን የደላላ ጫናንና ሚናን እንዲሁም የኮንትሮባንድ ንግድን በመቀነስ በሂደት ማስቀረት አለበት የሚለው የዝግጅት ክፍላችን መልዕክት ነው።

# የኢትዮጵያ ብዝሃ ሕይወት ሀብት እና አጠባበቅ



ተክለሃይማኖት ኃይለ ሥላሴ
(ተባባሪ ፕሮፌሰር)



ሽብሩ ተድላ
(ፕሮፌሰር ኢሜሪተስ)

## መግቢያ

ኢትዮጵያ ብዙ የተለያዩ ሥርዓተ ምህዳሮች አሏት፣ ይኸም ሁኔታ ከፍተኛ የብዝሃ ሕይወት ባለ ሀብት ለመሆን አብቅቷታል። ለተለያዩ ሥርዓተ ምህዳሮች መገኘት ምክንያት ከሆኑት አንዱ፣ ኢትዮጵያ የምድር ገፅታ ከምድር መቀነት(equator) በሰሜን አቅጣጫ ከሦስት ዲግሪ "ኪክሮስ" እስከ አሥራ አምስት ዲግሪ "ኪክሮስ"(latitude) የተለጠጠ መሆኑ ነው። በተጨማሪ ምድረ-ገፅታዋ፣ በጣም ሙቀት ከሆነው ከባህር ወለል በታች 115 ሜትር(ዳሎል) ጀምሮ፣ በጣም ቀዝቃዛ እስከሆነው አካባቢ ከባህር ወለል በላይ እስከ 4,620 ሜትር(ራስ ደጀን) መዘለቁ ነው። የገፀ ምድሩም አቀማመጥ ወጣ ገብ ነው፣ ሸለቆ፣ ኮረብታ፣ ተራራ፣ ወዘተ. ይኸም ለተለያዩ ሥርዓተ ምህዳሮች መገኘት መንስዔ ሆኗል።

የተለያዩ ሥርዓተ ምህዳሮችም በበኩላቸው ለተለያዩ እፅዋት፣ እንስሳት፣ ዘረ እንጉዳይ(fungus) እና ደቂቀ ሕዋሳት(ሚክሮብ/microbes) መኖሪያነት ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፤ ብርድ፣ ሙቀት፤ ደረቅ፣ እርጥብ፤ ሸለቆ፣ ተራራ፣ ሜዳ፣ በረሃ፤ ጫካ፣ ወዘተ. ስለሆነም ለተለያዩ ሕያው አካላት ምቹ የሆኑ አካባቢዎች ይፈጠሩላቸዋል። በእነዚህም ምክንያቶች ኢትዮጵያ ለመጠነ ሰፊ የብዝሃ ሕይወት ስብጥር መከሰት፣ ብሎም ኢትዮጵያ በዓለማችን ውስጥ ከሚገኙ በብዝሃ ሕይወት ሀብት ከታደሉት ጥቂት አገሮች አንዷ ለመሆን በቅታለች። በተጨማሪም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች፣ በሌላ አካባቢዎች የማይገኙ ግን በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ፣ የኢትዮጵያ "አገሬ" ዝርያዎች(endemic species) ባለቤት እንድትሆን አድርገዋታል።

## ብዝሃ ሕይወት ምንድን ነው?

ብዝሃ ሕይወት ማለት ሕይወት ባላቸው አካላት ሁሉ(እፅዋት፤እንስሳት እና ደቂቀ ዘአካላት) መካከል ያለ ተለያይነት(variation) ማለት ሲሆን፣ ይህም በይዘት በሦስት የእርከን ደረጃዎች ይመደባል። አንደኛው በአንድ የብቸኛ ዝርያ(species) ስብስብ(population) ውስጥ ባሉ ነጠላ ሕያው አካላት(individuals within a species) ውስጥ ያለው የበራሂዎች ክምችት ተለያይነት ሲሆን፣ "ጄኔቲክ ተለያይነት"(Genetic diversity) በመባል ይታወቃል። ሁለተኛው በተለያዩ የብቸኛ ዝርያዎች(species) መካከል የሚገኘው የበራሂዎች ክምችት ተለያይነት ሲሆን፣ ይኸም የብቸኛ ዝርያዎች ብዝሃ ሕይወት በመባል



የሥርዓተ ምህዳር ብዝሃ ሕይወት

የሚታወቀው ነው፣ ብሎም በአንድ አካባቢ የሚገኙ የብቸኛ ዝርያዎች ቁጥርና ክምችት የሚገለፅ ይሆናል። ሦስተኛው ቀደም ካሉት በዘለለ ሁኔታ፣ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሕያው አካላት፣ በዚያን መሰል ሥርዓተ ምህዳር(ecosystem) ለመኖር የሚያበቃቸው የበራሂ መሰናዶዎች አሏቸው፣ ስለሆነም በአካባቢው ከሚገኙ ሌሎች ሕያው አካላት ጋር አካባቢውን ተጋርተው ይኖራሉ። በዚያ አካባቢ የሚኖሩ ሕያው ብዝሃ ሕይወት የከባቢውን ሁኔታ ሚዛን ጠብቆ ለመኖር አለኝታ ነው። በአንድ ሥርዓተ ምህዳር ለመኖር የሚያስችሉ፣ በተለያዩ ሕያው አካላት የታቀፉ የበራሂዎች ጥርቅም፣ የበራሂዎች ክምችት የሥርዓተ ምህዳር ብዝሃ ሕይወት በመባል ይታወቃል። ሥርዓተ ምህዳር ውስን ወይም ሰፊ ሊሆን ይችላል፣ ዋናው መለያው ግን ሚዛን ጠብቆ በአካባቢው የሚኖሩ ሕያው አካላትን አስተናጋጅ መሆኑ ነው።

የመጀመሪያው በነጠላ አካል ውስጥ ያለው በራሂ ክምችት፣ ሁለተኛው በብቸኛ ዝርያ ስብስብ ውስጥ ያለው የበራሂ ክምችት፣ በሦስተኛ ደረጃ በአንድ ሥርዓተ ምህዳር ውስጥ ያለውን የበራሂ ክምችት ገላጮች ናቸው። በዘመናችን የሚገኘው(አሁን ያለው) የብዝሃ ሕይወት ሀብት በዝግምተ ለውጥ(evolution) እየተገራ፣ በቢሊዮን ዓመታት የተገኘ የተፈጥሮ ሀብት ነው።

ከላይ እንደተጠቀሰው ብዝሃ ሕይወት በመሠረቱ የበራሂዎች ክምችት ነው። የሕያው ቅርጽ፣ ባህርይ እና ተግባራት የሚወሰነው፣ ከወላጆቻቸው በሚወርሷቸው በራሂዎች(genes) ነው። በራሂዎች በማርዳ(የልጆች የአንገት ጌጥ) መሰል፣ ሃብለ በራሂ(chromosomes) በመባል በሚታወቅ አወቃቀር፣ ተገንብተው፣ በሕያው አካላት የሚፈበረኩ የፕሮቲኖችን ዓይነት እና ይዘት ይወስናሉ። ለምሳሌ የአንድ ቤት ፕላን፣ የሚገነባው ቤት ምን ዓይነት እንደሚሆን፣ ስንት ክፍሎች፣ በሮች፣ መስኮቶች፣ ወለሎች፣ ወዘተ. እንደሚኖሩት ይወስናል። የሚገነባው ቤት አካል የሚሆኑ ክፍሎች ሁሉ በእቅዱ መሠረት ነው የሚገነቡት፣ እቅዱ ይዘታቸውንም ሆነ ቅርጻቸውን ይወስናል። በዚሁ አምሳያ በራሂዎች ለሕልውና ወሳኝ የሆኑ ተግባራት የሚያስተናግዱ የኬሚካላዊ ውሁድ፣ ሕልውና፣ እቅድ ወሳኝ መዋቅሮች ናቸው።

የበራሂዎች ኬሚካላዊ መዋቅሮች በተለያዩ ምክንያቶች ሊቀየሩ ይችላሉ። ለምሳሌ በፀሐይ ጨረር፣ በኑክሊየር ጨረር፣ በመርዛማ ኬሚካላዊ ውሁዶች፣ ወዘተ. ። ስለሆነም በነኝህ መንስዔዎች የተቀየሩ በራሂዎች በተከታይ ትውልድ ስለሚወረሱ፣ በሂደት የልጅ፣ ልጅ፣ --- ልጆች ባህርይ እና ቅርጽ ከምንጅላቶቻቸው የተለየ ሊሆን ይችላል። ሁኔታው አመቺ ሆኖ ሲገኝ፣ በሂደት አዲስ ብቸኛ ዝርያ(species) ሆነው ሊከሰቱ ይችላሉ። በዚህ ሂደት ነው አዳዲስ የእንስሳትም ሆኑ የእፅዋት፣ የዘረ እንጉዳይም ሆነ የሚክሮብ ብቸኛ ዝርያ ዓይነቶች የሚገኙት/የሚከሰቱት።

ከላይ እንደተጠቀሰው፣ የሕያው አካላት ይዘት፣ ቅርፅ፣ ባህርይ ተግባር የሚወስኑት



ለምግብነት የሚያገለግሉ የተላመዱ (Domesticated) የእፅዋት ዝርያዎች

በራሂዎች ናቸው። የሰው ልጅ ከ35 እስከ 45 ሺ የሚገመቱ በራሂዎች፣ በሃብለ በራሂ(chromosome) ይዘት ተያይዘው፣ ተሰድረው ይገኛሉ። የያንዳንዱ ግለሰብ በራሂዎች ከሌሎች ግለሰቦች በራሂዎች ጥቃቅን ልዩነቶች አሏቸው። ለዚህም ነው በዓለማችን ሁለት ምንም ልዩነቶች የሌሏቸው፣ በሁሉም ሁኔታ አንድ ዓይነት የሆኑ ግለሰቦችን ማግኘት የማይቻለው። እያንዳንዱ ግለሰብ ልዩ ነው፣ ልዩነቱም በበራሂዎች ልዩነቶች ላይ የተመሠረተ ነው። የሰው ልጆች የጣት አሻራ በበራሂ አማኻኝነት የተመሠረተ ስለሆነ ነው ለያንዳንዱ ግለሰብ እንደ ልዩ መለያ ሆኖ የሚወሰደው/ የሚያገለግለው። ምንም ጥቃቅን ልዩነቶች ቢኖሩ፣ የሰው ልጆች ካለምንም ችግር ለመራባት/ለመዋለድ ስለሚችሉ፣ የአንድ ብቸኛ ዝርያ አባላት ናቸው። የሰው ዘር ብቸኛ ዝርያ "ሆሞ ሳፒያንስ"(Homo sapiens) በመባል ይታወቃል፣ ከላይ እንደተወሳው በዓለም ላይ ያሉት ሕዝቦች፣ ምንም ጥቃቅን ልዩነቶች ቢኖሯቸው፣ በአንድ ብቸኛ ዝርያ ነው የታቀፉት።

ሕያው አካላት በተፈጥሮ የተጎናፀፉት እምቅ የብዝሃ ሕይወት ሀብት አላቸው። እንዲሁም የተለያዩ ሕያው አካላት፣ የተለያዩ በራሂዎች ውጤቶች ናቸው። አንድ አካባቢም በውስጡ ምን ዓይነት እፅዋት፣ እንስሳት፣ ዘረ እንጉዳይ ወይም ማይክሮብ ሊያንሰራሩ እንደሚችሉ ይወስናል። ስለሆነም አካባቢም የራሱ የሆነ የብዝሃ ሕይወት ባለቤት ነው። በነኚህ ምክንያቶች ነው፣ ብዝሃ ሕይወት እንክብከቤ ሲደረግ፣ የእንስሳትም ሆኑ የእፅዋት ክምችቶች፣ በያሉበት አካባቢ(in situ)፣ ለምሳሌ ቆላ፣ ደጋ፣ ረግረጋማ ቦታ፣ ጫካ፣ ወዘተ. እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው።

## የብዝሃ ሕይወት ጥቅማ ጥቅሞቱ

ከላይ በተገለጸው መሠረት፣ ብዝሃ ሕይወትን በሥነ ፍጥረት ይዘቱ ብቻ መገንዘብ ግንዛቤውን ጎደሎ ያደርገዋል። ብዝሃ ሕይወት ለሰው ልጆች ብዙ ጥቅማ ጥቅሞችን ያበረክታል። ይኸውም በምግብ፣ በማገዶ፣ በመጠለያ ግንባታ፣ በቁሳቁስ መሰናዶ፣ ወዘተ. ይተረጎማል። የሰው ልጆች ምግብ ፍጆታቸው መሠረቱ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ(ሳር፣ ቅጠላቅጠል ተመግበው ያደጉ እንስሳት አማኻኝነት) እፅዋት ናቸው። ከምግብ ዋስትና በተጨማሪ፣ ብዝሃ ሕይወት ለሰው ልጆች ከሚያስገኘው ዘርፈ ብዙ ጥቅማ ጥቅም አንጻር ግንዛቤ ማዳበር ይገባል። የመድኃኒት፣ ንፁህ አየር እና መጠለያ፣ በአጠቃላይ ለጤና ተስማሚ የሆነ አካባቢ መገኘትም ብዝሃ ሕይወት ዓይነተኛ ምክንያት ነው።

የብዝሃ ሕይወት ጥቅማ ጥቅም ጎልቶ የሚታየው ከእፅዋት አንፃር ነው። በዓለማችን ሰባት ሺ ገደማ እፅዋት ለሰው ልጆች ምግብነት ያገለግላሉ፤ ሆኖም የሰው ልጅች በብዛት ለምግብነት የሚጠቀሙባቸው(የሚበሉት)፣ ዘጠና በመቶ(90%) የምግብ ፍጆታን የሚያሟሉት ሰላሳ ገደማ ብቸኛ ዝርያዎች ናቸው። በብዛት የምግብ ፍጆታዎችን የሚያሟሉት የተላመዱ(domesticated races) የእፅዋት ብቸኛ ዝርያዎች ሲሆኑ፣ ለነኚህ ለተላመዱት፣የቅርብ ወገኖች የሆኑ፣ ያልተላማዱ(wild races) አቻዎች አሏቸው። ከተላመዱት ብቸኛ ዝርያዎች ይልቅ ባልተላመዱት ብቸኛ ዝርያዎች ውስጥ የበራሂዎች ስብጥር ልዩነቶች አለ፤ ስለሆነም ያልተላመዱት፣ ከተላመዱት ጋር ሲነፃፀሩ፣ የላቀ የበራሂዎች ተለያይነት ሀብታሞች ናቸው። በአንፃሩ የተላመዱት ደግሞ የበራሂዎች ተለያይነት ክምችት ድሆች ናቸው።

ከምግብነት በተጨማሪ እፅዋት የሰው ልጆች መድኃኒት ፍላጎቶችን ያሟላሉ፣ 70 ሺ ገደማ እፅዋት ለመድኃኒትነት ያገለግላሉ። በገጠር የሚኖሩ ማህበረሰቦች የመድኃኒት መደብሮቻቸው እፅዋት ናቸው። ለምሳሌ የሰማኒያ በመቶ(80%) አፍሪካውያን መድኃኒት መደብሮቻቸው እፅዋት ናቸው፣ አገራችንም ከዚህ የተለየች አይደለችም። በአገራችን እነ ቀብርቾን፣ መተሬን አንደ ምሳሌነት ማውሳት ይቻላል። በአደጉ አገሮችም ቢሆን፣ ለምሳሌ ሰሜን አሜሪካ፣ በሐኪሞች ከሚታዘዙት መድኃኒቶች ግማሹ(50%) መሠረታቸው የእፅዋት ዝርያዎች ናቸው፣ ለምሳሌ "ፔኒሲሊን"(penicillin)፣ "አስፕሪን"(aspirin)፣ የወባ ኪኒን(quinine)፣ ወዘተ. ።

ብዝሃ ሕይወት ከሥርዓተ ምህዳር አንፃር ሲታይ፣ አንደ አካባቢ ሚዛን አስተናጋጅ ሊወሰድ ይችላል። አካባቢ በካይ የሆነውን "ካርቦን ዳይኦክሳይድን"($CO_2$) እፅዋት ምገው፣ በፀሐይ ኃይል ታግዘው፣ "ካርቦን ዳይኦክሳይድን" ለእድገታቸው ግብዓት ካደረጉ በኋላ፣ ለሕያው ሕልውና አስፈላጊ የሆነውን የአየር ዓይነት፣ "ኦክሲጅንን"($O_2$) ያበረክታሉ። ስለሆነም የአካባቢውን ብክለት ቀንሰው፣ ጠቃሚ አየር አፍልቀው፣ የሕያውን ሕልውና አረጋግጠው፣ ሁኔታውን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ያስተናግዳሉ።

እፅዋት ለአካባቢ ውበትም አለኝታዎች ናቸው። ለአረንጓዴ ቅጠላቅጠል እንዲሁም በአበባ ሕብረ ቀለማት ያሸበረቀ አካባቢ አበርካቾች ከመሆናቸው በተጨማሪ በእንደዚህ ያሉ አካባቢዎችም ወፎች ሲከንፉ፣ ቢራቢሮዎች ብር ትር ሲሉ ማየት ይቻላል። ይህም ለሰው ልጆች መንፈሳዊ እርካታን ያበረክታል።

## በኢትዮጵያ ብዝሃ– ሕይወት" (biodiversity) ጥቅማ ጥቅሞቱ ምሳሌዎቱ

ብዝሃ-ሕይወት በጥቅሉ ሲታይ ሰበነክ

ያልሆነ፣ በተፈጥሮ የሚገኝ የተትረፈረፈ ሀብት ነው። ከላይ እንደተገለጸው የብዝሃ-ሕይወት ጥቅም ፈርጀ-ብዙ ነው። ቀደም ሲል፣ በሌላ ጽሑፍ በአንዳችን (ሽብሩ ተድላ) እንደተወሳው፣ ከኢትዮጵያ የተገኘች አንድ የገብስ ዘር፣ የካሊፎርንያን(USA) የቢራ ግብዓት የሆነን የገብስ ዘር ከመጥፋት ታድጋለች። ታሪኩ እንዲህ ነው፤ ከዓመታት በፊት ከሰሜን ሸዋ የተገኘች አንድ የገብስ ዝርያ፣ በካሊፎርንያ የቢራ ግብዓት የሆነን የገብስ ዘር ሊያጠፋ የደረሰውን የበሽታ መንስዔ "ቫይረስ"(Virus) ለመቋቋም የሚያስችል "በራሂ"(gene) እንዳላት በምርምር ተደረሰበት።

ስለሆነም ይህች የገብሱን በሽታ ለመቋቋም የምታስችለዋ "በራሂ"፣ ኢትዮጵያ ከተገኘው የገብስ ዘር ተፈልቅቃ ወጥታ፣ በበሽታ ሲጠቃ የነበረው የካሊፎርንያ ገብስ "ሃብለ በራሂ" ሰንሰለት አካል እንድትሆን ተደርጋ (ከነባሩ ተቆርጣ አዲሱ በበሽታ ከሚጠቃው ላይ ተቀጥላ)፣ ሊጠፋ የነበረውን የካሊፎርንያ የገብስ ዘር በሽታውን ለመቋቋም በቃች፣ ሂደቱም "የዘረመል" ምህንድስና ነው። ስለሆነም፣ ሊጠፋ የደረሰው የካሊፎርንያ የገብስ ዝርያ "በቫይረሱ" ምክንያት ሲጠቃ ከኖረበት በሽታ ነፃ ሆኖ፣ በካሊፎርኒያ የቢራ መፈብረኩ(ማምረቱ) ሥራ ቀጠለ። ይህች በኢትዮጵያ ገብስ ውስጥ ያለች "በራሂ"፣ ማለትም የኢትዮጵያ "የብዝሃ-ሕይወት" አካልና ሀብት፣ ውቅያኖስ አቋርጣ ምንም ዋጋ ሳይከፈልባት(ጥቅም ሳናገኝባት)፣ ለሌላ አገር ሰዎች ጥቅም አበርካች ለመሆን በቃች-ከሞኝ ደጅ ሞፈር ይቆረጣል እንዲሉ።

በተጨማሪ በ1970ዎች የቡና በሽታ(Coffee rust) የብራዚልን፣ የመካከለኛውን አሜሪካ እና እንዲሁም የሲሪላንካን የቡና ተክል ባጠቃበት ወቅት፣ በሽታውን ለመከላከል በሚችል፣ ኢትዮጵያ ውስጥ በተገኘ የቡና ዘር ነው በሽታውን ለመቋቋም የተቻለው።

በመሠረቱ ታዳጊ አገሮች የብዝሃ ሕይወት ሀብት ባለፀጎች ሲሆኑ፣ ያደጉ አገሮች ደግሞ የቴክኖሎጂ ልህቅና አላቸው። የብዝሃ ሕይወት ጥቅማ ጥቅም አንዱ መግለጫ፣ ባዮቴክኖሎጂ ሲሆን፣ የባዮቴክኖሎጂ ዋናው ግብዓት(በራሂዎች) የሚገኘው በብዝሃ ሕይወት ዋና ቋት ውስጥ ነው። በራሂዎች ናቸው ከአንድ ሕያው አካል ሃብለበራሂ ተቆርጠው፣ ሌላ ሕያው አካል ሃብለ በራሂ አካል ተደርገው፣ የሚፈለገውን ተግባር የሚያስተናግዱ። ለምሳሌ በሽታን ወይም ቅዝቃዜን፣ ወዘተ. መቋቋም የመቻል አቅምን የሚያጎናጽፉ። ስለሆነም ታዳጊ አገሮች የብዝሃ ሕይወት ሀብታቸውን አቅርበው፣ ያደጉ አገሮች ደግሞ በቴክኖሎጂ ተጠቅመው፣ በጋራ ብዙ ጠቀሜታ ያሏቸው ተግባራትን ማከናወን ይቻላል። ወደፊት ታዳጊ አገሮችም የቴክኖሎጂ ዕውቀትን እና ክህሎትን ይጎናፀፋሉ፣ ብሎም የብዝሃ ሕይወት ሀብታቸውን ካለ እገዛ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

## ብዝሃ ሕይወት ሕያውን ከማላመድ(Domestication) አንፃር

የብዝሃ ሕይወት ይዘት ቀለል ባለ መልክ ልንገነዘብ የምንችል በርቢ/በማዋለድ ሂደት ነው የሚል እይታ አለን። ለምሳሌነት እንዲያገለግሉ ከእፅዋት እንዲሁም ከእንስሳት ምሳሌዎች እናወሳለን። ጽጌ ረዳ የእፅ ዝርያ ነው፣ ሁሉም የጽጌረዳ ዓይነቶች መሠረታቸው ሰብነክ ያልሆነ፣ ማለት ያልተላመደ(wild) የጽጌረዳ ዝርያ ነው። የሰው ልጅ በማዳቀል ተግባር የተለያዩ ቀለማት ያሏቸው የጽጌረዳ ዓይነቶችን ለማምረት በቅቷል። ስለሆነም በመሠረቱ ሰብ ነክ ያልሆነው ዘር፣ የተለያዩ ቀለማትን ለማግኘት የሚያስችል በራሂዎች አሉት ማለት ነው፤ ይህም እንደ ብዝሃ ሕይወት ባለሀብትነት፣ አቅም፣ ይወሰዳል። በማዳቀል/ማዋለድ ሂደት የተፈለገውን ቀለም ለማግኘት (ቢጫ፣ ቀይ፣ ወይን ጠጅ፣ ወዘተ.) የሚያስችሉ በራሂዎቸን መርጦ፣ የተፈለገውን ዓይነት ጽጌረዳን ማምረት ይቻላል።

እንዲሁም ለዓለም ገበያ የሚውል አበባ ሲመረት፣ ከተፈላጊው የአበባ ቀለም ዓይነት በተጨማሪ፣ በቶሎ የማይጠወልግ እንዲሆን ይፈለጋል። በዚህ ሂደት የአበባውን መዓዛ ልናጣ እንችላለን። ሽታ አልባ ወይም መዓዛው ውስን የሆነ አበባ ነው ለማምረት የምንገደደው። ምክንያቱም በትነት የአበባ መዓዛ አመንጪ የሆኑ የተፈጥሮ ዘይቶች፣ ከአበባው በቶሎ ከመጠውለግ ጋር የተዛመዱ ስለሆኑ፣ በምርጫ ተግባር የአበባ ዘይቶች፣ በመትነን የአበባን ሽታ የሚያበረክቱት መጠን በጣም እንዲቀንስ ይደረጋል፣ ብሎም የአበባ የሚያውድ ሽታ ይደበዝዛል።

በአገራችን ለምግብነት ከምንጠቀምባቸው የእፅዋት ዝርያዎች አተርን እንወስድ። ምርጥ የአተር ዘር ብለን የምናውቀው አተር ቀደም ሲል ከነበረ የአተር ዘር በማዋለድ የተገኘ ነው። ግኝቱንም የወሰኑት የበራሂ ዓይነቶች ናቸው፣ ስለሆነም በራሂዎች ናቸው የተመረጡት ማለት ነው። የተመረጠው አተር ምንም መጠኑ ካልተመረጠ የአተር ዘር ጋር ሲነፃፀር የላቀ ቢሆንም፣ በመምረጥ ሂደት ከነባር ባህርዮች የምናጣቸው ሊኖሩ ይችላሉ። ለምሳሌ በአገራችን ያለው የአተር ምርጥ ዘርን ተመጋቢዎች የለመዱት ጣእም የለውም፣ ነባሩም ቀለም በመጠኑ ይቀየራል። ስለሆነም ጣፋጭነትን የሚወስኑ ባህርያትንም ሊያጣ ይችላል። ይህ እጦት ለምርት መጠን ብዛት የሚከፈል እዳ ነው፤ ያም ነፃ የሚባል ምግብ የለም፣ ይከፈልበታል፣ እንደ ማለት ሊታይ ይችላል።

ከእንስሳት ዓይነት ምሳሌ ብንወስድ፣ ውሻን ማዳቀል አንዱ ሊሆን ይችላል። ውሻ እና ተኩላ አንድ ብቸኛ ዝርያ(species) ናቸው፣ ማለትም ተኩላ እንዳልተላመደ ውሻ ይቆጠራል። ከነባሩ የውሻ ዝርያ(wild)፣ ማለት ገና ሰበ ነክ ካልነበረው የውሻ ዘር ሃበለ በራሂ ቋት በማዋለድ ሂደት፣ የተፈለገውን ዓይነት ውሻ፣ የተለያዩ ተክለአቋም እና መጠን ያሏቸው የውሻ ዓይነቶች ለማግኘት ተችሏል። እነሱም ድመት አከል፣ ድመት መሰል ድንክዬ፣ ወይም አንበሳ መሰል ግዙፍ አውሬ መሰል ሊሆኑ ይችላሉ። ስለሆነም ብዝሃ ሕይወት ለተለያዩ ሕያው ገላጭ ለሆኑ ተግባራት እንደ ግዙፍ ቋት ሊመሰል ይችላል። በርቢ ጊዜ የሚፈለገውን ባህርይ ለማግኘት፣ ወሳኝ የሆኑት በራሂዎች ናቸው የሚመረጡት። ሰበ ነክ ካልነበረ ውሻ ውስጥ የነበረው ብዝሃ ሕይወት፣ በርቢ ከተመረጡት የውሻ ዓይነቶች የበራሂ ቅልቅል በጣም የላቀ ነው። በሰበነክ ምርጫ ብዙ በራሂዎች ይታጣሉ።

በራሂዎችን በሸማኔ ባለቀለም ክሮች ብንመስላቸው የሚፈለገውን ጥለት ለማግኘት፣ ተፈላጊ የሆኑ ቀለማት ያሏቸውን ክሮች መምረጥ ይገባናል። በተመረጡ የክር ቀለሞችም የተለያዩ ዓይነት የልብስ ጥለቶችን ለመሸመን እንችላለን። በበራሂዎች ምርጫም የተፈለገው ባህርይ ያሏቸውን ሕያው አካላት ማግኘት ይቻላል።

ብዝሃ ሕይወት ለብቸኛ ዝርያውም ጥቅም አለው፣ ይህን ገላጭ የሆነ አንድ ምሳሌ እንውሰድ። በእንግሊዝ አገር ቅድመ-ኢንዱስትሪ አብዮት አንድ የእሳትራት ዝርያ ነበረች። የዝርያዋ አባላትም ብዙዎቹ ክንፎቻቸው ወደ ነጭ ያደላ ቀለም ያለው ነበር፣ ያም እሳትራቶች የሚያርፉበትን የዛፍ ቅርፊት ቀለም መሰል ነበር። ስለሆነም የሳትራት-በል ወፎች፣ ዛፎች ቅርፊት ላይ ያረፉትን የሳትራቶች በቀላሉ ለማየት ይሳናቸው ነበር። ጥቂት ቢሆኑም አንዳንድ ጠቆር ያለ ቀለም ክንፍ ያሏቸው በማኻላቸው ይገኙባቸው ነበር። ስለሆነም የብቸኛ ዝርያው ብዝሃ ሕይወት ጥቁርም ነጭ ቀለም ክንፍ ያሏቸው አባላት ነበሩት። አእዋፍ ጠቆር ያለ ቀለም ያላቸውን በቀላሉ ለማደን ይችላሉ፤ ይህም የሆነበት ምክንያት በነጭ ቅርፊት ላይ ያረፈን ጥቁር ክንፍ ያለው የሳትራት በቀላሉ ለማየት ስለሚቻል ነበር።

በኢንዱስትሪ አብዮት መንስዔ፣ የእንግሊዝ ገጠር አካባቢ በኢንዱስትሪ ጢስ ሲበከል፣ የአካባቢ ዛፎች ቅርፊት በጥላሸት መሸፈን ጀመረ። በዚህን ጊዜ የሳትራት አዳኝ አእዋፍ ነጭ ክንፎች የነበሯቸውን የሳት ራቶች በቀላሉ ለማየት፣ ብሎም ለማደን በቁ። በአንፃሩ ጥቁር ክንፎች የነበሯቸው አባላት፣ ከአእዋፍ እይታ ተሰወሩ፣ ብሎም ከመታደን ተረፉ። በሂደት በአካባቢው በብዛት የሚታዩት ባለ ጥቁር ክንፍ የሳትራቶች ሆኑ። በዚህ ሂደት የሳትራት ዘር እንዳይወድም የብዝሃ ሕይወት ሀብት ስብጥር ታደገው ማለት ነው።

## የቁልፍ ብቸኛ ዝርያዎች (Keystone Species) ጉዳይ

በአንዳንድ አካባቢዎች ብዙ ውስብስብ ተግባራትን የሚያከናውኑ ሕያው አካላት አሉ። እነኝህ ዓይነቶች ሕያው አካላት ቁልፍ ብቸኛ ዝርያዎች ይባላሉ። እንደ አካባቢውም ሕያው መዋቅር ዋልታ ተደርገው ይወሰዳሉ፤ እንዲሁም እንደ የማዕዘን ድንጋይ ይመሰላሉ። እንደ ዋልታ የሚመሰለው፣ ብቸኛ ዝርያ የሚያከናውናቸውን ተግባራት፣ እሱን ተክቶ ለማከናወን የሚችል ሌላ ዝርያ በአካባቢው አለመገኘቱ፣ ተኪ አልባ መሆኑ

ነው። በማዕዘን ድንጋይ የሚመሰለውም፣ የማዕዘን ድንጋይ ሾልኮ ከወጣ፣ ሕንፃው(ቤቱ) ስለሚናድ ነው። ቁልፍ ብቸኛ ዝርያዎች ሲጠፉ የአካባቢው ሚዛናዊ ሁኔታ ይናዳል፣ ትስስሩ ይበጠሳል።

ለምሳሌ ንቦች ለጥቂት የእፅዋት ዝርያዎች፣ ርቢ ሂደት ወሳኝ ሚና አላቸው። ንቦች ከአካባቢ ቢጠፉ፣ የብዙ እፅዋት ዝርያዎች ርቢ/ስነ ተዋልዶ ሥርዓት ይቃወሳል። ምክንያቱም ንቦች ናቸው የአበባ ወለላ(nectar) በመቅሰም ላይ ሲሰማሩ፣ ከአንድ የባለ አበባ እፅ፣ ፅጌ ብናኝ(pollen) ወስደው፣ ለሌላ ባለ አበባ እፅ የሚያበረክቱት፣ ሂደቱም ርክበ ብናኝ(pollination) በመባል ይታወቃል። የወንድ አባለ ዘር የሚገኘው በፅጌ ብናኝ ይዘት ውስጥ ነው። ንቦች በአካባቢው ከሌሉ ይህ የመዋለድ ተግባር ይስተጓጎላል። በዚህ መንስዔ አንዳንድ የእፅዋት ዝርያዎች ለውድመት ይዳረጋሉ።

እንደዋልታ የሚመሰሉት ሕያው አካላት፣ በተለያዩ ተግባራት የተሠማሩ ሊሆኑ ይችላሉ። አዳኝ ሥጋ በል፣ ለምሳሌ ድመት፣ የአይጥ ዝርያዎች ተራብተው ቁጥራቸው ከመጠን በላይ እንዳይገር ይቆጣጠራል። አይጥ ካለ ገደብ መራባት ለብዙ የአካባቢ ሚዛን መዛባት (የበሽታ ስርጭት፣ የሀብት መውደም፣ ወዘተ.) ምክንያት ሊሆን ይችላል።

## በዘመናቱን ብዝሃ ሕይወት ሀብት መመናመን

ለብዝሃ ሕይወት መጎሳቆል፣ መመናመን ብዙ ምክንያቶች አሉ። ይህም የተፈጥሮ አንዱ ሂደት እንደሆነ ይታወቃል። በራሂዎች ይከስማሉ፣ ብሎም በአዳዲስ በራሂዎች ይተካሉ፤ ይህ ተግባር የዝግመተ ለውጥ(evolution) መሠረት ነው። እንደውድመት የሚቆጠረው ግን ሰበ ነክ የሆነው ነው። ብዝግመተ ለውጥ የሚከሰተው በራሂዎች መክሰም፣ ሰበ ነክ ከሆነው ጋር ሲነፃፀር በጣም ኢምንት ነው። ሰበ ነክ የሆነው የበራሂዎች ውድመት፣ በተፈጥሮ ከሚከሰተው በሙቶ እጥፍ ከፍ ያለ ነው።

የሰው ልጅ በገፀ ምድር ከተከሰተ ጀምሮ የብዝሃ ሕይውት ሀብት ተፈጥሮ ካሰናዳለት ፈር ወጣ እያለ መሄድ ጀምሯል። ለምሳሌ በእንስሳት ርቢ የሚፈለገውን ባህርይ የሚያበረክቱ (ፈጣን ፈረስ፣ በዛ ያለ ወተት የሚታለብ ላም፣ ወዘተ.) ለማግኘት እንስሳትን ማርባት፣ ብሎም ማዳቀል፣ እፅዋትን ማላመድ፣ እንዲሁም በእፅዋት ውጤቶች አጠቃቀም (ማገዶ፣ ቤት መሥራት፣ ቁሳ ቁስ ከእንጨት ውጤቶች ማበጀት፣ መፈብረክ፣ ወዘተ.)፣ የከባቢን አየር መበከል፣ እና መሰል ተግባራት በብዝሃ ሕይወት ሀብት አሉታዊ ተፅዕኖ አድርሷል። ጥቂት እንስሳትን ወይም እፅዋትን ለይቶ ለሰው ልጅ ምግብ ፍጆታ ማሟያ ማድረግም፣ እፅዋቱን ወይም እንሰሰቱን ለውድመት ይዳርጋል።

ሰበ ነክ ለሆኑ ውድመቶች ምክንያቶች ብዙ ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹ ደን መጨፍጨፍ፣ ረግረግ ቦታዎችን አጠንፍፎ ለግብርና ወይም ለሌላ ተግባር ማዋል (ረግረግ ቦታ እንደ ጉበት ይመሰላል፣ ያን ዓይነት አካባቢ ከፍተኛ የባክቴሪያ/የሚክሮብ ዝርያዎች የሚገኙበት ሲሆን፣ እነኝህ ሚክሮቦችም ጎጂ ኬሚካላዊ ውህዶችን የማስወገድ/ የማውድም ባህርይ አሏቸው)፣ የዱር እንስሳት እና የእፅዋት የሆነውን ክልል ጥሶ በመግባት እና አካባቢውን በመመንጠር፣ ሰፋፊ እና የተንጣለሉ የመኖሪያ ሰፈሮችን በመመሥረት ምክንያት የነባር ሕያው አለኝታን ማጎሳቆል እና አካባቢውን ሚዛን ማዛባት ናቸው።

በአካባቢው ነባር ያልሆኑ እፅዋትን ሆነ እንስሳትን ወደ አዲስ አካባቢ በማስገባት፣ ነባር ባለቤቶችን ለውድመት ይዳርጋል። ይህም በአውስትራሊያ ክፍለ ዓለም በገሃድ ታይቷል። ያም የሚከሰተው መጤዎችን የሚያጠቁ ሌላ ሕያው አካል በአዲሱ አካባቢ አለመኖራቸው ነው (የበሽታ መንስዔም ሆነ፣ መጤዎች ለምግብነት የሚጠቀም፣ ወዘተ.)።

ኬሚካላዊ ብክለትም ለብዝሃ ሕይወት ውድመት አንዱ ምክንያት ነው። ለምሳሌ የወባ ትንኝን ለመከላከል የሚረጨው "ዲዲቲ"(D-DT) ለአካባቢ ኬሚካላዊ ብክለት አንድ ዋና መንስዔ ሆኖ ስለተገኘ፣ በብዙ አካባቢዎች በዚህ ኬሚካላዊ ውሁድ መጠቀም የተወገዘ ነው። ከኢንዱስትሪ የሚመነጩ ኬሚካላዊ ውሁዶች ለአካባቢ ብክለት፣ ብሎም ለብዝሃ ሕይወት ውድመት መንስዔዎች ናቸው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአየር ቅጥ/ንብረት ለውጥ(climate change) ለብዙ ሕያው ውድመት መንስዔ እየሆነ መጥቷል። የአየር ቅጥ ለውጥ የሚያስከትለው ዋናው ችግር ድርቅ ሲሆን፣ በድርቅ መንስዔ ብዙ ብቸኛ ዝርያዎች(እፅዋት እና እንስሳት፣ ወዘተ.) ለመመናመን፣ ከዚያም ባለፈ ለውድመት ይዳረጋሉ። በአየር ቅጥ ለውጥ መንስዔ የአካባቢ ሙቀት ሲጨመር፣ አንዳንድ አካባቢዎች ለወረራ ይጋለጣሉ፣ ለምሳሌ የወባ ትንኝ ወደ ደጋ አካባቢዎች መዛመት።

## በኢትዮጵያ ብዝሃ ሕይወት ሀብት ችግሮች መከሰት ምክንያቶች

የብዝሃ ሕይወት መጎሳቆል ዋናው መንስዔ የሰው ልጅ የሚያከናውናቸው ተግባራት ናቸው፣ ማለት ችግሩ ሰበነክ ነው። ሰው በበዛ መጠን ለእርሻ የሚውለው መሬት ስፋት ይጨምራል። በኢትዮጵያ ለከብት መዋያ ያገለግል የነበረው፣ መታረስ የማይገባው ተዳፋት መሬት ተመንጥሮ ወደ ሰብል ማምረቻነት ተቀይሯል። እንዲሁም ወንዝ አጠገብ ያለው ውሃ-አዘል መሬት ሁሉ ወደ ማሳነት/ወደ እርሻ መሬትነት ተቀይሯል። ከብት የሚሰማራበት ቦታም እየጠበበ ሄዷል። ባለንበት ወቅት፣ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ወይናደጋ እና ደጋማ ቦታዎች የሚገኙ የከብት ማሰማሪያ ቦታዎች በብዙ እጅ ቀንሰዋል። ስለሆነም፣ የቤት እንስሳት በቂ መኖ አያገኙም፤ በቂ ምግብ ካላገኙ ምርታማነታቸውም ሆነ ጉልበታቸው ይቀንሳል። በሂደት እፅዋት እየተጨፈጨፉ ነው።

ሃሩር ቢፈጃቸው፣



በአፈር ጥበቃ እና በዛፍ ተከል የብዝሃ ሕይወት ማገገሚያ ተግባር

የሳቶችን እናት፣ ፀሐይቱን ሸሽተው፤
እንስሳት በሙሉ፣ ከዛፍ ስር አረፉ፤
ምሳር ሲያሳድደው፣ የት ይሸሽግ ዛፉ።
(ስብስብ ግጥሞች-በውቀቱ ስዩም ስንኝ በግርድፉ የተዘረፈ...)

የሕዝብ ብዛት ብቻውን የአካባቢ ቀውስን አያስከትልም። ነገር ግን ሕዝቡ የድህነት ሰለባ ከሆነ በአካባቢ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ ያደርጋል። ሕዝብ ሲበዛ፣ ተጨማሪ ማሳ፣ ተጨማሪ ጎጆ፣ ተጨማሪ ምግብ ማብሰያ ማገዶ ያስፈልጋል። ይህም ሂደት በአካባቢው ያለውን የተፈጥሮ ሀብት ያመናምነዋል፣ ሥርዓተ ምህዳሩንም ያቃውሳል። የድህነት ሰለባ የሆነው ማህበረሰብ ኑሮውን በቀጥታ ከመሬት በሚገኝ የተፈጥሮ ሀብት ላይ እንዲመሠረት ይገደዳል። የሕዝቡ ብዛት በጨመረ መጠን በየቤቱ የሚሰማው ሮሮ፣ ምግብ ሳያልፍበት የሚውለው/የሚያድረው ጉሮሮ ይበረክታል። ያም ለተጨማሪ የአካባቢ መጎሳቆል መንስዔ ይሆናል፣ ሂደቱ አዟሪት መሰል ነው።

ከላይ የተደረደሩት ችግሮች ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በመጠኑም ቢሆን ቀንሰዋል። ይህ ማለት ከችግሩ ተላቀናል ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ያሻል። ከችግር የመላቀቅ ጥረቱ ኅብረተሰቡን በጠቅላላ ባሳተፈ መልኩ ነገ ዛሬ ሳይባል መቀጠል ይኖርበታል።

## የኢትዮጵያ የብዝሃ ሕይወት ሀብት እና እንክብካቤ /ጥበቃ/

በእፅዋት ይዘት ያለው የኢትዮጵያ ብዝሃ ሕይወት ሀብት መጠነ ሰፊ ነው። በኢትዮጵያ ከስድስት ሺ እስከ ሰባት ሺ የሚገመቱ የእፅዋት ብቸኛ ዝርያዎች አሉ። ከነኝህ በመቶ አሥሩ(10%) ኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ "አገሬ"(indigenous species) ዝርያዎች ናቸው። እንዲሁም 284 አጥቢ የዱር እንስሳት፣ 861 የአእዋፍ ብቸኛ ዝርያዎች፣ 201 የገበሎ አስተኔ ብቸኛ ዝርያዎች፣ 200 ገደማ የዓሣ ብቸኛ ዝርያዎች፣ 63 የእንቁራሪት አስተኔ ብቸኛ ዝርያዎች አሉ። ከነዚህ 29 አጥቢ ብቸኛ ዝርያዎች፣ 18 የአእዋፍ ብቸኛ ዝርያዎች፣ 10 የገበሎ አስተኔ ብቸኛ ዝርያዎች፣ 40 የዓሣ ብቸኛ ዝርያዎች እና 25 የእንቁራሪት ብቸኛ ዝርያዎች በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ "አገሬ" ዝርያዎች ናቸው። ስለ ሦስት አፅቄዎች(insects) ብዙ መረጃ ባይኖርም፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ብዙ እንዳሉ ይገመታል።

ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያ በአዝርእት ብዝሃ ሕይወት የከበረች ናት። ስለሆነም በዓለም ደረጃ "የብዝሃ ሕይወት ማዕከል" ተብላ ተመድባለች። በዓለማችን ካሉ ሀብታም የአዝርእት ብዝሃ ሕይወት አካባቢዎች ተብለው ከተመደቡት ከአሥራ ሁለቱ "የቫቪሎቭ ማዕከሎች" አንዷ ኢትዮጵያ ናት። ኢትዮጵያ "የአረቢካ ቡና"(Coffee arabica) ዋና የብዝሃ-ሕይወት ማዕከል ናት። በተለያዩ ደረጃዎችም ቢሆን (የብዝሃ-ሕይወት ክምችት መግለጫ ደረጃዎች አሉ)፤ የጤፍ፣ የእንሰት፣ የአንጮቴ፣ የሰናፍጭ፣ የማሽላ፣ የአጃ፣ የአተር፣ የኑግ እና የሰሊጥ ዋና ዋና ማዕከሎች ከሚባሉት አንዷ ናት።

የብዘሃ ሕይወት ሀብት እንዳይመናመን፣ ማለት በያንዳንዱ ብቸኛ ዝርያ በራሂ ይዘት እንዳይመናመን፣ እንዳይቀንስ፣ እንዳይጠፋ ለማድረግ እየተሞከረ ነው፡፡ እንዲሁም ለአካባቢ ተገቢውን ክብካቤ ለማድረግ በሥርዓት ምህዳር የታመቀው የብዝሃ ሕይወት ሀብት እንዳይመናመን ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ የብዝሃ ሕይወት ሀብት እንክብካቤ ሁለት ዋና ዋና ስልቶች ያሉ ሲሆን፣ አንዱ ሀብቱን በነባር አካባቢው፣ በሚገኝበት አካባቢ ተገቢው ክብካቤ የማድረግ ዘዴ ነው(in situ conservation)፡፡ ለዚህም ምሳሌ የሚሆኑት በብዙ አካባቢ የተመሠረቱት የዱር እንስሳት ጥብቅ አካባቢዎች(wildlife parks/zoological parks/sanctuaries) እና ጥብቅ ደኖች ናቸው፡፡ ሁለተኛው ዘዴ ደግሞ ከነባር መኖሪያ አካባቢ አውጥቶ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ሥርዓት ብዝሃ ሕይወትን ከውድመት መታደግ ነው(ex situ conservation)፣ ለዚህም ተምሳሌቶች የበራሂ ባንኮች(gene banks) እና የእፅዋት ማዕከሎች(botanical gardens) ናቸው፡፡ ለዚህ ተግባር አካባቢው እንግዳ አይደለም፣ ምክንያቱም ለተግባሩ ቀዳሚ ተዋናይ የነበሩ ብዙ የእምነት ማዕከላት በኢትዮጵያ ስለሚገኙ ነው፤ እነሱም እንደ እፅዋት ማዕከላት ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡

ኢትዮጵያ ብዝሃ ሕይወትን ለመታደግ ተቋማትን መሥርታለች፣ ፖሊሲዎች፣ ሕግጋት እና ደንቦችን አውጥታለች፡፡ ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ፣ የብዝሃ ሕይወት ተቋም(Institute of Biodiversity) መመሥረት፣ የብዝሃ ሕይወት ጥበቃ ስትራቴጂ መንደፍ፣ የተግባር እቅድ ማውጣት(National Biodiversity Strategy and Action Plan)፣ የዱር እንስሳት ጥብቅ አካባቢዎች(Protected areas) መመሥረት ናቸው፡፡ ከኢትዮጵያ ገፀ ምድር አሥራ አራት በመቶው(14%) በተለያዩ ደረጃዎች የእንስሳት ጥበቃ አካባቢዎች ተመሥርተዋል፡፡ እንዲሁም ከአገሪቱ ገፀ ምድር አሥራ አምስት ተኩል በመቶ(15.5%) በተለያዩ ደረጃዎች የእፅዋት ጥበቃ አካባቢዎች ተመሥርተዋል፡፡

በበራሂ ባንኮች(Gene banks) ወደ 494 የእፅዋት ብቸኛ ዝርያዎች በነባር አካባቢዎቻቸው ጥበቃ እየተደረገላቸው ነው። ከነዚህም 297 የዛፍ ዝርያዎች እና 13 የቤት እንስሳት ዝርያዎች ናቸው። ብዙ የሰብል ዝርያዎች በዚሁ መንገድ ክብካቤ እየተደረገላቸው ነው። እንዲሁም 275 የእፅዋት ዝርያዎች ለመድኃኒትነት የሚያገለግሉ በበራሂ ባንኮች ጥበቃ እየተደረገላቸው ነው። በተጨማሪ 460 ብቸኛ እፅዋት ዝርያዎች ለዚሁ

ተግባር በተዘጋጀ ቀዝቃዛ አካባቢ በበራሂ ባንኮች ይዘት እየተጠበቁ ነው፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በትምህርት እና ምርምር መዋቅሮችም ለብዝሃ ሕይወት ክብካቤ ትኩረት እየተሰጠ ነው፡፡ በተለይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና በሃሮማያ ዩኒቨርሲቲ ለዚህ ተግባር ልዩ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ በጉለሌ የሚገኘው “የእፅዋት ማዕከልም” የዚህ ተግባር አካል ነው፡፡ እንዲሁም ስለ ብዝሃ ሕይወት ክብካቤ ብሎም ጥቅማ ጥቅም ማህበረሰቡ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

ዓለም አቀፍ የሆኑ የተለያዩ ስምምነቶች፣ በብዙ አገሮች(መንግሥታት) ተቀባይነት አግኝተው የብዙ አገሮች የሕግ አካላት ተደርገው ተወስደዋል፡፡ ስምምነቶቹም ለብዝሃ ሕይወት ክብካቤ እና ጥበቃ ልዩ ትኩረት ሰጥተው በፈረሙት መንግሥታት እየተተገበሩ ይገኛሉ፡፡ ብዝሃ ሕይወትን ለመንከባከብ ትኩረት የሰጡ ተቋማትም ተመሥርተዋል፡፡

በተቋም ደረጃ እንደ የዩኔስኮ “የሰው ልጅ እና ሕያው አካባቢውን”፣ “የዓለም የተፈጥሮ ሀብት ተቋም”፣ “የእፅዋት ብዝሃ ሕይወት ቦርድ” እና መሰሎች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በስምምነት ደረጃ የአእዋፍ ጥበቃ፣ ለውድመት የተቃረቡ ብቸኛ ዝርያ ንግድ፣ የሕያው ክብካቤ፣ “የራመሳር ረግረግ አካባቢዎች ጥበቃ”፣ “የአፍሪካ የሕያው እና ተጓዳኝ ሀብት ጥበቃ”፣ “የካርታጀና ሕያው ነክ አጠቃቀም ጥንቃቄ ዙሪያ”፣ “የብዝሃ ሕይወት ጥበቃ ስምምነት” እና መሰሎቹ ይገኙባቸዋል፡፡ ለብዝሃ ሕይወት ክብካቤም ተግባር የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ጠቅለል ተደርገው ሲታዩ፣ ስምምነቶችም ሆኑ ተቋማቱ ትኩረት የሰጡት ለብዝሃ ሕይወት ጥበቃ እና ክብካቤ ነው፡፡

የብዝሃ ሕይወት እንክብካቤ አሁን ላለው ትውልድ ብቻ ሳይሆን፣ ገና ወደፊት ለሚመጣው ተከታታይ ትውልድ ፋይዳ ያለው ተግባር ነው፤ ስለሆነም ነው የብዝሃ ሕይወት እንክብካቤ አስፈላጊ የሆነው፡፡ እንዲሁም ብዝሃ ሕይወት ሲወድም ጥቅማ ጥቅሙ ሳይታወቅ ሊወድም የሚችል የተፈጥሮ ሀብት አለ፡፡

## መደምደሚያ

በኢትዮጵያ የብዝሃ ሕይወት ሀብት አካባቢ ያሉ ተግዳሮቶች እየተገመገሙ፣ ችግሮችን ለመታደግ የሚበጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች እና ደምቦች እያዘጋጁ ወደ ተግባር መቀየር ይገባል፡፡ ከዚያም ባለፈ “ሳይንሳዊ አስተሳሰብን በማስገዘብ(ሕዝባዊ በማድረግ)”፣ እንዲሁም ሳይንሳዊ አስተሳሰብን የባህላችን አካል በማድረግ፣ ችግሩን በማህበራዊ ደረጃ ልንገታው እንችላለን፡፡ “ሳይንሳዊ አስተሳሰብ” ማለት በሳይንሳዊ አስተሳሰብ ዘዴዎች መጠቀምን እንጂ የዕውቀት ዘርፍን አያመላክትም፡፡

የሳይንሳዊ አስተሳሰብ አንዱ ዋና ዓላማ፣ አንድን ጉዳይ፣ ተግባር፣ ወዘተ. ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለማየት ማስቻሉ ነው፡፡ ስለሆነም ሳይንሳዊ አስተሳሰብ የሚያበረክትልን እይታ አድማሱም ሆነ ጥራቱ፣ ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ካላዳበረ አስተያየት ጋር ሲነፃፀር፣ በጣም የላቀ ነው፡፡ የማንኛውም የዕውቀት ዘርፍ የመረጃ አሰባሰብም ሆነ በመረጃ ላይ ተመርኩዞ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚጠቀምበት ዘዴ ሆነ ሂደቱ የሚስተናገደው በ “ሳይንሳዊ አስተሳሰብ” ነው፡፡

የአገራችን ዓበይት ችግርች ናቸው ተብለው ከሚወሰኑት ጉዳዮች መኻከል፣ አገሪቱ ያላት የተፈጥሮ ሀብት ብሎም ብዝሃ ሕይወት በከፍተኛ የውድመት ሂደት ያለ መሆኑ ነው፡፡ የዚህ ውድመት መከሰቻው የለም አፈር መታጠብ፣ የመሬት የእፅዋት አልባሳት መመናመን፣ በአንዳንድ ቦታዎች የምድር አልባስ ጨርሶ መጥፋቱ፣ ምንጮች ብሎም ወንዞች መድረቃቸው፣ ወዘተ. ናቸው፡፡ ችግሮቹ ውስብስብ እና ተመጋጋቢ ስለሆኑ፣ የርስ በርስ ግንኙነቶችም አሏቸው፡፡ እነዚህ እና እነዚህን የመሰሉ ችግሮች ተደራርበው ከፍተኛ የሰው ምግብ እና የከብት መኖ እጥረት(እጦት)፣ የመጠጥ (ውሃ) መጥፋት፣ የማገዶ ችግር እና ተመሳሳይ ሌሎች ችግሮች በኢትዮጵያ እንዲከሰቱ አድርገዋል፡፡

> **የባህልን ለውጥ ለማምጣት ከሚያገለግሉ መድረኮች ዋነኛው ትምህርት ቤት ነው። በትምህርት ቤት ውስጥ፣ ከትምህርት ጋር አቀናጅቶ ጥሩ ጥሩ ልማዶችን/ ባህሎችን መመሥረት ብሎም ማዳበር ይቻላል**

የተፈጥሮ ሀብት መመናመኑ እንዳይቀጥል መደረግ እንዳለበት በማመን፣ በብዙ አካባቢዎች የእርከን ግንባታ እና በተለይ በቅርብ ጊዜ የእፅዋት ተከላ ቢከናወንም፣ የተደረጉት ጥረቶች ተገቢውን (የሚጠበቀውን) ውጤት ገና አላመጡም፡፡ የሂደቱ አንዱ እንቅፋት፣ ጥረቱ/ ሙከራው በባህል/ ልማድ ላይ የተመሠረተ አለመሆኑ ነው፡፡ ችግሩን ለመፍታት ግን መጀመሪያ በተፈጥሮ ሀብት ክብካቤ ዙሪያ ባህላዊ ለውጥን ማምጣት ያሻል፡፡ መጥፎ ልማድን ለማስጣል እና በምትኩ ጥሩ ልማድን ለመተካት፣ የለውጥ መሠረታዊ ግብዓቶች(አንቀሳቃሾች/ ሞተሮች) ትምህርት ብሎም ዕውቀት/ ክህሎት ናቸው፡፡ ጉዞውም ረጅም ነው፣ አርቆ ማየት ያሻል፡፡

ስለሆነም የባህልን ለውጥ ለማምጣት ከሚያገለግሉ መድረኮች ዋነኛው ትምህርት ቤት ነው፡፡ በትምህርት ቤት ውስጥ፣ ከትምህርት ጋር አቀናጅቶ ጥሩ ጥሩ ልማዶችን/ ባህሎችን መመሥረት ብሎም ማዳበር ይቻላል፡፡ በብዙ አገሮች የተፈጥሮ ክብካቤ ባህል የሚዳብረው በክለቦች አማካኝነት ነው፡፡ ስለሆነም፣ በየትምህርት ቤቱ አንዳንድ የተፈጥሮ ክብካቤ ክለቦች፣ በብቸኝነትም ሆነ፣ ከሳይንስ ክለቦች ጋር ተቀናጅተው በጣምራ እንዲመሰረቱ ጥረት ማድረግ ያሻል፡፡ የተመሠረቱም ካሉ እንዲጎለብቱ ማድረጉ ይበጃል፡፡ ተግባሮችም እንደየአካባቢው፣ ከአካባቢው ባህል፣ ማህበራዊ ኑሮ ጋር እየተዛመዱ፣ አመቺነታቸው እየተቃኘ፣ ተስማሚነታቸው እየተመረመረ፣ እየጠለለ ሥራ ላይ ሊውሉ(ሊተገበሩ) ይገባል፡፡

እነኝህን እና እነኝህን መሰል ተግባሮች ዛሬ ነገ ሳይባል በማከናወን፣ ከከፍተኛ የሕልውና ሥጋት መላቀቅ ይቻላል፡፡

# አዲስ ሥርዓተ-ትምህርት ለምን ?

**ንጉሤ ተስፋዬ**

ሥርዓተ ትምህርት በትምህርት ተቋማት አማካይነት እንዲመጣ የሚፈለገው ለውጥ የሚመራበት ሳይንስ ነው። ለውጡ ደግሞ በተማሪዎች በኩል መታየት አለበት። የባህርይ፣ የአመለካከት፣ የክህሎት መዳበር፣ዕውቀት የመፍጠር አቅም ለውጦች የሚመሩበት ሥርዓት፤ የትምህርት ተቋማት አስፈላጊውን አመለካከት እንዲያመጡ፣ተማሪዎች ዕውቀት እንዲፈጥሩ እና የክህሎት መዳበር እንዲኖራቸው ለማድረግ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ታቅዶ ትምህርት ቤቶች የሚመሩበትና ተግባራዊ የሚደረግበት መንገድ ነው ሥርዓተ ትምህርት።

በሥርዓተ ትምህርቱ እንዲመጣ የሚፈለገው ለውጥ ማዕከል የሚያደርገው በአንደኛ፣ በሁለተኛ እና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ከሚገኙ ተማሪዎች የአካል፣ የመንፈስና የአዕምሮ ዕድገት ጋር የሚያያዝ መሆን እንዳለበት የዘርፉ ምሑራን ይገልፃሉ። ተማሪዎችን በባህላቸው እንዲቀረጹ እና እንዲያድጉ የሚያግዝ፣ልጆች ሲያድጉ በአካል፣ በአዕምሮና በስሜት፣በሀገራቸው ባህል፣ ወግና ሥርዓት ስር እንዲሰዱ ለማድረግ ሥርዓተ ትምህርቱ ማኅበረሰቡንም ከግምት ማስገባት ይኖርበታል። ሥርዓተ ትምህርት ከሀገሪቱ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ፍልስፍና ጋርም መያያዝ መቻል አለበት። ሥርዓተ ትምህርት የአንድ ሀገር ማኅበረሰብ የደረሰበትን የዕድገት ደረጃ፣ ትውልዱ የሚገኝበትን የሥነ ምግባርና የግንዛቤ፣ እንዲሁም የማኅበረሰቡን ሁለንተናዊ የአኗኗር ደረጃ ታሳቢ አድርጎ ይቀረጻል። በወቅቱ የሚገኘውን የማኅበረሰቡን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ የዕድገት ደረጃ ከግምት ውስጥ ያስገባ፣በተለይም ሥርዓተ ትምህርት የነገውን ማኅበረሰብ የዕድገት ደረጃ የሚደግፍና የሚያፋጥን የትምህርት ሥርዓትን ታሳቢ ያደርጋል።

የትምህርት ዓላማም ለዕድገት፣ ለብልጽግና፣ ለለውጥ እና ለሽግግር ማብቃት ስለሆነ፣ትምህርት ከተማሪዎች እድገት፣ከወቅቱ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ለውጥ እና ከማኅበረሰቡ እሴት ጋር ተያይዞና ተጣጥሞ የሚሰጥ መሆን አለበት። በመዋዕለ ሕጻናት፣ በአንደኛ፣ በሁለተኛ እና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚሰጥ ሥርዓተ ትምህርትም በመሠረታዊነት ከተማሪዎች የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ጋር አብሮ የሚሄድ መሆን እንዳለበት ግልፅ ነው።

ከዚህ አንፃር የቆየው ሥርዓተ ትምህርት በርካታ ችግሮች እንደነበሩበት በጥናት ተረጋግጧል። በተካሄደው ጥናት የተገኘው ውጤት በዋናነት አራት መሠረታዊ ችግሮች የነበሩበት መሆኑን በአራዳ ክፍለ ከተማ የትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ወንድሙ ይመር ይገልጻሉ። የትምህርት ሥርዓቱ የሕግ ማዕቀፍ የሌለው መሆኑ፣ ሥርዓተ ትምህርቱ በራሱ ክለሳ የሚያስፈልገው መሆኑ፣ የትምህርት አደረጃጀቱ በተለይም መዋቅሩ አሁን



**አቶ ወንሙ ይመር**

> “ የቆየው ሥርዓተ ትምህርት በርካታ ቾግሮቹ እንዳነበሩበት በጥናት ተረጋግጧል።

ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር መከለስ ማስፈለጉ እና የትምህርት ፖሊሲም ለውጥ ማስፈለጉ ባለፉት ዓመታት ይተገበር የነበረው ሥርዓተ ትምህርትን ለመቀየር ምክንያት ሆነዋል።

አቶ ወንድሙ በዋናነት የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ ያስፈለገበትን መሠረታዊ ጉዳዮች ሲያብራሩም፣ አንደኛው ሥርዓተ ትምህርቱ በመጽሐፍ ዝግጅቶቹ የይዘት መጨናነቅ ይበዛበታል። ሁለተኛው ጉዳይ የሥርዓተ ትምህርቱ ይዘት ትኩረቱ ከተማሪዎች እና ከኅብረተሰቡ ሕይወት ጋር መቆራኘት አለመቻሉ ነው። ይህ ማለት ደግሞ የትምህርቱ ትኩረት በተማሪዎች ዕውቀት ላይ ብቻ እንጂ ተማሪዎቹን ወደ ተግባር የሚመራ አልነበረም። ሌላው ችግር ለሀገር በቀል ዕውቀት የሰጠው ቦታ ዝቅተኛ በሚባልበት ደረጃ ላይ መገኘቱ ነው። የሥነ ዜጋና ስነ ምግባር ትምህርትም ትኩረት የሚያደርገው መብት እና ግዴታዎች ላይ በመሆኑም ለግብረገብ ትምህርት የሚፈለገውን ቦታ እና ትኩረት የሰጠ አልነበረም። ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች፣ በተለይም ልዩ ተሰጥዖ ያላቸውን ተማሪዎች ሥርዓተ ትምህርቱ አላካተታቸውም የሚሉ ይገኙበታል።

አቶ አገኘሁ መለሠ ደግሞ በዳግማዊ ምኒልክ አጸደ ሕጻናትና የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት የመማር ማስተማር ምክትል ርዕሰ መምህር ናቸው። እንደሳቸው አስተያየት፣ የቆየው ሥርዓተ ትምህርት ከሥነ ምግባሩ ላይ ትኩረት አድርጎ ባለመሥራቱ ምክንያት ሀገራችን የሰለጠነ የሰው ኃይል ሳታጣ፣ ሥነ ምግባር የጎደለው ምሑር እየተፈጠረ ሀገሪቱን ለከፍተኛ ብጥብጥ ዳርጓታል ይላሉ። አቶ አገኘሁ አያይዘውም፣ አንዳንድ የትምህርት ዓይነቶች የተማሪዎችን አቅም የማያገናዝቡ፣ የትምህርት አሰጣጣቸውም ከከባዱ ወደ ቀላሉ የመሄድ

ሂደት ስለነበረው በችግርነት የሚነሱ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

የቆየው ሥርዓተ ትምህርት በአብዛኛው፣ በተለይም በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የማንበብ፣ የማስላት እና የመጻፍ ችግር የነበረበት መሆኑን የሚገልጹት ደግሞ በአጼ ናኦድ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ አሳየ የኋላሸት ናቸው። የመጽሐፍቶቹ አዘገጃጀትም ተማሪ ተኮር ከመሆን ይልቅ አስተማሪ ተኮር የነበሩ መሆኑን በተካሄደው ጥናት መረጋገጡን ያብራራሉ።

ዶ/ር በቀለ ወርቄ ደግሞ በኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ መምህር፣ ተመራማሪ፣የትምህርትና ስነ ባህርይ ጥናት ኮሌጅ ዲን ናቸው። እንደ ዶ/ር በቀለ አስተያየት ደግሞ የቆየው ሥርዓተ ትምህርት የሚከተሉት ችግሮች ነበሩበት፣ የመጀመሪያው ችግር ከእውነታዎች፣ ከመርሆዎች፣ ከንድፈ ሃሳቦች ጋር በተያያዘ፣ተግባርን ያገለለ የይዘት መታጨቅ ነው። ተማሪዎች በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ማነብነብ፣መግለጽ እና ችግርን መተንተን ቢችሉም ችግርን የመፍታት ብቃት ግን የላቸውም። ምክንያቱም ችግር እንዲፈቱ ሆነው አልተለማመዱም፣ንድፈ ሃሳቡን ወደ ትግበራ እንዲቀይሩት አልተማሩም። ስለዚህ ተማሪው ችግር ያወራል እንጂ ችግር ግን አይፈታም። በዋናነት ደግሞ ሥርዓተ ትምህርቱ የምዕራቡ ዓለም ተጽዕኖ ያጠቃው ስለነበር የማኅበረሰቡን ችግር በመፍታት እና የግለሰብን ሕይወት በማሻሻል ላይ ትኩረት አላደረገም።

ሥርዓተ ትምህርቱ የሥነ ምግባር ትምህርት ይዘትን በአግባቡ ባለማካተቱ ተማሪዎች ከባህል ያፈነገጡ፣ትውልዱን ደግሞ ከኢትዮጵያዊነት እንዲርቅ አድርጎታል። ችግሩ ደግሞ በየቦታው የሚስተዋል እና በወላጆች፣በመምህራን፣ እንዲሁም በማኅበረሰቡ የሚታይ ነበር። ይህ ደግሞ ሕጋዊነትን፣በተለይም አብሮ መኖርና መብላላት፣መተባበር፣መከባበር፣መደጋገፍ የሚባለውን ኢትዮጵያዊነትን አጥፍቶታል። በአብሮነት ውስጥም ልዩነት መኖሩን መገንዘብ እንዳይችሉ ሆነዋል።

የሕይወት ዘመን ክህሎትን በተገቢ ደረጃ ትኩረት ባለመስጠቱ፣ተማሪዎች ከሰው ጋር መግባባትና ሃሳባቸውን የመግለጽ ችግርም ታይቶባቸዋል። የኢትዮጵያን ሕዝብ ለዘመናት በሰላም አብሮ ላኖረው ለባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት፣ለሀገር በቀል ዕውቀት ቦታ አለመስጠቱም ሌላው የሚነሳ ችግር ነው። ተከታታይ የትምህርት ምዘናን በተመለከተም በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ይገለጽ እንጂ በተግባር እየተሰጠ አልነበረም። ተማሪዎቹን ዘላቂነት ባለው መልኩ በመፈተን ምን ውጤት አገኙ፣ምን ደካማ ጎን ነበረባቸው፣ምን መሻሻል አለበት፣ተማሪዎቹ እንዴት ይደገፉ የሚለው ነገር በአግባቡ አልተዳሰሰም።

በመሆኑም ይህን የትምህርት ጥራት ችግር ለማሻሻልና ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት ለመስጠት፣ ትምህርት ሚኒስቴር አዲስ ሥርዓተ ትምህርት አዘጋጅቶ ወደ ትግበራ ተገብቷል። በያዝነው 2015 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ



ዶ/ር በቀለ ወርቄ

እየተደረገ የሚገኘው አዲሱ ሥርዓተ ትምህርትም ተገቢውን ዕውቀትና ክህሎት ከሥነ ምግባር ትምህርት ጋር አጣምሮ ለመስጠት የሚያስችል ነው። በትምህርት ዘርፉ የሚታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት ቁልፍ ሚና እንደሚኖረውም በትምህርት ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ዴስክ ኃላፊ፣ ወ/ሮ ዛፉ አብርሃ መስከረም 6 ቀን 2015 ዓ.ም በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ አብራርተዋል።

እንደ ወ/ሮ ዛፉ አብርሃ ማብራሪያ፣ አምስት ዓመታትን በፈጀውና ከ3 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ የማኅበረሰብ ክፍሎች የተሳተፉበት አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት በርካታ ነባር ችግሮችን ይፈታል ተብሎ ይታሰባል። በዚህም በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ግብረገብ፣ ሀገር በቀል ዕውቀት፣ ሙያና የቀለም ትምህርት፣ ቴክኖሎጂ፣ ምርትና ተግባር፣ ጥናትና ምርምር ትኩረት አግኝተዋል። ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ላሉ የክፍል ደረጃዎች ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ይሰጣል። ከሰባተኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል ያሉት ተማሪዎች በእንግሊዘኛ ቋንቋ ይማራሉ። ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ እስከ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች የእንግሊዘኛ ቋንቋን እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ይወስዳሉ።

በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ሦስተኛ ክፍል ላይ በክልሎቹ ውስጥ በስፋት የሚነገረውን ተጨማሪ ቋንቋ በመምረጥ ተማሪዎቹ እንደ አንድ የትምህርት አይነት እንዲወስዱ ይደረጋል። 10ኛ ክፍል ይሰጥ የነበረው ሀገራዊ የመልቀቂያ ፈተና ቀርቶ፣ በክልል ደረጃ ስድስተኛ ክፍል፣ እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ ስምንተኛ እና 12ኛ ክፍል ላይ ይሰጣል። ሦስት ዓመት የነበረው የተማሪዎች የዩኒቨርስቲ ቆይታ፣ዝቅተኛው የቆይታ ጊዜ አራት ዓመት ይሆናል። ለሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በመጀመሪያ ዓመት ከሚሠጡ የትምህርት ዓይነቶች ውስጥ እንደ ጂኦግራፊ፣ አንትሮፖሎጂ፣ ሶሺዮሎጂና ሥነ-ምግባር የመሳሰሉት ይካተታሉ። ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል የግብረገብ፣ የማኅበራዊና የተፈጥሮ ሳይንስ ውሑድ ትምህርትም ይሰጣል።

ሰባተኛና ስምንተኛ ክፍል በተናጠል ይሰጡ የነበሩት ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪና ባዮሎጂ አጠቃላይ ትምህርት ተብለው፣ እንዲሁም ጂኦግራፊና ሂስትሪም ተቀናጅተው ይሰጣሉ። የእርሻ ትምህርት፣ አካውንቲንግ፣ ቢዝነስና ጀኔራል የሆነው የሥራና ክህሎት ትምህርት በሙያ ትምህርትነት ይካተትላቸዋል። 11ኛ እና 12ኛ ክፍሎች ላይ የጤና፣ የግብርና፣ የእርሻ፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ ኮንስትራክሽን፣ቢዝነስ፣ አካውንቲንግ የመሳሰሉት የሙያ ትምህርቶችን እንዲማሩ ይደረጋል።

የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍልን፣ እንዲሁም ከአንድ እስከ ስምንተኛ ክፍል ያሉ የተመረጡ አምስት የትምህርት አይነቶችን የመጽሐፍት ዝግጅት ትምህርት ሚኒስቴር ሲያከናውን፣ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ያለውን የትምህርት መጽሐፍት ክልሎች በራሳቸው ባህልና አካባቢያዊ ሁኔታ ቃኝተው ያዘጋጃሉ።

ምክትል ርዕሰ መምህር አቶ አገኘሁም፣ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ከቆየው በተለየ መንገድ፣በተማሪዎች ሥነ ምግባር ላይ ትኩረት ሰጥቶ የሚሠራ፣ከንድፈ ሃሳብ በዘለለ ተግባር ላይ ያዘነበለ፣ በተለይም ተማሪዎች ሰባተኛ እና ስምንተኛ ክፍል ላይ ሲደርሱ ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ የሚያግዝ መሆኑን ያስረዳሉ። ከዚያም አልፎ የአንድ ሀገር ትምህርት የአገሪቷን ነባራዊ

ሁኔታ፣ወግ፣ባህል፣እሴት፣ አኗኗር፣ወዘተ መሠረት አድርጎ መቀረጽ ስለሚኖርበት ሀገር በቀል ቋንቋዎች እንዲካተቱበት የተደረገበት ሁኔታ በጠንካራ ጎኑ ሊታይ እንደሚገባው ይናገራሉ።

በተመሳሳይ መንገድ ርዕሰ መምህር አቶ አሳየም፣ በተሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናና በተካሄደው ውይይት አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት ከገሃዱ ዓለም ጋራ አገናዝበው እንዲማሩ በማድረግ ለፈጠራ ሥራ ትኩረት የሰጠ መሆኑን ተረድተዋል። የመጽሐፍቶቹ አዘጋጆችም ተማሪዎች የተማሩትን የንድፈ ሃሳብ ትምህርት ወደ ተግባር እንዲቀይሩ የሚጋብዙ ሆነው አግኝተዋቸዋል። እንደማሳያ የሚያቀርቡትም የቴክኒክና ሙያ ትምህርት በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ መካተቱ እና የአይ ሲ ቲ ትምህርት በመካከለኛ የትምህርት ደረጃ እንዲሰጥ መደረጉን ነው።

አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት በዕቅድ ደረጃ ሲታይ ጥሩ መሆኑን የሚገልጹት ደግሞ ዶ/ር በቀለ ናቸው። እንደ ዶ/ር በቀለ ሃሳብ፣ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት በዋናነት ለመዋዕለ ሕጻናት ትምህርት ትኩረት ሰጥቷል። ይህ የትምህርት ደረጃ ደግሞ የልጆች የመማር ፍላጎት የሚቀሰቀስበት፣እንዲማሩ የሚዘጋጁበት እና አካባቢያቸውን እንዲያውቁ የሚታገዙበት ስለሆነ በጣም ወሳኝ ነገር ነው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርትም መዋዕለ ሕጻናት 2 ዓመት ከተማሩ እና በአግባቡ ከተዘጋጁ በኋላ ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል እንዲማሩ ተደርጓል። ይህ ደግሞ ትምህርት ለሁሉም የሚለውን ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን አድርጎታል። 10ኛ ክፍል ላይ ይሰጥ የነበረው የሁለተኛ ደረጃ ትምርት ማጠናቀቂያ 12ኛ ክፍል መሰጠቱ ተማሪዎችን ሁለት ዓመት በአካልና በአዕምሮ እንዲጎለብቱ ስለሚያደርጋቸው በትምህርት ውጤታቸው ላይ ለውጥ ያመጣሉ። በአጠቃላይም አዲሱ የትምህርት መዋቅር ከ70 በመቶ በላይ ከሚሆኑ አገሮች የትምህርት መዋቅር ጋር ስለሚመሳሰል እንደባለሙያ ሳየው የሚደገፍ ነው ይላሉ።

ከይዘት አኳያም ሥርዓተ ትምህርቱን ዶ/ር በቀለ ሲዳስሱት፣የሥነ ምግባር ትምህርት ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል መሰጠቱ ውጤቱን ዘላቂ የማድረግ ዕድሉ ሰፊ ነው ይላሉ። የቴክኒክና የሙያ ትምህርትን 7ኛ እና 8ኛ ክፍል ላይ እንዲሰጥ መደረጉም ተማሪዎች 8ኛ ክፍል ላይ ባይሳካላቸው በአገኙት የቴክኒክ ዕውቀት በመታገዝ የሆነ ዳቦ፣የሆነ እንጀራ መቁረስ እንዲችሉ ያደርጋቸዋል። በአጠቃላይ የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ጠንካራ ጎኖች የሚመነጩት ከቆየው ሥርዓተ ትምህርት ችግሮች በመሆኑ ጠንካራ ጎኖቹን ያጎላቸዋል በማለት ያብራሩታል።

የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ቅድመ ዝግጅትና አተገባበርን በተመለከተ ምክትል ርዕሰ መምህር አቶ አገኘሁ ሲያብራሩ፣ በ2014 በጀት ዓመት የሙከራ ጊዜ ስለነበረ በመማር ማስተማሩ ሂደት የተወሰነ ልምድ እና ተሞክሮ አግኝተዋል። በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ምንነትና አተገባበር ዙሪያም ለትምህርት



ርዕሰ መምህር አቶ አሰየ የኋላሸት

**አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት በዋናነት ለመዋዕለ ሕጻናት ትምህርት ትኩረት ሰጥቷል።**

አመራሩ ስልጠና ተሰጥቶ ውይይት ተካሂዷል። ለተማሪዎችም በተመሳሳይ መልኩ የትውውቅ ፕሮግራም ተዘጋጅቶላቸዋል። መምህራን ደግሞ በሁለት ዙር ስልጠና ወስደዋል። በአፋን ኦሮሞ እና በአማርኛ በሁለቱም ቋንቋዎች መጽሐፍቶች ተዘጋጅተው በሶፍት ኮፒ በየትምህርት ቤቶች ተደራሽ ሆነዋል።

ርዕሰ መምህር አቶ አሳየም የምክትል ርዕሰ መምህር አቶ አገኘሁን አስተያየት በመደገፍ፣ ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ መስጫ ስልጠናዎች መስጠታቸውን ይናገራሉ። በተካሄዱ የግንዛቤ ፈጠራ መድረኮችም አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ከቅርጽም ሆነ ከይዘት አኳያ ምን እንዳካተተ፣ የማስተማሪያ መጽሐፍት ምን እንደሚመስሉ፣ መምህራን ለሰን ፕላን እንዴት ማዘጋጀት እንደሚኖርባቸውና ማስተማር እንዳለባቸው፣ ተማሪዎችን እንዴት በደረጃቸው ከፍለው ማስተማርና መደገፍ እንደሚገባቸው በመድረኮቹ መነሳታቸውን ያስረዳሉ።

ለተማሪዎችም ምን ዓይነት ትምህርት፣ በምን ዓይነት የትምህርት ፕሮግራም እንደሚማሩ የማሳወቅ ተግባር መከናወኑን ርዕሰ መምህር አቶ አሳየ ይገልጻሉ። በት/ቤት ደረጃም አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት አስመልክቶ ከመምህራን ጋር ውይይት ተደርጓል። በተካሄደው ውይይትም ማን ምን ቢያስተምር የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት አተገባበር ውጤታማ ሊሆን ይችላል የሚለው ጉዳይ ዋና የመወያያ ርዕስ እንደነበር ይናገራሉ። በተለይም በሙያው የተመረቁ መምህራን የሌሉባቸው የትምህርት ዓይነቶችን ማን የትኛውን ቢይዝ ውጤታማ መሆን ይቻላል በሚለው ጉዳይ ላይ



ም/ርዕሰ መምህር አቶ አገኘሁ መሰሰ

# እንደ ቴክኒክና ሙያ፣ የዕይታ መስክና ክንውን ጥበብ የመሳሰሉ የትምህርት ዓይነቶቹ በሙያው የሰለጠኑ መምህራን ያለመኖር የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ትግበራ ሂደት ችግሮቹ ናቸው

በመወያየት በፍላጎት ላይ የተመሠረተ የመምህራን ምደባ ማድረግ ተችሏል።

በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት አተገባበር ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግን በተመለከተ ርዕሰ መምህር አቶ አሳየም፣ የየትምህርት ዓይነቱ ኃላፊዎች በየሳምንቱ በትግበራው ወቅት ሲያስተምሩ ያጋጠማቸውን ችግር ለመለየት በቃለ ጉባኤ የተደገፈ ውይይት እንደሚያካሂዱ ይናገራሉ። እንደ አስተዳደር ደግሞ በየ15ቀኑ የዲፓርትመንት ኃላፊዎችን በመያዝ በሚካሄድ የውይይት መድረክ ያጋጠሙ ችግሮችንና የተፈቱበትን መንገድ፣ የተገኙ ስህተቶች ካሉም በምን መልኩ መስተካከል እንደሚኖርባቸው የሚያመላክቱ ሃሳቦችን በቃለ ጉባኤ እንደሚወያዩ ይገልጻሉ። አሁን ላይ ወደ ትግበራ ሲገቡ፣ በተለይም ከሥርዓተ ትምህርቱ ቅበላና ቅድመ ዝግጅት ጋር በተያያዘ በከተማ አስተዳደር፣በክ/ከተማና በወረዳ ደረጃ ድጋፍና ክትትል ተደርጎላቸዋል፤ ግብረ መልስም ተሰጥቷቸዋል። በተሰጠው ግብረ መልስ ግን በኋላ መልኩ የታየ ክፍተት ባለመኖሩ የትግበራ ሂደታቸው ደህና መሆኑን ተገንዝበዋል።

እንደ አራዳ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የሙከራ ትግበራ ውስጥ ሲገባ ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ይሆናል የሚል እምነት እንደሌለው አቶ ወንድሙ ያብራራሉ። ስለሆነም የሥርዓተ ትምህርት ትግበራውን በሁሉም የመንግሥትም ሆነ የግል ትምህርት ቤቶች በተጠናከረ ድጋፍና ክትትል መመራት እንዳለበት በዕቅዳቸው ላይ በግልጽ ማስቀመጣቸውን ያስረዳሉ። በክፍለ ከተማ ደረጃ የሱፐር ቪዥን ቡድኖች ስላሉ በእነሱ አማካይነት አተገባበሩ እየተፈተሸ ክትትልና ድጋፍ እንደሚደረግ አሠራር ተቀምጧል።

እንደ አቶ ወንድሙ ማብራሪያ፣ በክትትልና ድጋፍ ተግባር መምህራን የሚያስተምሩትን መጽሐፍ ከይዘት እና ከሌሎች ጉዳዮች አንጻር የሚገመግሙበት መስፈርት ተዘጋጅቶ እንዲወርድላቸው ተደርጎ ግምገማ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ከሰዓት፣ ከይዘት፣ከያዘው ጭብጥ አንጻር ማነቆ የሚሆኑ ነገሮች ካጋጠሙ እየተከታተሉ ለማስተካከል እንዲቻል የመጽሐፍ ግምገማ ተግባርን እንዱ የትኩረታቸው አካል አድርገውታል። በየዕለቱና በየሳምንቱ ታቅደው ለሚከናወኑ ተግባራትም በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ እየተከናወኑ ስለመሆኑ ቅጽ አዘጋጅተው በማውረድ የሚከታተሉበት እና ክፍተቶች የሚስተካከሉበት አሠራርም ተፈጥሯል።

የመማሪያ መጽሐፍት ሙሉ በሙሉ ቀደም ብለው ባለመድረሳቸው ምክንያት ዓመታዊ ዕቅዳቸውን አቅደው ወደ ሥራ ለመግባት መቸገራቸውን ምክትል ርዕሰ መምህር አቶ አገኘሁ ይናገራሉ። ወደየትምህርት ቤቶች የደረሱት የእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ሁለትና ሦስት ቻፕተሮች ብቻ ለዚያውም በሶፍት ኮፒ ነው። በእርግጥ አሁን ላይ ስርጭት በመጀመር ላይ እንደሚገኝ የሚገልጹት አቶ አገኘሁ፣ ስርጭቱም ቢሆን በግዴለሽነትና በተለያዩ ምክንያቶች የመዘግየትና ያለመድረስ ሁኔታ ስለሚኖር በሥርዓተ ትምህርቱ አተገባበር ላይ እንደ ስጋት ያነሱታል። የተማሪዎች ቴክስትም በእጃቸው አለመድረሱ አሁንም በችግርነት የሚያዩት ጉዳይ ነው። በመሆኑም የመጽሐፍት ዝግጅትም ሆነ ስርጭት ቶሎ አለመከናወኑ በትምህርት አሰጣጡ ላይ ራሱን የቻለ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚኖረው በየደረጃው የሚገኙ አካላት ሊያስቡበት እንደሚገባ ያሳስባሉ።

በተመሳሳይ መንገድ ርዕሰ መምህር አቶ አሳየም፣ በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት አተገባበር ዙሪያ ከመጽሐፍት ህትመትና ስርጭት ጋር የተያያዘውን ጉዳይ በችግርነት ያነሱታል። ሌላው እንደ ቴክኒክና ሙያ፣ የዕይታ መስክና ክንውን ጥበብ የመሳሰሉ የትምህርት ዓይነቶች በሙያው የሰለጠኑ መምህራን ያለመኖር የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ትግበራ ሂደት ችግሮች ናቸው ብለው ያቀርቧቸዋል።

በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ከታዩ ክፍተቶች መካከል አንዱ በአሁኑ ወቅት በዓለም ደረጃ ትልቁና አንገብጋቢ ጉዳይ የሆነውን የአካባቢ ጥበቃ ተግባር፣ተማሪዎች ከታችኛው ክፍል ጀምረው ዕውቀት ይዘው ማደግ እንዲችሉ በሥርዓተ ትምህርቱ አለመካተቱ ነው። የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ግፊት ደግሞ በሥርዓተ ትምህርቱ አካቱ የሚል እና የወደፊቱም የሰው ልጅ ትልቁ ፈተና በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባ የሚሉት ዶ/ር በቀለ ናቸው። ከሥርዓተ ትምህርቱ አተገባበር ስጋቶች መካከል ደግሞ የመምህራን ፍልሰት መሆኑን ያነሳሉ። በመጀመሪያ ደረጃ መምህራን ሙያውን መርጠውት ሳይሆን ምርጫ ሲያጡ የሚማሩትና በሙያው ላይ የሚቆዩትም ወደ ሌላ ሙያ እስኪሄዱ ድረስ ለመሸጋገሪያነት ነው ይላሉ።



ወ/ሮ ዛፉ አብርሃ

ስለዚህ የመምህራን ችግር፣ በተለይም በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ለተካተቱ አዳዲስ የሙያ ትምህርቶች የሰለጠነ የሰው ኃይል ካለመኖሩ ጋር ተያይዞ ሲታይ ችግሩን የከፋ እንደሚያደርገው ይናገራሉ።

እንደ ዶ/ሩ ገለጻ፣የሰው ሀብት ልማት ለሀገር ዕድገት ቁልፍ ነገር ነው ካልን እና ውጤታማ ለውጥ ማምጣት ከተፈለገ ለትምህርት ዘርፉ ትኩረት በመስጠት የበጀት ጉዳይን መጨመር ያስፈልጋል። በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ዙሪያም ማኅበረሰቡ በቂ ግንዛቤ መያዝ ይኖርበታል። መምህራን ራሳቸው በአግባቡ መገንዘባቸውን ማረጋገጥ ይገባል። የትግበራው አካል የሆኑ ባለድርሻ አካላትም ሥርዓተ ትምህርት ምንድነው፣በሀገር ደረጃ ምን ታስቧል፣ምን ዓላማ አለው፣ልጆች ምን ይማራሉ፣መቼ ይማራሉ፣መቼ ምን ይደረጋል የሚለውን ግንዛቤ ለማስጨበጥ በስፋት መሥራት ይኖርበታል። የግል ትምህርት ቤቶችም የራሳቸው ሥርዓተ ትምህርት ያላቸው በመሆኑ የመንግሥትን ሥርዓተ ትምህርት ለመተግበር ፍላጎት ማጣት ይታይባቸዋል። ስለሆነም በሀገሪቱ ሥርዓተ ትምህርት ለማስተማር ተስማምተው ት/ቤት እስከከፈቱ እና ፈቃድ እስከወሰዱ ድረስ የተዘጋጀውን ሥርዓተ ትምህርት ላለመቀበል ጥረት ማድረጋቸው የሕግ ጥሰት እና ወንጀልም ጭምር በመሆኑ ከአሁኑ መስተካከል አለበት፡

እንደ አራዳ ክፍለ ከተማ ጽ/ቤት በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት የ2014 ዓ.ም የሙከራ ትግበራ ሁለት በአማርኛና ሁለት በአፋን ኦሮሞ ሥርዓተ ትምህርት የሚሰጥባቸው አራት ት/ቤቶች እንደነበሩ አቶ ወንድሙ ገልጸዋል። በእነዚህ አራት ት/ቤቶች ከሚገኙ መምህራንንና የትምህርት አመራሩ ጋር በለውጡ ላይ እና የሥርዓተ ትምህርቱን የመጽሐፍት ትውውቅ መደረጉን በጥንካሬ ያነሱታል። በሂደቱም መጽሐፉን ከሽፋን ጀምሮ እስከ ውስጠኛው ይዘት ድረስ ያሉ ችግሮችን አሳይቷቸዋል። ይህም ወደ ዋናው የመጽሐፍ ሕትመት ከመገባቱ በፊት የታዩ ክፍተቶችን ለማወቅ፣ግብረ መልስ ለመስጠትና ለማስተካከል በማገዝ ጥሩ ልምድ ተወስዶበታል ይላሉ።

ይሁን እንጂ በሥርዓተ ትምህርቱ አተገባበር ሂደት ሁለት መሠረታዊ ክፍተቶች መገኘታቸውን አቶ ወንድሙ ይናገራሉ። የመጀመሪያው ለአዳዲስ የትምህርት ዓይነቶች በሙያው የሰለጠኑ የመምህራን እጥረት ማጋጠሙ ነው። ሁለተኛው ችግር ደግሞ መጽሐፍ በበቂ ሁኔታ ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች በበቂ ሁኔታ ማድረስ አለመቻሉ ነበር። በትግበራ ሂደቱ ያጋጠሙትን ችግሮችን ለማቃለል የተወሰዱ መፍትሔዎችን በተመለከተም አቶ ወንድሙ ሲያብራሩ፣ በመጀመሪያ ደረጃ በእጃችን ላይ ምን አለን የሚለውን በማየት የመጽሐፍት እጥረትን ለማሟላት እየሠሩ ይገኛሉ። በሙያው የሰለጠነ የባለሙያ እጥረትን ለማቃለልም ከመምህራን መካከል በተጓዳኝ በሙያው የሰለጠኑትን በመለየት በምርጫቸው እንዲያስተምሩ የማድረግ ሥራ ሠርተዋል። በተለይም ከአይ ሲ ቲ ሙያ ጋር የተያያዙትን ለመመለስ ጥረት ተደርጓል። የባለሙያ እጥረት ያሉባቸውን የትምህርት ዓይነቶችም በቅጥር ለማሟላት ከተማ አስተዳደሩ ጥረት እያደረገ ይገኛል። ሌላው አማራጭ መፍትሔ ተደርጎ የተወሰደው ደግሞ መምህራንን በአጫጭር ስልጠናዎች በሙያው ብቁ ማድረግን ነው።


ትምህርት ለአንዲት ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት ወሳኝ ሚና ያለው ጉዳይ መሆኑ አያጠያይቅም። የሀገር ዕድገትም ሆነ ስልጣኔ ያለ ትምህርት አይታሰብም። የታሰበውን ዜጋ ለመፍጠር ደግሞ በአግባቡ የተዘጋጀና ወቅታዊ ሀገራዊ ሁኔታውን ከግምት ያስገባ ሥርዓተ ትምህርት ሊኖር የግድ ነው። በዚህ ረገድ ትምህርት ሚኒስቴር በጥናት የተደገፈ የሥርዓተ ትምህርት ክለሳ አድርጓል። ከዚያም አልፎ ወደ ሙሉ ትግበራ መግባቱም የማያበረታታ ነው። ይሁን እንጂ በትግበራ ሂደቱ የታዩ ጠንካራ ጎኖች እንደተስተዋሉ ሁሉ ችግሮችም አልታጡበትም። በተለይም ከመጽሐፍ ዝግጅትንና ስርጭት፣ እንዲሁም ከመምህራን ጋር የተያያዙ ችግሮች ጊዜ ሊሰጣቸው የሚገባ አይደለም። ስለሆነም በየደረጃው የሚገኘው ጉዳዩ የሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ሁሉ፣ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት በአግባቡ እንዲተገበር እና የሚጠበቀውን ውጤት ማምጣት ይቻል ዘንድ፣ የሚነሱ ችግሮችን ትኩረት ሰጥቶ መመለስና ክትትልና ድጋፉን ማጠናከር አለበት እንላለን።

**የግል ትምህርት ቤቶችም የራሳቸው ሥርዓተ ትምህርት ያላቸው በመሆኑ የመንግሥትን ሥርዓተ ትምህርት ለመተግበር ፍላጎት ማጣት ይታይባቸዋል**



ሽብሩ ተድላ
(ፕሮፌሰር ኤሚሪተስ)

# የዳሉል ስምጥ ሸለቆ ሳይንሳዊ ይዘት፣ አስደናቂ ውበት እና እምቅ የተፈጥሮ ሃብት



ገዛኸኝ ደርጉ
(ፕሮፌሰር)

## መግቢያ

የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ ሳይንስን ማኸዘብ (የሳይንስን ዘዴ እና ዕውቀት ለሕዝብ እንዲዳረስ ማድረግ) ሲሆን፣ የተዘጋጀው በዳሎል ስምጥ ሸለቆ ሳይንሳዊ ይዘት፣ አስደናቂ ውበት እና እምቅ የተፈጥሮ ሃብት እንዲሁም ትዝታ ላይ ተመሥርቶ ነው፡፡ስለ ዳሎል በረሃ ዝርዝር ሁኔታ ከማቅረባችን በፊት፣ ትንሽ ደረቅ ያለ ሳይንስን ማውሳቱ አይቀሬ እና አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።ጽሑፉ የአካባቢውን ሥነ ምድራዊ (ጂኦሎጃዊ) አመሠራረት፣ አካባቢው በከርሱ ያመቀውን እምቅ ሃብት፣ እንዲሁም ከላይ የሚታየውን ልዩ ውበት ይዳስሳል።

ዳሎልን አንዳችን (ሽብሩ ተድላ) የጎበኘው በአካባቢ ጥናት መንስዔ ሲሆን፣ ሌላችን (ገዛኸኝ ይርጉ) በተደጋጋሚ በሳይንሳዊ ምርምር መንስዔ አካባቢውን ጎብኝቷል፣ እየጎበኘም ነው።እዚህ ላይ በብዛት የሚወሳው በአካባቢ ጥናት ጉብኝቱ ተመሥርቶ የተገኘ ግንዛቤ እና እይታ ነው፡፡



የጨው መጅ በግመል ትራንስፖርት

## የዳሎል ስምጥ ሸለቆ (Dalol Depression) ሳይንሳዊ ሁኔታ

የአፋር ስምጥ ሸለቆ ቅርፅ እንደ “ትራያንግል” (triangle) መሰል ሲሆን፣ የሸለቆው አጠቃላይ ስፋቱ 50 ሺ ኪሎ ሜትር ካሬ ገደማ ነው።የስምጥ ሸለቆው አመሠራረት የጀመረው ከ25 ሚሊዮን ዓመት ገደማ በፊት እንደነበረ ይገመታል።የምድር ጠንካራውና ውጫዊው ክበብ (lithosphere) አካል የሆኑ ሁለት “ስፍሃን “ (Plates)፣ ማለት ግዙፉ የአፍሪካ “ስፍሃን “ እና መጠነ ውስኑ (አንፃራዊ) የዓረቢያ “ስፍሃን” የሚገናኙበት አካባቢ ሆኖ፣ በሁለቱ “ስፍሃን “ ዝግመታዊ የመራራቅ እንቅስቃሴ መንስዔ የተከሰተ ሸለቆ ነው።ይህም የቀይ ባህር ስምጥ ሸለቆ፣ የኤደን ባህረ ሰላጤ ስምጥ ሸለቆ እና የምሥራቅ አፍሪቃ ስምጥ ሸለቆ (East African Rift Valley) መገናኛ አካባቢ መሆኑ ነው።

የአፋር ስምጥ ሸለቆ የአፍሪካ ክፍለ ዓለም (ስፍሃን) ለሁለት የሚከፈልበት የመጀመሪያው ምዕራፍ የመጀመሪያው ጫፍ ሲሆን፣ ከሚሊዮኖች ዓመታት በኋላ ምሥራቅ አፍሪካን ለሁለት የሚከፍለው (የሚሰነጥቀው) እና የሚለያየው ግዙፍ እንቅስቃሴ እውን የሆነበት አካባቢ ነው።የመሬት አካል መሰነጣጠቅ የዚህ ስምጥ ሸለቆ አንዱ ባህርይ ነው።የዚህ መሬት መሰንጠቅ



ስመገበያያነት ያገለግል የነበረ አሞሌ ጨው

ክፍተት በየዓመቱ ከሰባት ( 7mm) እስከ ሃያ ሚሊሜትር (20mm) ገደማ እየጨመረ ነው፡፡

የሰሜን አፋር (ደንከል) ስምጥ ሸለቆ፣ በሰሜን የዳሎል ረባዳ የጨው ሜዳ አካባቢ ሲሆን፣ በደቡብ ኤርታ አሌ (Ert’ale) እሳተገሞራዎች ሰንሰለት ይገኛሉ።የዳሎል የጨው ሜዳ አራት ሺ ኪሎ ሜትር ካሬ ይሸፍናል።በዚህ አካባቢ በሰሜን አቅጣጫ ከዘይላ ወደብ በስተደቡብ ዝቅ ብለው የተዳፈኑ እሳተገሞራ ኮረብታዎች ይታያሉ።ከነሱም ውስጥ የጃልዋ (Jalua) እና የአሊድ (Alid) እሳተገሞራ ኮረብታዎች፣ አካባቢው በቀይ ባሕር ውሃ እንዳይጥለቀለቅ ይገታሉ፡፡

## እሳተገሞራ

በመሠረቱ ምድር አሎሎ መሳይ ቅርፅ ይዛ፣ ከላይ በስሱ እንደ ቅርፊት ከሚሸፍናት አካል በቀር፣ ውስጧ እሳት (እጅግ የጋለና አልፎ አልፎም የቀለጠ ድንጋይ እና የብዙ ንጥረ ነገሮች ቅልቅል) ነው።ሽፋኑ (ጠጣር አካሉ) በጣም ውስን ሲሆን፣ ከአጠቃላይ ይዘቱ አንድ ከመቶ (1%) በታች ነው፣ ሳይንሳዊ ስያሜውም “ሊቶስፌር” (lithosphere) ይባላል፡፡

ይህ ስስ የምድር ሽፋን፣ በአማካኝ ከ100 ኪሜ ጥልቀት ሲኖረው፣ ደረቁ የላይኛው ቅርፊት (crust) ከ35 እስከ 50 ኪሜ ይዘልቃል፣ በጣም ከፍተኛ ቦታዎች የሚገኙባቸው አካባቢዎች ከላይ ያለው ደረቅ ቅርፊት ከዚህ ወፈር ይላል።ከምድር ገፅ ወደ ከርሰ ምድር በተዘለቀ መጠን፣ ሙቀቱ አብሮ ይጨምራል፣ በእያንዳንዱ ኪሎሜትር የጥልቀት ጭማሪ፣ ሙቀቱ በሰላሳ ዲግሪ ሴልሲየስ

(30°C) ይጨምራል።በዚህም ምክንያት ወደ ውስጥ በተዘለቀ መጠን ውስጣዊው የምድር ክፍል ጠጣርነቱ እየላላ እየላላ ሄዶ፣ ምድር አስኳል (outer core) ሲደርስ ሙሉ በሙሉ የቀለጠ ድንጋይ/ ብረታ ብረት ፈሳሽ ይሆናል፡፡


አንዱ የእሳተ ገሞራ መንስዔ የምድር “ስፍሃኖች” (Plates) ሲፋተጉ/ሲጋጩ በሚፈጠረው ከፍተኛ ሙቀት አለት ሲቀልጥ ነው።ሌላውና ዋናው መንስዔ ግን ከስፍሃን በታች ያለው እጅግ የጋለውና የላላው አካል ወደ ላይ ሲነሳና: ቀድሞ የተጫነው ከፍተኛ ግፊት በፍጥነት ሲቀንስ (decompression) ያለምንም ተጨማሪ ሙቀት ጠጣርነቱ ተቀይሮ ፈሳሽ ይሆናል (ይቀልጣል)፣ የቀለጠው አለት በስንጥቅ ውስጥ ፍጭጭ ብሎ ወደላይ ሰረጎ መሬት ገፅ ላይ በፍንዳታ መልክ ይፈሳል፣ ይህ ነው እሳተገሞራ የሚባለው፡፡

በዓለማችን ሰባት ግዙፍ “ስፍሃን “ አሉ፣ አንዳንድ ተመራማሪዎች እነዚህን በሰባት ፋንታ ስምንት ናቸው ይላሉ።ሰባቱ “ስፍሃን” የአፍሪካ፣ የአንታርክቲካ፣ የዩሮእስያ፣ የሰሜን አሜሪካ፣ የደቡብ አሜሪካ፣ የሰላማዊ ውቅያኖስ እና የኢንዶአውስትራሊያ ናቸው።ስምንት ናቸው የሚሉት ደግሞ የመጨረሻውን፣ ኢንዶአውስትራሊያዊውን ለሁለት በመክፈል እና ኢንዶያዊ እና አውስትራሊያ ብለው በመሰየም ነው።ከነዚህ ከግዙፍ “ስፍሃን” በተጨማሪ ትናንሽ (አንፃራዊ)”ስፍሃን” አሉ፣ ለምሳሌ የዓረቢያ፣ የካሬቢያን፣ የፊሊፒንስ፡፡

እነኝህ “ስፍሃን” ብለን የሰየምናቸው ግዙፍና ጠጣር የድንጋይ ሰፌድ/ምጣድ መሰል አካላት፣ ሽፋኖች፣ ከበታቻቸው ከሚገኘው ከጋለውና ከላላው የምድር ከርስ ላይ ተንሳፈው፣ ተጠጋግተው ነው የሚገኙት።እነሱም በዓመት እስከ አሥር ሴንቲ ሜትር (10 cm) ገደማ ይንቀሳቀሳሉ (ነባር ቦታቸውን ይለቃሉ)።ጎን ለጎን ያሉ “ስፍሃን” በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ከሚገናኙበት ወሰን እየተራራቁ ሊሄዱ ወይም ሊቀራረቡ ብሎም ሊጋጩ ይችላሉ።በሚጋጩበት ጊዜ አንዱ ግዙፍ ሰፌድ/ምጣድ ጠርዝ ሌላኛው ላይ ሊያርፍና ሊደረብ ይችላል።አንዱ ወፍራምና ቀላል፣ ሌላኛው ስስና ከባድ (አንፃራዊ) የሆኑ ሲገናኙ፣ ወፍራሙና ቀላሉ ከላይ ሲሆን፣ ስሱ ደግሞ በክብደቱ ወደ ታች ይጠልቃል።ይህ ሲከሰት በታች የሚገኘው ስፍሃን ቀስ በቀስ እየተንሸራተተ ዝቅ ይላል (ወደ ውስጥ ይሰምጣል)፣ በተቃራኒው ላይኛው ደግሞ ከነበረበት ከፍ ይላል።

አብዛኛው እሳተ ገሞራ የሚፈነዳው (60% ገደማ) እነኚህ ግዙፍ ምጣዶች ከሚገናኙባቸው (ወሰኖች) አካባቢዎች ነው።በተቃራኒው ላይኛው ክብደተ-ቀላሉ ስፍሃን ደግሞ፣ በመደራረብና በመተጣጠፍ ከነበረበት በጣም ከፍ ይላል፣ይህም ለተራራ ሰንሰለት መከሰት መንስዔ ይሆናል።ለምሳሌ በእስያ አህጉር የሚገኘው “የሂማላያ ተራራ ሰንሰለት” (Himalaya) በዚህ


የተመሰቃቀለ የመሬት ገፅታ


ሆድ እቃው የተቦረቦረ የመሬት አካል


በጨው አለት ላይ መኪና መንዳት ይቻላል


የሃማዴላ የቱሪስት
ሆቴል መሰናዶ



የግመል ሰልፈኛ ከመሪው ጋር



የጨው መጅ በመጥረቢያ
እየተከረከመ ሲዘጋጅ

ዓይነት “ስፍሃ” ግጭት መንስዔ የተገኘ የተራራ ሰንሰለት ነው፡፡

እሳተገሞራ ከምድር ውስጥ ፈንድቶ የሚወጣ የድንጋይ (በብናኝ ቅላጭ ወይም በአለት መልክ) ቃጠሎ ነው።ምድር ውስጥ እያለ በወፍራም ሊጥ መልክ የሚገኝ “ቅላጭ ድንጋይ” (“ማግማ” / magma) ነው።ከ”ቅላጭ ድንጋይ” (“ማግማ”) በተጨማሪ እሳተ ገሞራ ጋዝ ብናኝ ቅላጭ እና ጠጣር አለትም ያስወጣል።እሳተ ገሞራ የሚተፋው “ገሞራ ትፍ” (lava) ሙቀቱ በአማካኝ ከሰባት መቶ እስከ ሺ ሁለት መቶ ዲግሪ ሴልሲየስ (ከ700 እስከ 1,200 °C ) ይሆናል።ዝልግልግነቱም በውሕዱ ዓይነት ይወሰናል (ቀጭን ከሆነ እንደ ቀለጠ ማር፣ በብዛት “ሲሊካ” (Silica) ካለበት እንደ ዳቦ ሊጥ በጣም ወፍራም ሆኖ፣ ዝግ ብሎ፣ የሚፈስ ይሆናል)።

የመሬት መንቀጥቀጥ መንስዔም የ”ስፍሃን” መሰንጠቅና መለያየት እንዲሁም ግጭት ነው፡፡ አንድ ስፍሃን ሲወጠርና፣ ውጥረቱ ስብራት ፈጥሮ ሲለቅ ወይም ሁለት “ስፍሃን “ ሲፋተጉ፣ ከፍተኛ ኃይል ስለሚገኝ፣ ይህ ኃይል ነው ለመሬት መራድ/ መንቀጥቀጥ (earthquake) መንስዔ የሚሆነው፡፡

## ጨዋማ አካባቢዎቹ

ጨው የሁለት ንጥረ-ነገሮች፣ “ሶዲየም” [Sodium (Na)] እና “ክሎሪን” [Chlorine (Cl)] ኬሚካዊ ውሁድ ሲሆን፣ ሳይንሳዊ ስያሜውም ጨው [“ሶዲየም ክሎራይድ”/ Sodium Chloride (NaCl)] ነው።“ሶዲየም” የሚባለው ንጥረ-ነገር በሰውነታችን ውስጥ ያለውን የፈሳሽ ይዘት መጠን ይቆጣጠራል፣ ሚዛኑን ጠብቆ በሥራ አካላታችን በጠቅላላ እንዲሰራጭ ያደርጋል። ይህም በአካል ውስጥ የሚገኙ ፍሳሾች ይዘት ሚዛኑን/መጠኑን እንዲጠብቅ ያደርጋል፣ ተግባሩ እና ሂደቱ እንደ ንዑስ የሕዋስ ፖመፕ ይመሰላል፡፡

የዳሎል በረሃ ረባዳ መሬት የጨው ሜዳ፣ በጨዋማ የባሕር ውሃ ትነት የተገኘ ሲሆን፣ የትነቱ ቅሪት ከጨው በተጨማሪ ሌሎች ኬሚካላዊ ውሑዶች ይገኙበታል፣ ለምሳሌ “ፖታሽ”፣ የድኝ ውሑዶች ወዘተ።በዳሎል ረባዳ ሜዳ ይህ በትነት የተገኘ የጨው አለት ጥልቀቱ እስከ 970 ሜትር እንደሆነ ይገመታል።ይህን የጨው አለት በአካባቢው ለመከማቸት ከአንድ መቶ ሺ ዓመት በላይ እንደፈጀ ይገመታል።በዚሁ አካባቢ ወደ ደቡብ አቅጣጫ “የአሳሌ” ጨዋማ ሐይቅ ይገኛል፡፡

የጨው ባሕር ውሃ ከቀይ ባሕር ወደ ዳሎል ረባዳ መሬት ሰርጎ የገባ ሁለት መቶ ሰላሳ ሺ ዓመት ጀምሮ እስከ ሃያ አራት ሺ ዓመት በፊት ገደማ፣ ማለት 206 ሺ ዓመት ገደማ የፈጀ ፍሰት ነው።አካባቢው በተደጋጋሚ በባሕር ጨዋማ ውሃ ተጥለቅልቆ እንደነበረ ሳይንሳዊ መረጃ አለ።ቅሪት ጨውማ ውሃ ከቀይ ባሕር ሰርጎ ዛሬም “አሳሌ” የጨው ሐይቅ ይገኛል ።



"ጎራይቶ" ሳይንሳዊ ስያሜ (Hyphaene thebaica)



በ"ጎራይቶ" ዳውጃ የተሠራ የዳሉል በረሃ ጎጆ

አንዳንዴ ከደጋው አካባቢ ከርሰ ምድር የሚመጣ ውሃ፣ ከአካባቢው በከርሰ ምድር የሚገኝ ከፍተኛ ሙቀት ካለው አለት ጋር እየተገናኘ፣ በፍልውሃ (የፈላ ውሃ) መልክ ወደ ላይ ይዘልቃል።በዚህ መንገድ የሚፈላው ውሃ ሙቀት ከርሰ ምድር ውስጥ እንዳለ እስከ 280-370 0C ድረስ ይዘልቃል፣ ሆኖም መሬት ላይ ሲደርስ የውሃው ሙቀት አንድ መቶ ሴልሲየስ (100 0C) አካባቢ ነው።ፍልውሃው ሙሉ በሙሉ የአሲድ ባህርይ አለው (አሲዳማ ነው)።ዳሎል በብዙ አካባቢዎች የተንጠባጠቡ ጨዋማ ኩሬዎች/ ሐይቆች የሚገኙበት ቦታ ነው፡፡



ከአፍዴራ ሐይቅ የተመረተ የጨው ክምር

የአፍዴራ ጨዋማ ሐይቅ የሚገኘው ከባሕር ወለል በታች 112 ሜትር ገደማ ላይ ሲሆን፣ በአማካኝ ጥልቀቱ 20.9 ሜትር ገደማ ነው፣ ስለሆነም አጠቃላይ የጨዋማው ውሃ መጠን 2.4 ኩብ ኪሎ ሜትር፣ ወይም 2.4,000,000,000 ሜትር ኩብ ነው (አንድ ሜትር ኩብ አንድ ሺ ሊትር ነው)።ሐይቁ ከሁለት መቶ ሺ ዓመት በፊት አሁን ከሚገኝበት ከፍታ በ50 ሜትር ገደማ ከፍ ብሎ ነበር (ማለት ከባሕር ጠለል በታች ያለው ጥልቀቱ ቀንሶ)።ሆኖም በሳይንስ ጥናት እንደተደረሰበት፣ ሐይቁ ላለፉት አሥር ሺ ዓመታት ገደማ ይህ ነው የሚባል ለውጥ አላሳየም።ላለፉት አምሳ ዓመታት ገደማ የሐይቁ ከፍታ እንዳልተለወጠ ይታወቃል።

ጨው ለብዙ ኬሚካላዊ ውሑዶች ለመፈብረክ ለኢንዱስትሪ ግብዓት በመሆን በምግብ ማጣፈጫነት፣ ብዙ የምግብ ዓይነቶች እንዳይበላሹ (መበስበስ፣ ወዘተ) አነባሪ (Preservative) ሆኖ ማገልገል፣ ሳሙና ለመፈብረክ፣ በክረምት በረዶ በሚጥልባቸው አካባቢዎች በመንገዶች ላይ የሚከመረውን በረዶ ለማሟላት ያገለግላል፡፡



የአፍዴራ ተራራ እና የአፍዴራ ሐይቅ


## የጨው ታሪካዊ ይዞት በኢትዮጵያ

ጨው እንደገንዘብ ሆኖ በብዙ የዓለም አካባቢዎች፣ ለምሳሌ በቻይና፣ በሮማን ግዛት፣ በቅርብ ምሥራቅ እንዲሁም በሀገራችን ለዘመናት አገልግሏል።እንዲያውም በላቲን “ሳል” (“sal”) ጨው ማለት ሲሆን ፡ ይህም “ ሳላሪየም” “salarium” ለሚባል ቃል መነሻ ሆኖ፣ ብሎም ደመወዝ /Salary/ ለሚለው ቃል መሠረቱ እንደሆነ ይታወቃል።“አሞሌ ጨው” እስከ ቅርብ ዘመን በኢትዮጵያ መገበያያ ገንዘብ ነበር።ለመንግሥት ከፍተኛ የገቢ ምንጭ በመሆን አገልግሏል፡፡


የአክሱም ዘመነ መንግሥት ከተዳከመ በኋላ፣ ከብር እንዲሁም ከወርቁ የተሠሩ መሐለቅ ሲጠፉ፣ ዓይነት በዓይነት ከመለዋወጥ (barter system/trading) በተጨማሪ፣ ለዘመናት ጨው (አሞሌ ጨው) መገበያያው ሆኖ ነበር።መገበያያነቱም በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ አንሰራርቶ እንደነበረ ታሪክ ያወሳል።ከትግራይ እስከ ባሌ፣ ከወለጋ እስከ አርጎባ፣ ተስፋፍቶ ሳለ፣ የጨው ነጋዴዎች በትናንሽ መንደሮች ሁሉ ይገኙ ነበር።የመንግሥት ግብርም ይከፈል የነበረው በአሞሌ ጨው ነበር፡፡

በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥትም ከጨው ንግድ በቀረጥ መልክ አርባ ሺ ጠገራ ብር ይሰበሰብ እንደነበረ ተመዝግቧል፣ የቀረጥ ግምት ይሰላ የነበረው፣ በአንድ የግመል ጭነት (አምስት መቶ አሞሌ ገደማ የምትሸከም) ወይም በሁለት በቅሎ/አህያ ጭነት (ከ200-250 አሞሌ የምትሸከም) አንድ አሞሌ እንዲከፈል ነበር።በሃያኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አካባቢ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ጠገራ ብር፣ ያም የአገሪቱ በመቶ ሃያ ሰባተኛ (27%) የቀረጥ ገቢ፣ ከጨው ይገኝ ነበር።

ለዘመናት በትግራይ አካባቢ በግመል (500 አሞሌ በጭነት)፣ በበቅሎ (250 አሞሌ በጭነት)፣ በአህያ (200 አሞሌ በጭነት)፣ እንዲሁም በሰው ሸክም (50 አሞሌ በሸክም)፣ ከበረሃው (ዳሎል እና ሌሎች አካባቢዎች) ሰላሳ ሚሊዮን ገደማ አሞሌ ጨው፣ ግምቱም አንድ ተኩል ሚሊዮን ጠገራ ብር የነበረ ይጋዝ እንደነበረ በታሪክ ተመዝግቧል፡፡



በቅርብ በእሳተ ገሞራ ቅሬት
የተሳበሰ አካባቢ



ቀደም ሲል በእሳተ ገሞራ
ቅሬት የተሳበሰ አካባቢ

## የዳሎል ስምጥ ሸለቆ ጉብኚት

በዚህ ጽሑፍ በብዛት የሚወሳው የዳሎል ጉብኝት በአካባቢ ጥናት ላይ የተመሠረተ ነው።ጉዞው የአካባቢ የመስክ ጥናት ሲሆን (Natural and Social Impact Assessment)፣ የጥናት ቡድን የተሠማራ “ቢ ኤች ፒ” (BHP Billiton World Exploration Inc–Ethiopia፡ Danakil Potash Exploration Project) የሚባል ኩባንያ፣ በዳሎል አካባቢ በፖታሽ ማዕድን ሥራ ላይ ሊሠማራ አስቦ፣ የፖታሽ ማዕድን ማምረት በአካባቢ ሊያስከትል የሚችለውን ተፅዕኖ ለማጥናት በዳሎል በረሃ በሥራ፣ ለአሥር ቀናት ያህል አንዳችን (ሽብሩ ተድላ) ተሰማርተን ነበር።የአካባቢ ጥናቱ የተካሄደ በጥቅምት 2003 ዓም ነበር፡፡

የጥናቱ ቡድን “ኸልተ አውላሎ” ከፍተኛ ቦታ (2400 ሜትር ከባህር ጠለል በላይ) ወደ ዳሎል በረሃ (115 ሜትር ከባሕር ጠለል በታች/ በድምሩ 2515 ሜትር) ወርዶ፣ በረሃሌ ለመድረስ ሁለት ቀናት ፈጅቶበታል።ጥልቀቱ እንደወረደ ሲሰላ፣ ከጎሐ ጽዮን እስከ አባይ ድልድይ ድረስ ያለውን ጥልቀት እጥፍ ይሆናል፡፡

## ደቂቀ እስጢፋኖስ (ደቂቀ እስጠፋ)

ከ”ኸልተ አውላሎ” ላይ ሆኖ ወደ በረሃው ሲወረድ፣ ደጋው ላይ በግራ በኩል ከሩቅ የደቂቀ እስጢፋኖስ (ደቂቀ እስጢፋ) ገዳም የነበረ ይታያል።ደቂቀ እስጢፋኖስ በኢትዮጵያ ክርስትና እምነትን የሞገቱ፣ አንዳንድ እምነት ቀመስ ድርጊቶችን የተቃወሙ፣ የቀን ተቀን ድርጊቶችን የማይቀበሉ፣የእምነት ምሰሶ የነቀነቁ፣ ቤተ ክህነት የማትቀበላቸው፣ እንዲያውም በኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማንያን የተወገዙ፣ በአሥራ አምስተኛው ምዕተ ዓመት ያበቡ፣ የተሐድሶ እንቅስቃሴ መሪዎች ነበሩ፡፡

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ እንደዘገበው፣ የወሰዱት አቋም መለያዎች፣ ዋናዎቹ ተሐድሶ መስተጋበር ለአብ፣ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር ለሥዕል፣ ለመስቀል ለንጉሥ አንሰግድም (እራስን በሚያስጎነብስ እጅ አንነሳም)።ደቂቀ እስጢፋ የተነሱት በአፄ ይስሐቅ (1406-1421) ዘመን ሲሆን፣ “ማርቲን ሉተር” ጀርመን ላይ ተመሳሳይ ሐሳብ ይዞ ከመነሳቱ ከሠላሳ ዓመት ገደማ በፊት ነበር።እንዲያውም ከደቂቀ እስጢፋ ከመቶ አምሳ ዓመት በፊትም ተመሳሳይ እምነት የነበራቸው ታላላቅ ሰዎች በትግራይ ተነስተው ነበር፣ እነሱም ለሥዕል አንሰግድም ምክንያቱም ሥዕል ሰሌዳ ነው፣ ለመስቀል አንሰግድም፣ ምክንያቱም መስቀል የጐሎጎታ እንጨት ነው ብለው ነበር።ይህንን ታሪካዊ አካባቢ ቡድኑ እያየ ነበር ዘበጣዘበጡን (escarpment) መውረድ የጀመረው።ከሁለት ሺ አራት መቶ ሜትር ከባሕር ጠለል በላይ ከፍታ ጀምሮ፣ በተጠማዘዘ ጥርጊያ መንገድ ወደ በረሃው ወርዶ መሐል ላይ ሲደርስ ነበር ለማመን የሚቸግር የመሬት ገፅታን ማየት የተቻለው፡፡

## የአፋር ስምጥ ሸለቆ እይታ

አፋር ስምጥ ሸለቆ ታች ደልዳላው ቦታ ቡድኑ ከመድረሱ በፊት፣ በግራ በኩል የሚታየው፣ ግዙፍ ጅብ ከመሬት የሆድ እቃ የቦጨቀው፣

የተቦደሰ ገደላ ገደል ነበር።በዚህ ግዙፍ ጥረሶች በቦጨቁት፣ ግዙፍ ጣቶች ባጎሰቋቆሉት የመሬት ገፅታ በድኑ ካለፈ በኋላ፣ ደልዳላው መሬት ላይ ከመደረሱ በፊት፣ በመጀመሪያ ጎጆ ቤቶች የሚያክሉ ቋጥኝ፣ ከዚያም መለስተኛ ይዘት ያሏቸው የድንጋይ ቋጥኞች በየቦታው ተፈነጋግለው መታየት ጀመሩ።ወደ በረሃው በተዘለቀ መጠን የሚታዩት የድንጋዮች መጠን እየቀነሰ ሄዶ፣ በመጨረሻ ኮረት መሰል፣ ጠጠር፣ ከዚያም አሸዋ ላይ ይደረሳል።ግዙፍ ቋጥኞች ተቦጭቀውበት የነበረው አካባቢ የተለያየ ቀለማት ያሉት፣ በብዛት ሰማያዊና ደብዛዛ ሮዝ መሰል፣ በገደሉ ደረት ላይ ይታዩ ነበር።

ታች ደልዳለው መሬት በአሸዋ የተሸፈነ ሲሆን፣ አሸዋው በንፋስ ኃይል ተገፍቶ፣ አንዳንድ ቦታ የተወቃ “ዳቦ ጤፍ” (ጥቁር ጤፍ|) የመሰለ ተከምሮ፣ አልፎ አልፎ ጉብ ብሎ ይታይ ነበር።እንዲሁም በአሸዋ መሬት ላይ አልፎ አልፎ የበቀሉ ንዑስ የእፅዋት ዝርያዎች ይታዩ ነበር።ከደጋ ዝናብ ሲዘንብ፣ ጎርፍ የሚወርድባቸው አካባቢዎች፣ በጣም ጥቂት ቢሆኑም በአካባቢው ነበሩ።

ከባሕር ጠለል በታች ያለው አብዛኛው አካባቢ፣ እፅዋት አልባ የሆነ፣ በደቃቅ አሸዋ የተላበሰ አካባቢ ነው።ቡድኑ ጉዞ በጀመረ በሁለተኛው ቀን ሲመሽ “ሃማዴላ” ከምትባል መናኸሪያ ደረሰ።ዋናው የአካባቢ ጥናቱ ትኩረት እዚች ቦታ አካባቢ ነበር።ሃማዴላ” በ2000 ዓ.ም መባቻ አካባቢ ሁለት ግለሰቦች (ባል እና ሚስት) ከአካባቢው ተጠልፈው፣ ታፍነው፣ ተወስደው ከብዙ ሳምንታት በኋላ ነበር በነፃ የተለቀቁ።እኛም እነሱ ተጠልፈው ከተወሰዱበት መጠለያ (ሆቴል) ነበር ያረፍነው፡፡

ቡድኑ በበነጋው ጠዋት ነበር የተነሳው፣ በበረሃ እስከ ረፋድ መተኛት ያዳግታል።ከዚያም በፊት ለፊት ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ተንጣሎ ይታይ ነበረው ገፅታ ነበር ከሁሉም በላይ ለቡድኑ እንግዳ የሆነው።ዳር ላይ ሸክላ መሰል ጭቃ፣ ከዚያም በአጭር ርቀት፣ መስተዋት መሰል፣ ወደ ነጭነት ያደላ፣ በስስ ደመና የተሸፈነ የሚመስል የመሬት ገፅታ ነበር የሚታይ።ከሩቅ ሰማይና መሬት የተገናኙበትን አካባቢ ለይቶ ለማየት በጣም አዳጋች ነበር፣ ከሩቅ ያለ ነጭ መጋረጃ መስሎ ነበር አካባቢው የሚታየው።ራቅ ብለው ሲያስተውሉት በሸክላማ ጥለት የተሸመነ ሰፊ፣ ጠንፍ አልባ ጋቢ መስሎ ነበር የሚታይ፡፡

“ከሃማዴላ” ወደ ደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ “አሳሌ ሃይቅ” ይታያል፣ ቀጥታውን ወደ ምሥራቅ እና ሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ የጨው አለት የሸፈነው አካባቢ ሲሆን፣ ይህን አካባቢ ከቅርብ መመልከት ቅዠት ውስጥ እንደመግባት ይመሰላል፣ በሆድ ሽብር ይለቃል፣ እይታን ያቃውሳል፣ የአንድን አካል ጥላ መሰል ገጽታ ዙሪያውን ማየት ይጀመራል።ከሁሉም አካባቢ ያለው የጨው ውሃ እንደመስተዋት ሆኖ፣ ለአንድ አካል ዙሪያውን ጥላ መሰል እይታ ያበረክታል።ይህ የጨው ሐይቅ፣ በከፊል ከታች፣ ወደ ፈሳሽነት ያደላ፤ ከላይ ጠጣር የሆነ አካባቢ ሲሆን፣ በዚህ የጨው አለት ላይ መኪና መንዳት ይቻላል፡፡፣

በጨው ላይ የሚሽከረከሩ መኪናዎች ከሩቅ ሲታዩ፣ ለአካባቢው ነፀብራቅ መንስዔ፣ በነጭ ጋቢ ላይ የሚሄዱ ሽረሪቶች ነበር የሚመስሉት።አንዳንድ በጨው ሐይቅ የቆሙ የቡድን አባላትም ትናንሽ ችካሎች መስለው ነበር የሚታዩት፣ በዚያ አካባቢ የአካልን ገፅታ ለይቶ ለማስተዋል ያዳግታል።በችካል መሰሉ አካል እና በአካባቢው ያለው የጨው ሐይቅ ድንበር በቅጡ መለየት አይቻልም።የፀሐይ ጨረርም እንዲሁም ወደ አምሳ ሴንቲግሬድ (50 0C) የሚጠጋ ሙቀት፣ ሁኔታውን ያባብሰዋል፡፡

በጨው አለት በተላበሰው አካባቢ አልፍ፣ አልፎ፣ ጉብ ጉብ ያሉ፣ ትናንሽ የቋጥኝ ድንጋይ ኮረብታዎች ይታያሉ።እንዲሁም በተለያዩ አካባቢዎች በሕብረ ቀለም ያሸበረቁ፣ አብዛኛው ቢጫ ቀመስ የድኝ ውሑድ ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ ሌሎች ቀለማት ያሏቸው፣ ለምሳሌ ሰማያዊ ቀመስ (የመዳብ ውሑድ መሰል ይዘት ያላቸው)፣ ሌሎች ደግሞ ደማቅ ቀይ (የብረት ውሑድ መሰል ቀለም የተጎናፀፉ)፣ እና ሌሎች ቀለማት የተላበሱ ብዙ አካባቢዎች ይታያሉ።ያንን ዓይነት የአካባቢ ይዘት በሌሎች የቱሪስት መስህብ በሆኑ የአገራችን አካባቢዎች አይታይም።

ከሰዓት በኋላ በመቶዎች የሚቆጠሩ፣ ከሩቅ ሲታዩ ጉንዳን መሰል አካላት ወደ ሰሜን አቅጣጫ ድንበር ሲመጡ ቡድኑ ተመለከተ፣ እየተጠጉ ሲመጡ ተከታትለው በሰልፍ በመዳዝ ላይ ያሉ ሲሆን፣ሰልፉ እየተጠጋ ሲመጣ፣ ሰልፉን የሚመሩት ወጣት ጠምዛዛ የበረሃ ጀግኖች፣ ተመሪዎች ጨው የተጫኑ ግመሎች መሆናቸውን ለመረዳት ተቻለ።ከሩቅ እነሱን (መሪዎችን) ከግመሎች ነጥሎ ለማየት ያዳጋታል።በአካባቢው የሚታይ ሌላ አካል ስለሌለ፣ ግመሎች ብቻ ናቸው በነፀብራቅ ጥላ መልክ ከሩቅ ሲያዘግሙ የሚታዩት።ያም በጨረቃ ላይ እንደሚሄድ ሰው ሰራሽ አካል ሊመሰል ይችላል፡፡

የሰልፉ ፍጥነት ሳይቀንስ፣ ሳይጨምር፣ ከአካላቱ ውጭ ባለ ኃይል የሚገፉ (በለሰስተኛ ነፋስ) ሰልፍ ነበር የሚመስለው።በጣም እየቀረቡ ሲመጡ ግመሎች፣የጨው አእማድን የተሸከሙ ግመሎች (የበረሃ ታንኮች) መሆናቸውን ቡድኑ በእርግጥ ለመረዳት ቻለ።እያንዳንዱ ግመል ከሁለት መቶ ኪሎ ግራም በላይ የወፍጮ መጅ መሰል የጨው ዓምድ ይሸከማል።ከቅርብ እርቀት ጉዞውን ለሚመለከት፣ ጉዞው፣ በእልከኛ፣ ግን የተዳከመ መሪ፣ ጉዞ የሰለቻቸውን ግመሎች የሚመራ ይመስላል።ያለማቋረጥ ተራ በተራ እግር ይነሳል፣ ከዚያም ወደፊት ይጣላል፣ ብሎም

ጉዞው ይቀጥላል፡፡

በዚያ ውሃ በሌለበት በረሃ፣ መሪም ተመሪም ውሃ ጥም መቋቋም አቅም አላቸው፣ መሪው በተለምዶ፣ ተመሪው በተፈጥሮ የተላበሱት አቅም ነው።ግመል ከማንኛውም አጥቢ እንስሳ በላይ ውሃ ጥም መቋቋም ችሎታ አላት፣ በበረሃው ውሃው ከአካሉ እየተነነ ሲወጣ፣ በአካሉ ውስጥ ያለው የጨው ሙኀረት (ውፍረት) አንፃራዊ ይዘት እየጨመረ ይሄዳል።ውሃ ሲገኝ ግመል ለቀናት የሚያስፈልጋትን ውሃ የመጠጣት አቅም አላት።ያ ሲሆን በአካሉ ውስጥ ያለው የጨው ሙኀረት (ውፍረት) አንፃራዊ ይዘት በጣም ይቀንሳል።ያም ሆኖ በአካል ውስጥ ያለው የፍሰት መጠን ሚዛኑን ጠብቆ፣ የአካላት ተግባር ሳይዛባ፣ ሳይቃወስ፣ ይቀጥላል፡፡

የጨው አለት በአንድ አካባቢ በምሳር (መጥረቢያ) ከተገዘገዘ በኋላ፣ ብዙ የአፋር ወጣቶች ተጋግዘው፣ ከስር አጣና አስገብተው፣ በአጣና ሰርስረው ተጋግዘው ይፈነቅሉታል።የተፈነቀለው ሰፊ የጨው ዓለት በምሳር እየተከረከመ የጨው መጅ መሰል ቅርፅ ይጎናፀፋል።እንዲሁም መጠነ ውስን የሆኑ የጨው አለት ንጣፎችን ዙሪያቸውን በመጥረቢያ ከገዘገዙ በኋላ፣ ተፈንቅለው ወጥተው፣ በመጥረቢያ የሚፈለገውን ቅርፅ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

የጨው መጅም ሆነ አሞሌ ጨው የማምረት ተግባር ሂደት ለዘመናት የተቀየረ አይመስልም።በነጭ ሜዳ መልክ የሚታየው የጨው አለት፣ በምሳር (መጥረቢያ) ከአራት አቅጣጫ ከተቆረጠ በኋላ ተመሳሳይ ቅርጽ እንዲይዝ ይጠረባል።የጨው መጅ በግምት 30 ሳ.ሜ፣ በ15 ሳ.ሜ እና በ 5 ሳ.ሜ ገደማ ስፋት እና ወርድ ይጠረባል።ከዚያም ለዚህ ተግባር በተዘጋጀ ገመድ ብጤ ይጠቀለል እና በመደራረብ በግመል ጀርባ ላይ ይጫናል።ለዚህ የጨው መገነገሃ የሚሆነው በአካባቢው በበረሃው ውስጥ የሚበቅል፣ ዘምባባ መሰል ዛፍ ቅጠል ነው የሚሸረበው።እፁ በአፋርኛ "ኀራይቶ" በመባል ሲታወቅ፣ ሳይንሳዊ ስያሜው "ሃይፌኔ ቴባቻ" (Hyphaene thebaica) ነው።የዚህ እፅ ቅጠል ጭረት በጣም ጠንካራ ስለሆነ፣ ቅጠሉ ለብዙ ዓይነት ቁሳቁስ ማበጃነት ያገለግል፣ ለምሳሌ የወተት ማለቢያ፣ የወተት/የቅቤ ማስቀመጫ፣ የውሃ መቅጃ፣ ወዘተ፡፡

ከዚያም ቡድኑ ሁለት ቀናት "ሃማዴላ" ካሳለፈ በኋላ ወደ አፍዴራ አመራ።በመንገድ ላይ ከሩቅ በስተምሥራቅ ኤርታ አሌ (Ert'ale) እሳተገሞራ ይታይ ነበር።በኢትዮጵያ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ለዘመናት በተለያዩ ጊዜያት የፈነዱ ብሎም የከሰሙና የተዳፈኑ (የሚያንቀላፉ/ያሸለቡ) እሳተገሞራዎች ይገኛሉ።አብዛኞቹ ከዘመናት በፊት የከሰሙ ቢሆኑም፣ ከሁለት መቶ ዓመት በፊት ገደማ የፈነዱ እና የተዳፈኑ ጥቂት አሉ፣ ከነሱም ቆኔ፣ ማንዳ-ኢናኪር፣ ቱሉ ሞዬ፣ ይገኙባቸዋል።ባለፈው ምዕተ ዓመት የፈነዱ እና የተዳፈኑ ብዙ ናቸው ለምሳሌ፣ አፍዴራ፣ አሌ ባጉ፣ አሉቶቱ ።በቅርብ ጊዜ ፈንድተው የተዳፈኑ፣ ዳባሁ፣ ዳፊላ እና ዳሎል እንደ ምሳሌነት ሊወሰዱ ይችላሉ።ብዙ ሰው የሚያውቀው አሁንም ሕያው የሆነውን ኤርታ አሌ (Ert'ale) እሳተ ገሞራ ሲሆን፣ ብዙ ጊዜ ስሟ የማይወሳው ዳሎል ረባዳ መሬት የምትገኘው ትንሿ "ካተሪን" (Catherine) እሳተገሞራ በዘመናችን አልፎ አልፎ ትፈነዳለች።የዳሎል ስምጥ ሸለቆ አካባቢ በብዛት በእሳተገሞራ ቅሪቶች የተሸፈነ ነው፡፡

መንገድ ላይ አንድ ቀን ካሳለፈ በኋላ በሁለተኛው ቀን አመሻሽ ላይ አፍዴራ ደረሰ።አፍዴራ ከፍተኛ የንግድ እንቅስቃሴ ይካሄድባት የነበረችው የበረሃ ጣቢያ ናት።ዋናው የንግድ መሠረት ጨው ማምረት ሲሆን፣ ከዚያም ተጓዳኝ አገልግሎቶች፣ ትራንስፖርት፣ ምግብ ቤትን፣ ወዘተ ያካትታል።ይህች ጣቢያ በቡድኑ በተጎበኘበት ጊዜ በደረቅ ጭነት መኪናዎች የተጣበበች ነበረች፡፡

ጨው የሚመረተው በኢንዱስትሪ መልክ ነበር።ሰፋፊ የእግር ኳስ ሜዳ የሚያክሉ ሁለት ሜትር ገደማ ተቆፍረው፣ የጨው ውሃ ከአፍዴራ ሐይቅ በፖምፓ እየተገፋ ወጥቶ፣ እነኝህን አናሳ ጥልቀት ያላቸው ሰፋፊ ጉድጓዶች እንዲሞላ ይደረጋል።በነገራችን ላይ በአፍዴራ ሐይቅ የሚገኘው ጨዋማ ውሃ፣ የጨው መጠን ባሕር ውስጥ ከሚገኘው መጠን በአምስት እጅ ይበልጣል (አምስት እጥፍ ይሆናል)፣ ምክንያቱም የሐይቁ ውሃ ለበረሃ ፀሐይ ትነት ስለሚዳረግ ነው፡፡

በነኝህ ሰፋፊ ሜዳዎች ገብቶ ለበረሃ ለፀሐይ የተጋለጠው የጨው ውሃ ተኖ እንዳለቀ፣ የጨው ንጣፍ (አለት) ብቻ ይቀራል።ይህ ሰፊ የጨው ሰፌድ አለት፣ በግንባታ መሣሪያዎች እየተከሰከሰ፣ እየተዛቀ ከጉድጓዶች ወጥቶ፣ በአሸቦ መልክ በአካባቢው እንደጠጠር ተከምሮ ይታያል፡፡

የአፍዴራ ሐይቅ ሰፊ መስተዋት መሰል ገፅታን ነው የሚያበረክት፣ በዚህ ሰፊ መስተዋት ውስጥ በስተምሥራቅ ያለውን የአፍዴራ የተዳፈነ እሳተ ገሞራ ተራራ፣ ድንኳን መሰል ቅርጽ ተጎናፅፎ ይታያል፡፡

## መደምደሚያ

በአፋር ስምጥ ሸለቆ ገና ያልተጠቀምንበት መጠነ ብዙ የጨው፣ የፖታሽ ማዕድን እና የሌሎች ለኢንዱስትሪ ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ ኬሚካዊ ውሑዶች ክምችት፣ ብሎም እምቅ ሃብት ያለበት አካባቢ አለ።አካባቢው የብዙ የተፈጥሮ ሃብት ክምችት ስለሚገኝበት፣ በዚህ ሃብት በተገቢ መንገድ ለመጠቀም ይቻላል።ዋናው ሃብት የጨው እና መሬት ማቅለጫነት የሚውሉ ኬሚካላዊ ውሑዶች ናቸው፡፡ውሃ ወደሚገኝበት የምዕራብ አቅጣጫ ለከብት ርቢ በተለይ ለግመል፣ ለበግና ፍየል ርቢ፣ በጣም ምቹ አካባቢዎች አሉ፡፡

እንዲሁም የአካባቢው ለየት ያለ ውበት የቱሪስት መስህብ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፣ አሁንም ቢሆን በመጠኑ እያገለገለ ነው።የስነ ሰብአት (Anthropology) ምርምር ጥናት በሰፊው ሊካሄደበት የሚችል፣ ብዙ የሕያው ቅሬት አካላት መገኛ አካባቢ ነው፣ "ሉሲም"/ "ድንቅነሽ" ከዚሁ አከባቢ ነው የተገኘችው።ስለሆነም አከባቢው ለሳይንሳዊ ምርምርም፣ እንዲሁም ለሳይንሳዊ ጉብኝት ብዙ ጠቀሜታን ያበረክታል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው በመጠኑም ቢሆን፣ አከባቢው የቱሪስት መስህብ በመሆን እያገለገለ ነው።ሆኖም የጉብኝቱ አያያዝ መስተናገድ ያለበት ሥርዓት በጥሞና ተጠንቶ ነው ወደ ተግባርነት መለወጥ የሚገባው፣ አሁን ያለው አያያዝ በሥርዓት የተከለለ አይመስልም።እንዲሁም በቱሪስት መልክ የሚደረጉ ጉብኝቶች ሆኑ፣ በተፈጥሮ ሃብት መጠቀም (ለምሳሌ ማዕድን) በተገቢው መንገድ ካልተከናወኑ ያልታሰቡ የአካባቢ ተግዳሮቶች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡

የበረሃው የወደፊት ዕጣ ፈንታ ባይታወቅም፣ አንዳንድ ግምታዊ አስተያየቶች መቅረብ ይበጃል የሚል እምነት አለን።አካባቢው የተዳፈኑ/ያንቀላፉ እሳተ ገሞራዎች ያሉበት አካባቢ እንደመሆኑ፣ በአካባቢው ያልታሰበ ከፍተኛ የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ ከተከሰተ፣ የአካባቢውን ይዘት በጠቅላላ ሊያቃውሰው ይችላል፡፡

ወደፊት የሚከሰተው ባይታወቅም፣ አሁን በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመሥርቶ መሪ እቅድ ተነድፎ፣ በእቅዱ መሠረት አካባቢው ደረጃ በደረጃ ሊለማ የሚችል፣ ብሎም ለሀገር ብዙ ሃብት የሚያበረክት ይሆናል ፡፡

# በበጎ ሰው ሽልማት
## የደመቀው በጎነት

ስሜነህ ደስታ

**ረዳት ፕሮፌሰር ዶክተር ኢንጂነር ውብሸት ዝቅአለ ተወልደው ያደጉት በቀድሞ አጠራር ናዝሬት ከተማ ነው። በንግድ ሥራ የሚተዳደሩት አባታቸው አቶ ዝቅአለ በከተማው ውስጥ የተለያዩ በጎ ተግባራት በመሥራት ይታወቃሉ። ልጃቸውም በጎ ተግባራትን በማየትና በመስራት ነው ያደጉት። በጎ የማድረግ ተግባራቸው በልጅነት ዘመናቸው ሳይወሰን አብሯቸው አድጎ እስከ አሁን ቀጥሏል። ይህ ሥራቸው የማታ ማታ ዕውቅና አግኝቶ በ2014 ዓ.ም. በትምህርት ዘርፍ የበጎ ሰው ሽልማት አሸልሟቸዋል።**

**ረዳት ፕሮፌሰሩ በዩኒቨርሲቲዎቻችን ባልተለመደ ሁኔታ ከተማሪዎች ጋር ሁሉ መግባባትና ቅርርብ በመፍጠራቸው፣ ከተመረቁም በኋላ በጓደኝነት እንዲሁም በቤተሰብ ደረጃ በመቀራረባቸው "አንተ ተማሪዎችን በጣም ስለምትቀርባቸው እኛን እያስደፈርክ ነው፤ ተማሪዎቻችንን እያበላሸሃቸው ነው" በሚል ከአንዴም ሁለት ጊዜ በስራ ባልደረቦቻቸው ቅሬታ ቀርቦባቸዋል። ከመደበኛ ስራቸው በተጨማሪ በተጠየቁበት ሀገራዊ ጉዳይ ላይ ሁሉ አስተዋጽኦ በማድረግ ለበርካታ አመታት በሙያቸው አገልግለዋል። ሀገራዊ ተሳትፎ ካደረጉባቸው ጉዳዮች ውስጥ ኢትዮጵያ የፕሮጀክት ማኔጅመንት ማንዋል እንዲኖራት ያደረጉት ጥረት ተጠቃሽ ነው። የመጽሔት ዝግጅት ክፍላችን የህይወትና የሥራ ልምዳቸው ሌሎችን ያስተምራል በማለት የፈለግ ዓምድ እንግዳ አድርጎ አቅርቧቸዋል። መልካም ንባብ!**



ረዳት ፕሮፌሰር ዶክተር ኢንጅነር ውብሸት ዝቅአለ የተወለዱት ህዳር 2 ቀን 1958 ዓ.ም. ሲሆን ለቤተሰባቸው ስድስተኛ ልጅ ናቸው። ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በመጀመሪያ ቄስ ት/ቤት በመቀጠል አፄ ገላውዲዮስ ት/ቤት በመግባት እስከ አስራሁለተኛ ክፍል በተወለዱበት ናዝሬት (በአሁኗ አዳማ) ከተማ ተምረዋል። በልጅነታቸው ማንበብ ከማዘውተራቸው በተጨማሪ እግር እና እጅ ኳስ ተጫውተዋል። አክሮባት መሥራትም በጣም ያስደስታቸው ነበር። በስፖርት የዳበረ ቁመና እንዳላቸው አሁንም ይታይባቸዋል። በተማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ በስፖርትና በድራማ ተሳታፊ ከመሆናቸው በተጨማሪ ጎበዝ ተማሪ ስለነበሩ እስከ ስምንተኛ ክፍል በተለይ በሂሳብ ትምህርት ከፍተኛውን ውጤት ያስመዘግቡ እንደነበር አጫውተውናል።

የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በነበሩ ጊዜ ለዕድሜያቸው ስነልቦና የማይመጥን ዘግናኝ ክስተት በሚማሩበት ክፍል ውስጥ አጋጥሟቸዋል። ይሄውም በደርግ የአስተዳደር ዘመን በነበረው የፖለቲካ ሁኔታ፣ ስምንተኛ ክፍል አስተማሪያቸው እያስተማራቸው እያለ አንድ ግለሰብ በመስኮት በኩል ሽጉጥ በመተኮስ መምህሩን በጥይት ሲመታው ያያሉ። ከዚያም የተመታው መምህር ደሙ ሲፈስ እንዲሁም ሲሞት አስተውለዋል። ይህም ጭንቅላታቸው ውስጥ ሁልጊዜ የማይረሱት ዘግናኝ ክስተት ሆኖ አሻራውን አሳርፎ አልፏል። በኋላም ሰርግ ቤት ውስጥ የኢህአፓ ወረቀት ተበትኗል በሚል ሰበብ በዚያ አካባቢ ያሉ ልጆች ሁሉ ታፍሰው ሲታሰሩ እሳቸውም ታስረዋል። ከታሰሩት ታዳጊ ልጆች መካከል ሁለት ልጆች (እሳቸውና የመምህር ልጅ) የውስጥ ሱሪ አድርጋችኋል በሚል ሰበብ ተለይተው "የአድሃሪ ልጆች" ተብለው በአሳሪዎቻቸው ተቀጥቅጠዋል። በዚህና በሌሎችም ምክንያት የተነሳ ፖለቲካን በልዩ ሁኔታ እንዲመለከቱና ሀገርን ለሚጠቅም ጉዳይ ሀሳብ ከመስጠት ውጭ፣ በሌሎች ጉዳይ ሳይገቡ የሌላውን ሀሳብና ሙያ አክብረው ከፖለቲካ ተሳትፎና ከስልጣን ፍላጎት ርቀው ለመኖር መርጠዋል።

በንግድ ሥራ የሚተዳደሩት አባታቸው ከአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ ተባብረው፣ ተረዳድተው እና ተቻችለው በመኖር ይታወቃሉ። (አሁን ድረስ ታክሲ የሚሳፈር ሰው "ዡቅአለ ሰፈር" አድርሰኝ ይላል)። ታዳጊ ውብሸትም የአባታቸውን በጎ ባህሪ መቅዳት የጀመሩት በልጅነታቸው ነው። ስምንተኛ ክፍል በሚማሩበት ጊዜ አንድ የክፍል ጓደኛቸው መኖሪያ ቤት ሲሄዱ በቤቱ ውስጥ አስር ያህል ልጆች እንደሚኖሩና የኑሯቸው ሁኔታም ዝቅተኛ መሆኑን ይረዳሉ። የክፍል ጓደኛቸው የኑሮ እንከን ሳያጋጥመው ትምህርቱን ጨርሶ ቤተሰቡን እንዲረዳ በሚል አባታቸውን አስፈቅደው ወደቤታቸው በማምጣት አንድ አልጋ ላይ እያደሩ፤ አብረው በመብላትና በማጥናት እየኖሩ እንዲማሩ አድርገዋል። ይህን በጎ ተግባር ካደጉም በኋላ ተማሪዎችን በሚማሩበት ጊዜም ሆነ ከተመረቁ በኋላ በሚችሉት መንገድ በማገዝ፣ ለዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች የሚችሉትን በማበርከት እንዲሁም የተቸገሩ ሰዎች ችግራቸው እንዲቀል የበኩላቸውን አስተዋጽኦ በማድረግ ገፍተውበታል። የአካባቢያቸው መንገድ ለኑሮ ምቹ እንዲሆን ሙያዊ አስተዋጽኦ አድርገዋል። በወረዳቸው ውስጥ በሚከናወን የልማት ሥራዎችም ይሳተፋሉ።

ረዳት ፕሮፌሰር ውብሸት የሚያውቁትን ሌሎች እንዲያውቁ ማስረዳትና ማስጠናት በጣም ይወዳሉ። በዚህ ተግባር የማተርፈው እኔ ነኝ ይላሉ። እንዴት እንደሚያተርፉ ሲያስረዱም አንደኛ ሰው በመርዳቴ ደስተኛ እሆናለሁ፤ ሁለተኛ ማወቄን አረጋግጥበታለሁ በማለት ይገልጻሉ። ይህን ተግባራቸውን በማሳደግ አስራ ሁለተኛ ክፍል መጋቢት ወር ላይ ማትሪክ ተፈትነው ከጨረሱ በኋላ ሌሎች ጓደኞቻቸው በመሰረተ ልማት ዘመቻ ሌላ ስፍራ ተመድበው ሲሄዱ፤ እሳቸው በወሊድ ምክንያት ፈቃድ የወሰደችን የዘጠነኛ ክፍል የፊዚክስ መምህርት ቦታ በመሸፈን ቀሪውን ጊዜ በመደበኛነት አስተምረዋል።

እናታቸው ከአባታቸው ባልተናነሰ ሁኔታ ሁሉ ነገር እንዳይጎድልባቸው አድርገው ነው ያሳደጓቸው። ትምህርታቸውን በተመለከተ ከፍተኛ ማበረታታትና ድጋፍ ያደርጉላቸው እንደነበረ ምስጋና በማቅረብ ያስታውሳሉ። የወለዷቸው እናታቸው በልጅነታቸው በሞት እንደተለዩዋቸው እንዲሁም ያሳደጓቸው እናት፣ እንጀራ እናታቸው መሆናቸውን ያወቁት ሁለተኛ ደረጃ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ሆነው እንደነበረ ይናገራሉ። ይህ እናታዊ ፍቅራቸውን በማየት፣ ሳይወልዱ የሚያሳድጉ እናቶች ላይ የሚሰነዘሩ አባባሎች ለሁሉም ስለማይሠራ ሊፈተሹ እንደሚገባ ይጠቁማሉ።

እንግዳችን ሁለተኛ ደረጃ መማር እንደጀመሩ የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት ጨዋታ በማብዛታቸው ሁለተኛ ይወጣሉ። አንደኛ የወጣው ተማሪ በቀጣይም እንደሚበልጣቸው ኮራ ብሎ ይነግራቸዋል። በቀጣዩ ጊዜ ጨዋታቸውን ቀንሰው በማንበባቸው በሁለተኛው መንፈቀ ዓመትም ሆነ በአማካይ ውጤት አንደኛ ወጥተዋል። በዚህም በጤናማ የውድድር መንፈስ ራስን ማበርታት እንደሚቻል ተምረውበታል።

ዘጠነኛ ክፍል ሌላው የገጠማቸው ጉዳይ የሂሳብ ትምህርት መጀመሪያ መቶ በመቶ ያመጣሉ፤ ሁለተኛው ላይ ዘጠና ስምንት ከመቶ አመጡ። ለምን ሁለት ማርክ ተቀነሰብኝ መልሱን ልክ ነኝ ብለው አስተማሪያቸውን ሲጠይቁ «ልክ ነው ውጤቱን አምጥተሃል፣ ሂደቱን ግን አልተከተልክም» በማለት ምላሽ ይሰጣቸዋል። ከዚያም አንድ ደረጃ በመዝለል መሥራታቸውን በመረዳት፣ ሂደትንም ውጤትንም ማክበር እንደሚገባቸው ትምህርት መውሰዳቸውን ይናገራሉ።

በአፄ ገላውዲዮስ ትምህርት ቤት በ1974 ዓ.ም. የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ከተፈተኑት መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ 12 ተማሪዎች ከማዕረግ በላይ አምጥተው ዩኒቨርሲቲ ሲገቡ እንግዳችን አንዱና ቀዳሚው ነበሩ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በ16 ዓመታቸው በመግባትም በሲቪል ኢንጂነሪንግ በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቀዋል። ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ደግሞ ስትራክቸራል ኢንጅነሪንግ ተምረው ከእንግሊዝ ሀገር አግኝተዋል። ሶስተኛ ዲግሪያቸውን ኖርዌይ



ሀገር ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ማኔጅመንት በመማር አጠናቀዋል። በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የኮንስራክሽን ማኔጅመንት ዶክተር ሲሆኑ በወቅቱ በአፍሪካ ውስጥ ሶስት ብቻ ነበሩ። በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ አለመግባባቶች ሲከሰቱና ፍርድ ሲሰጥ አንዳንድ ውሳኔዎች ልክ አልመስል ሲላቸው ደግሞ ህግ በመማር ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪ አግኝተዋል። ባገኙት የህግ ዕውቀትም በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ በግልግል ዳኝነት፣ ዋና(መሃል) እንዲሁም የግራና የቀኝ የግልግል ዳኛ በመሆን ሠርተዋል። በዚህም የግልግል ዳኝነቱ ውጤታማ ሆኖ እንዲያድግ ካደረጉ ሰዎች አንዱ ለመሆን በቅተዋል።

ረዳት ፕሮፌሰር ውብሸት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን እንዳገኙ በከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን ውስጥ የፊዚካል ፕላን ማስተባበሪያ ቢሮ ውስጥ ተመድበው መሥራት ጀምረዋል። አዲስ አበባ ውስጥ ቫቲካን ኤንባሲ ጎን ባለ አንድ ፎቅ የዘጠኝ ቤቶች ዲዛይን ሠርተው፣ ሱፐርቫይዝ አድርገው ጨርሰው የመጀመሪያ ሥራቸውን አስረክበዋል። በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ሶስት ሳኒቴሪ ኢንጅነሮች ብቻ ነበሩ። ከሲቪል ኢንጅነሮች የተመረጡ 21 ሰልጣኞች በሳኒቴሪ ስልጠና ሲሰለጥኑ እንግዳችንም ሰልጥነዋል። በዚህ ስልጠናም አንደኛ ወጥተው ተሸልመዋል። በስልጠናው ባገኙት ዕውቀት በመጠቀም የዘጠኙን ቤቶች የሳኒቴሪ ሥራውን የሠሩት እሳቸው ናቸው።

እንግሊዝ ሀገር ማስተርስ ሲማሩ የሁለት ዓመቱን ኮርስ በአንድ ዓመት ነው ያጠናቀቁት። በዚህ ምክንያት ሥራ ለመሥራት ጊዜ ስላገኙ በቻርተርድ ስትራክቸራል ኢንጅነሪንግ ሠርቲፋይድ(የሥራ ፈቃድ) ለማግኘት ዘጠኝ ሰዎች ሲፈተኑ ብቸኛው ጥቁር እሳቸው ነበሩ። ከተፈታኞች መካከል ያለፉት ሁለት ሲሆኑ አንደኛው ሁለት ጊዜ ወድቆ በሶስተኛው ያለፈ የሀገሩ ዜጋ ሲሆን፣ እሳቸው ግን በመጀመሪያ ፈተና አልፈዋል። በዚህ ሠርተፍኬት የመመረቂያ ጽሑፋቸውን እየሠሩ ለአንድ ዓመት በድርጅት ውስጥ ተቀጥረው አመርቂ ሥራ ሠርተዋል። ድርጅቱ የሥራ ትጋታቸውንና አፈፃፀማቸውን አይቶ ትምህርታቸውን ሲጨርሱ ሴኔጋል ወይም ሆንግ ኮንግ በሚገኙት ቅርንጫፎቹ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሆነው እንዲሠሩ አጥብቆ ጠይቋቸው ነበር። እሳቸው ግን ወደሀገራቸው መመለስ መርጠው መጥተዋል።

እንግዳችን ኢትዮጵያ ውስጥ አዲስ ነገር ለመሞከርም ሆነ ለመሥራት በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ እንዳለ የራሳቸውን የሥራ ተሞክሮ በመግለጽ ያስረዳሉ። ካጋጠማቸው ውስጥ አንደኛውን ሲገልጹ ጎባ ውስጥ አንድ ዲዛይን እንዲሠራ ቢሯቸው ይመረጥና ለሥራ ይሄዳሉ። ቦታው ጥቁር መረሬ አፈር ያለበት ነው፤ መሰረት ለመጣል ውሃውን ለማግኘት እስከ 14 ሜትር ወደታች መቆፈር ያስፈልጋል። ጥቁር መረሬ አፈር ያለበት አካባቢ የተለመደው ሶስት ወይም አራት ሜትር ለሚረዝም ቤት ውሃ እስከሚገኝበት ድረስ ወርዶ መሰረት መሥራት ነው። "እንዴት ይህ ይሆናል?



በምን መልኩ ማሻሻያ ማድረግ ይቻላል?" በማለት ጥናት ያደርጋሉ። እሳቸው በተማሩበት አውሮፓ መረሬ አፈር ስለሌለ መረጃ አላገኙም። ደቡብ አፍሪካና ህንድ የተጠና ጥናት አግኝተው ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ባደረጉት ምርምር ከ 0.65 እስከ 1.20 ሜትር ወርዶ መሰረት ለመጣል የሚያስችል መንገድ አገኙ። ይህንንም ዲዛይን አድርገው ሊያጸድቁ ሲሄዱ ከተለመደው የተለየ ነገር ይዘው ስለቀረቡ አጽዳቂዎቹ "የፍሬሽ ነገር" በማለት ሥራቸውን አናናቁባቸው።

አጽዳቂዎቹ ቢያናንቁባቸውም ወደ ተግባር ሊለወጥ የሚችል የሚሠራ ሀሳብ ይዘው ስለተነሱ ተስፋ ሳይቆርጡ የወቅቱ የዲዛይን ሥራ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስፈፃሚ ኢንጂነር ካሳ ኃይሌ ዘንድ በመሄድ ያደረጉትን ጥናትና ምርምር ያስረዳሉ። ኢንጂነር ካሳ ኃይሌም በጥሞና ካዳመጡ በኋላ "ኃላፊነት እወስዳለሁ፤ ይፈቀድለት" በማለታቸው ሥራው ተጠናቆ ቤቶቹ እስከ አሁን ድረስ እንከን ሳያጋጥማቸው እያገለገሉ ይገኛሉ። አዲስ ነገር ተሞክሮ፣ መሥራቱ ታይቶ ሌላው መቀበልና መከተል ሲገባው፤ የሚያሳዝነው ነገር እስከ አሁን ድረስ ውሃ እስከሚገኝበት ድረስ ወርዶ እየተቆፈረ መሰረት በመገንባት ገንዘባችን መሬት ውስጥ እየቀበርን እንኖራለን በማለት ሀዘናቸውን በምሬት ይገልጻሉ። ይሄን ዘመን የምንኖር ሰዎች ለቀጣይ ትውልድ መልካም ነገር በማሰብ ብዙ ነገሮችን በማገናዘብ የተሻለች ኢትዮጵያን ለማምጣት ቴክኖሎጂን ከሀገር በቀል ዕውቀት ጋር በማቀናጀት መሥራት ይገባናል በማለትም ያሳስባሉ።

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በኢትዮጵያ ውስጥ በአብዛኛው በባህላዊ መንገድ ነው እየተመራና እየተሠራ ያለው። ይህን ለማዘመን ብዙ ጥረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ የሚገልጹት እንግዳችን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማስተማር ጊዚያቸው በግላቸው ከ80 በላይ በሀገር ላይ የሚያተኩር ለችግር መፍትሔ ሊሆን የሚችል ጽሑፍ አቅርበዋል(በውጭ ሀገር ላይ በማተኮር፣ በሌሎች ጆርናል የሚወጣ 80 ጽሑፍ ቢጽፉ ኖሮ ከረዳት ፕሮፌሰር የበለጠ ማዕረግ ያገኙ እንደነበር ይናገራሉ)። የፒኤችዲ መመረቂያ ጽሑፋቸውንም በሀገራቸው ላይ ሠርተዋል። ከዚህ በተጨማሪ በኮንስራክሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ ስታንደርድ ወጥቶለት ያልተመራውን፣ ሁሉም እንደመሰለው የሚሠራበትን ጥናት በማድረግ 21 የፕሮጀክት ማኔጅመንት የዕውቀት መስኮችን ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው አዘጋጅተዋል።

ለኢትዮጵያ የፕሮጀክት ማኔጅመንት ማንዋል ሲዘጋጅ በመንግሥት ተመርጠው ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር በመሆን አስራ ስምንቱን በመውሰድ በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውል በማድረጉ ሂደት የበኩላቸውን ጥረት አከናውነዋል። ይሄ ስራቸው ኮንስራክሽን ኢንዱስትሪው ወጥ የሆነ አንድ ስታንዳርድ ስለተበጀለት በባህላዊ መንገድ መመራቱ ቀርቶ በዕውቀትና በቴክኖሎጂ እንዲመራ ያደርገዋል፣ የፕሮጀክት አፈጻጸም እንዲሻሻል ያደርጋል እንዲሁም ኩባንያዎችም ትርፋማ እየሆኑ ስለሚሄዱ ተወዳዳሪ ይሆናሉ። ስለሆነም ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ማኑዋሉ አስፈላጊ ነው።

ረዳት ፕሮፌሰር ውብሸት በማስተማር ሂደት ውስጥ ብዙ ጊዜ በዩኒቨርሲቲዎቻችን ባልተለመደ ሁኔታ ከተማሪዎች ጋር ሁሉ መግባባትና ቅርርብ ይፈጥራሉ። ተማሪዎቹ ከተመረቁም በኋላ በጓደኝነት እንዲሁም በቤተሰብ ደረጃ ይቀራረባሉ። በዚህም "አንተ ተማሪዎችን በጣም ስለምትቀርባቸው እኛን እያስደፈርክ ነው፤ ተማሪዎቻችንን እያበላሸሃቸው ነው" በሚል ከአንዴም ሁለት ጊዜ በባልደረቦቻቸው ቅሬታ ቀርቦባቸዋል። እሳቸው ግን መልካም እየሠራሁ ነው ብለው ስለሚያስቡ በዚያው ቀጥለዋል። ተማሪዎች ሀገራዊ ዕውቀት እንዲኖራቸው እና ተግባራዊ የሆነ አሠራር እንዲለምዱ በሚል በአብዛኛው የመስክ ሥራ ሠርተው እንዲመጡ በማድረጋቸው፣ በወረቀት ፈተና ላይ የተመሰረተውን አሠራር በመፈተናቸውም ችግር ገጥሟቸው ያውቃል። ይህንንም ጥሩ ነገር እስከሠራሁ ድረስ ሊያስጨንቀኝ አይገባም በማለት አልፈውታል። ተማሪዎቻቸው ግን በስማቸው "ጃክ ዴይ" በሚል በማዘጋጀት የሰጧቸውን ዕውቅና እና ሽልማት እስከመቼውም ጊዜ ድረስ የሚያስደስታቸው፤ እንዲሁም የማይዘነጉት ተግባር እንደሆነ ፊታቸውን ፈካ አድርገው ያስታውሳሉ።

ከአስተማሯቸው ተማሪዎች መካከል የሙያ ስነምግባር አክብረው የሚሠሩ ባለሙያዎች፣ ደረጃ አንድ ኮንትራክተር፣ ጥሩ አማካሪዎች እና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው መሪ ሆነው ያገኟቸው አሉ። ለአብነት ሲጠቅሱ «የአዲስ አበባ መስተዳድር የመንገዶች ባለስልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ሞገስ ጥበቡ በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሠራውን ሥራ ከተማዋን ውብ እንዳስመሰላት ሁሉም የሚመሰክረው ነው። ጥረቱን ስመለከት ለሚቀጥለው ትውልድ ተግቶ የሚሠራ አድርጌ ነው የምወስደው። ዶክተር አብርሃም አሰፋ ግዙፍ የሆነውን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ህንጻ ዋና መሃንዲስ ሆኖ ሠርቷል፤ ይህ ቀላል ሥራ አይደለም። የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ ትልቅ ሥራ እየሠራ ያለ ኢንጅነር ነው» ብለዋል። አክለውም ሌሎች ተማሪዎቻቸውም በተለያዩ የሥራ ኃላፊነት ላይ እንደሚገኙ በኩራት ይናገራሉ።

ረዳት ፕሮፌሰር ውብሸት ወደኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዓለም ለሚቀላቀሉ ተመራቂዎች ዓለም አቀፍ የሆነውን ዕውቀት ለሀገር ሊጠቅም በሚችል መልኩ ከሀገር በቀሉ ዕውቀት ጋር በማዛመድና በማዋሃድ ተግባር ላይ ተግተው መሥራት እንደሚገባቸው ይመክራሉ። ከዚህ በተጨማሪ ቴክኖሎጂን ለማሸጋገር ጥረት ማድረግ ለዚህም የህይወት ዘመን አንባቢ መሆን እንደሚያስፈልጋቸው የራሳቸውን ተሞክሮ በማሳያነት በመጥቀስ ያሳስባሉ። ተመራቂ ባለሙያዎች በሙያ ስነምግባር ታንጸው ኢንዱስትሪውን መምራት ከቻሉ ለራሳቸውም ለሀገራቱም ጠቃሚ መሆን እንደሚችሉ ያስገነዝባሉ። ስለሆነም ባለሙያዎቹ አሁን ያለው ትውልድ መክፈል ያለበትን መስዋዕትነት ከፍሎ፣ የሚቀጥለው ትውልድ ከጭንቀትና ከድህነት የሚወጣበትን መንገድ መፍጠር አለበት የሚለውን የሚቀበሉ ሆነው በጎነትን የሚተገብሩ እንዲሆኑ መልዕክት ያስተላልፋሉ።

ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ባለሀብቶች ደግሞ ሥራን ለማግኘት ብለው የሚሄዱበትን ተገቢ ያልሆነ አካሄድ እና ሳያነቡ የሚፈርሙበትን መንገድ ማቆም እንዳለባቸው በማሳሰብ በዝቅተኛ ዋጋ ገብተው በሌላ መንገድ ለመክበር የሚያደርጉትን አካሄድ ማቆም ይኖርባቸዋል ሲሉ ይመክራሉ። የሙያ ስነምግባርን አክብሮ ሀገርን መጥቀም እንዲሁም ትርፍ ማግኘት እንደሚቻል እንዲሁም አንድ የውጭ ኮንትራክተር ከሚመጣ ስድስቱ ባለሃብቶች አንድ ላይ ሆነው ቢሠሩ አብሮ መሥራትና ጥራትን ከመለማመዳቸው በተጨማሪ ዕድገት እንደሚገኝ ያሳስባሉ።

እንግዳችን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከማስተማር ሥራቸው በተጨማሪ ለተለያዩ ድርጅቶች የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ይሰጣሉ። የሰጧቸው ሥልጠናዎች ቢሰሉ ከ900 በላይ ይሆናሉ። በሙያ ማህበራቸው ውስጥ በአመራርነት ከማገልገላቸው በተጨማሪ ንቁ ተሳታፊ ናቸው። የዩኒቨርሲቲ መምህር የአማካሪ ቢሮ ከፍቶ መሥራት ስለሚችል በግላቸው "ዡቅ አለ የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት አማካሪ" የሚል ድርጅት በማቋቋም እየሠሩ ይገኛሉ። በዚህም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው እንዲያድግ

የተለያዩ ሥራዎች ሠርተዋል። የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን በተመለከተ የ30 ዓመት ፍኖተ ካርታ እና የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ ሲሠራ ከፍተኛ አማካሪ ሆነው አገልግለዋል። መንግሥትም ትልቅ ችግሮች ባሉበት የኮንስትራክሽን ሥራዎች እየወከላቸው ያላቸውን የተወዳዳሪነት ችሎታ በመጠቀም ተደራድረዋል። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ህንጻ ሲሰራ ከሁለት መቶ ዘጠና አራት ወደ ሁለት መቶ ሰላሳ ሰባት ሚሊዮን ዶላር ዝቅ ብሎ ውል እንዲፈጸም አስደርገዋል። ከዚህ በተጨማሪ በጊዜው በነበረው የውጭ ምንዛሪ እንዲሰላ በማስደረጋቸው ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ እንዳይሆን አድርገዋል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ የመሃለኛው ተርምናል ጣራው ሲሠራ ችግር ስለነበረበት ተደራድረው እስከ 2.8 ሚሊዮን ዶላር ማስመለሳቸውም በተደራዳሪነታቸው የሚጠቀስ አስተዋጽኦ ነው። ሌሎችም የፋይናንስ ተቋማት ሰማይ ጠቀስ ህንጻዎች ሲሠሩ ከጨረታ ጀምሮ እስከ ትግበራ በማማከር እየሠሩ ይገኛሉ።

ረዳት ፕሮፌሰሩ ስለ አዲሱ ትምህርት ፖሊሲ ሲናገሩ ሊሠራ የሚችል መሆኑን ይገልጻሉ። ፖሊሲው ማህበራዊ ግንኙነትን ያሳድጋል፣ የሀገርን ተምሳሌት ያመጣል፣ በተናጠል ማሰብን ያስቀራል የሚል ዕምነት አላቸው። ነገር ግን ፖሊሲውን ተማሪው፣ አስተማሪው እንዲሁም ህብረተሰቡ እንዲያውቀው ማስረጽ እንደሚቀረው ያሳስባሉ። ይሄ ደግሞ መሰረታዊ ጉዳይ ስለሆነ እኔ የማውቀውና አብሮኝ የሚያስተምረው ሌላው የሚያውቀው ተቀራራቢ ሊሆን ይገባል፤ አብዛኛው ህብረተሰብ የሚለውና የሚያውቀው አስረኛ ክፍል ይሰጥ የነበረው ፈተና ቀርቶ አስራ ሁለተኛ ክፍል ሆነ የሚለውን ነው። ስለሆነም አተገባበሩ ጥሩ እንዲሆን በሁሉም ዘንድ በተገቢ ሁኔታ ፖሊሲው መስረጽ ይገባዋል ይላሉ። ይሄ ፖሊሲ ያመጣው በጣም ጥሩ ነገር ብዬ የምለው ግብረገብ እና ሀገር በቀል ዕውቀት ላይ ትኩረት መስጠቱ ነው በማለት በጎ ጎኑን አጉልተው ያነሳሉ።

ረዳት ፕሮፌሰር ውብሸት በትምህርት ዘርፍ ከነበሩት ዕጩዎች ልቀው የበጎ ሰው ሽልማት በመሸለማቸው ደስተኛ ናቸው። ላገኙት ዕውቀናም ምስጋና ያቀርባሉ። ስለሽልማቱ ሲናገሩ «መምህር ተማሪዎች ዕውቀት፣ ብቃት እና በጎነት እንዲኖራቸው በማድረግ የሚያስተምር ነው። ተማሪዎች በምክንያታዊነት፣ በተረጋገጡና በርትዕ መንገዶች ግንኙነታቸውን እንዲመሰርቱ እንዲሁም ለህብረተሰቡ የተሻለ ሁኔታ መፍጠር እንዲችሉ አድርጎ ማብቃት ከመምህር የሚጠበቅ ተግባር ነው። ይሄን የመምህርነት ሥራ የሚያበረታታ ሲገኝ የተሻለ ህብረተሰብ ይፈጠራል። በመሆኑም ይህ የማበረታታት ተግባር ይቀጥል፣ ይደግ ብዬ ነው የምመኘው። የምችለውንና የማምንበትን ሠርቻለሁ፤ ሽልማቱ የእኔ ብቻ ሳይሆን አብረውኝ የሠሩ ሁሉ የሚጋሩት ነው። ከሁሉም በላይ ያስደሰተኝ በጎ መሥራትን ማበረታታት የሚችል ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ መፈጠሩና መኖሩ የወደፊት የሀገሬን ተስፋ ከማሳየቱ በላይ ሌሎችም ለበጎነት እንዲተጉ ያደርጋቸዋል። የእኔን ሽልማት አይተው ሌሎችም የተሻለ ሥራ ይሠራሉ፤ እኔም የበለጠ መሥራት እንዳለብኝ ኃላፊነት ተጨኖብኛል» በማለት ያስረዳሉ።



ከበጎ ሰው ሽልማት በተጨማሪ ከተማሪዎቻቸው፣ ከሙያ ማህበራቸው፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ከጎህ ቤቶች ባንክ፣ ወዘተ. የተለያዩ ሽልማቶች አግኝተዋል። የአዲስ አበባ አስተዳደር የህይወት ዘመን የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ባለሙያ ብሎም ሸልሟቸዋል። ከኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂና ማኔጅመንት ባለሙያዎች ማህበር ልዩ የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ባለሙያ በመባልም ሽልማት አግኝተዋል። ከሁሉም ሽልማቶች የሚያስደስታቸው ያገለገሉዋቸው ሲሸልሟቸው ነው። በተለይ የተማሪዎቻቸውን ሽልማት ከፍተኛ ሥፍራ ይሰጡታል።

ዕውቀትን፣ ዕምነትን እና በጎነትን በማጣመር ራስን በመምራት መኖር የሚል የህይወት ፍልስፍና የሚከተሉት እንግዳችን ባለትዳር እና የሁለት ሴት ልጆች አባት ናቸው። የመጀመሪያ ልጃቸው ሁለተኛ ዲግሪ ያላት ሲሆን፣ ሁለተኛዋ የመጀመሪያ ዲግሪ አላት። ልጆቻቸው በራስ መተማመን እንዲኖራቸው፣ የበታችነትም የበላይነትም መንፈስ እንዳይኖራቸው አድርገው እንዳሳደጓቸው፤ በዚህም ተሳክቶልኛል ብለው እንደሚያስቡ ይናገራሉ። ባለቤታቸው ለስኬቱ በከፍተኛ ሁኔታ እንዳገዟቸውም ያስረዳሉ። ቤተሰብን ከማስተዳደር አንጻር ከባለቤታቸው ጋር ተግባብተው ከመኖራቸው በተጨማሪ ሚስታቸውንም አክባሪ ናቸው። ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር በሚኖራቸው ስብሰባ ላይ ባለቤታቸው ከደወሉ "ሚስት ቅዱስ" በማለት ይቅርታ ጠይቀው ወጥተው ያናግራሉ። ይህን በተደጋጋሚ ጊዜ ሲተገብሩ የተመለከቱ ባልደረቦቻቸው "እኛ ሚስቶቻችንን ፌደራል፣ አልቃይዳ፣ ወዘተ. እያልን ነው የምንጠራው አንተ እንዴት ነው ቅዱስ እያልክ የምትጠራው?" ሲሏቸው "ሚስትን ቅዱስ ብላችሁ ከጠራችሁ፣ ባለቤታችሁ እንደተመኛችሁት ቅዱስ ትሆናለች፤ ሌላም ካላችሁ፣ እንዳስተሳሰባችሁና እንዳያያዛችሁ ትሆናለች" በማለት በመመለሳቸው አንዳንዶቹ "ሚስት ቅዱስ" ማለት እንደጀመሩ ያስታውሳሉ።

በሚኖሩበት አካባቢ መደበኛ ዕድር የላቸውም። በመደበኛው ዕድር እንዳይሳተፉ ያደረጋቸው ደግሞ የዕድሩን ህግና ስርዓት አክብረው ሁል ጊዜ መሳተፍ እንዳይችሉ የሥራ ሁኔታቸው ስለማይፈቅድላቸው ነው። ይህ ይሁን እንጂ ከመደበኛው የዕድር አባላት ባልተናነሰ በሚመቻቸው ጊዜ በሀዘናቸውም በደስታቸውም ከአካባቢያቸው ሰዎች ጋር ይሳተፋሉ። በዚህም ምክንያት እሳቸው ሀዘን ሲያጋጥማቸው የሰፈራቸው ዕድር አባላት የሚያስፈልግ ቁሳቁስ በነጻ በማቅረብ ይተባበሯቸዋል፤ ያስተሳዝኗቸዋል። መደበኛ ዕድር ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ለመሳተፍ የተቸገሩ ሰዎች ከእሳቸው ተሞክሮ ቢወስዱ በአካባቢያቸው ዘንድ መልካም ግንኙነት ለመፍጠር ያግዛቸዋል።

ረዳት ፕሮፌሰር ውብሸት በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዕውቀትን፣ ቴክኖሎጂን፣ ዕምነትን እና ሥነምግባርን እንደትልቅ ጠቃሚ ጉዳይ አይተው እንዲኖሩ፤ ጊዜያዊ ጥቅም በማየት ከእነዚህ ነገሮች መራቅ እንደማይገባ ይመክራሉ። ትምህርት ተምሮ ሥራ የለም በሚል በአብዛኛው ተማሪዎች አስረኛ ክፍል ትምህርት እያቆሙ ነው የሚል መረጃ መስማታቸውን በመግለጽ፣ ወደፊት ኢትዮጵያ የተሻለ ሁኔታ ውስጥ ገብታ እንደምትታይ ተስፋ ስለሚታይ ከዕውቀት መራቅ እንደማይገባ በማሳሰብ ምክራቸውንም ቆይታቸውንም ይቋጫሉ።